
# የአማራው ሕዝብ
# ከዬት ወዴት



# የአማራው ሕዝብ
# ከዩት ወዴት

ከአንዳርጋቸው ጽጌ

አዲስ አበባ
ሰኔ 1985

## ምስጋና

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በሰፈሩ ሃሳቦች ላይ ረጅም ሰዓታት የፈጀ ውይይት በማድረግ ሃሳቦችን በማዳበርና በማጥራት ያልተቆጠበ ድጋፋቸው ላልተለየኝ ለአቶ ሚሊዮን አሰፋ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

እንዳርጋቸው ጽጌ

## የጽሁፍ መታሰቢያነት

በረጅሙ የአማራው ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ለነፃነት ፣ ለፍትህና ፣ ለእኩልነት ለወደቁ አማሮች በሙሉ መታሰቢያ ትሁን ።

## ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 3 |
| ምዕራፍ አንድ<br>ብሔረተኝነት በኢትዮጵያ ፈጠራ ወይንስ እውነታ | 7 |
| ምዕራፍ ሁለት<br>ኢትዮጵያዊነት የሁሉም ብሔር ሕዝቦች የጋራ የዜግነት መግለጫ ወይንስ ብሄሮችን የተካ ራሱን የቻለ ብሔረተኝነት<br>— ከስነልቦና ጭንቀት የሚመነጭ ችግር<br>— ከጠንካራ ብሄራዊ ማንነት አለመኖር የሚመጣ ችግር<br>— ከነቃ የፖለቲካ ተቃውሞ የሚመነጭ ችግር | 13 |
| ምዕራፍ ሶስት<br>አማራነት ምንድነው ?<br>— በግድፈት የተደረሰበት ማንነት<br>— አማራነት የተሸፈነ እንጂ የጠፋ ስሜት አይደለም<br>— አማራነትን ደምና አጥንት አይገልፀውም | 25 |
| ምዕራፍ አራት<br>አማራነትና ብሔረተኝነት<br>— ጭፍን ብሔረተኝነትን የማይቀበል የአማራ ብሔረተኝነት ከቶውኑ ሊኖር አይችልም | 32 |
| ምዕራፍ አምስት<br>ለአደማሳዊ ጭቆና የአማራው ምሁር ብቸኛ ምላሽ አደማሳዊ ፀረ ጭቆና ትግል ነበር<br>— ታህሳስ 1953<br>— የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ<br>— 1966 የካቲትና ከየካቲት በኋላ<br>— ከኢህአፓ ውድቀት በኋላ | 42 |
| ምዕራፍ ስድስት<br>አዲሱ እውነታና የአማራው ሕዝብ የውክልና ጥያቄ | 55 |
| ምዕራፍ ሰባት<br>ቅርብና እሩቅ ላላችሁ አማሮች በሙሉ | 59 |

# መግቢያ

ዙሪያችንን ስንቃኘው አውላላ ሜዳ ላይ ብቻችንን ቆመናል ።
ግማሹ እንገቱን ደፍቷል ። ከፊሉም መንገድ የጠፋበት ይመስላል ።
ገሚሱም እንደ ዕብደት አድርጎታል ። ቀሪው ብዙኃኑ በያለበት ኩር
ምት ጭርምት ብሎ ተቀምጧል ። ይህ ሁኔታ ነው ፤ ምነው ጉብዝ ምን
ነካን ያሰኘን ። የአማራ ብሔረተኝነት ዕሑፍ ምንጭ ይህ አሳዛኝና
አሳሳቢ ቅርሊት ነው ።

ስለ ብሔረተኝነት ስናነሳባችሁ አንዳንዶቻችሁ ምነው ጃል
ዓለም ወደ አንድነት በሚጓዝበት ዘመን ይህን ጉድ ታመጡብናላ
ችሁ እንደምትሉ እናውቃለን ። ዓለም ወደ አንድነት መጓዙን ግን
እኛም አላጣነውም ። የኢኮኖሚ ግንኙነቱ የንግድ ልውውጡ እርስ
በርሱ የተተበተበ የገንዘብ ሲስተም ፣ የቴሌፎን ፣ የቴሌክሱ ፣ የፋክሱ
የሳተላይት ግንኙነቶች ፣ የዜናና የመረጃ አብዮት የቴክኖሎጂ ዕድገ
ገት ፣ ፈጣን የባሕርና የዓየር ትራንስፖርት ዓለምን እያጠበቡት እን
ደሆነ እናውቃለን ። በትንሿ የአፍሪካ መንደር የሚሠራ ሥራ በደቂ
ቃዎች የዓለምን ሕዝብ ትኩረት የሚስብ ዜና ሆኖ መቅረብ የሚ
ችልበት ዘመን መምጣቱ ራሷ ዓለም ትንሽ መንደር እየሆነች መም
ጣቷን ያሳየናል ። ከዚህ በተጨማሪም ለምዕተ ዓመታት እርስ በርሳ
ቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሲናቆሩ ፣ ደም ሲያፋስሱና ሲያፈሱ የነበሩ
የአውሮፖ መንግሥታት መንግሥታዊ ልዑላዊነታቸውን የሰረዘ
የጋራ የአውሮፖ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኀበረሰብ ለመመሥረት
ታች ላይ እያሉ እንደሆነ እናውቃለን ። ይህ ግን አንድ ጉንዮሽ የዓ
ለም ገፅታ ነው ።

ሌላው ገፅታ በዓለም ላይ እየተጠናከረ የሚሄድ ብሔረተኝነት
ነው ። በአውሮፖ ማኀበረሰብ መንግሥታት ሃገሮች ውስጥ ሳይቀር
የብሔረተኝነት ጥያቄ የሞተ አይደለም ። በእንግሊዝ የአይሪሾች ፣
በእስፔን የባስኮች ብሔረተኝነት ዛሬም አልረገበም ። ከአውሮፖ
ውጭ ካናዳን ፣ ሕንድን ፣ የቀድሞ ሶቭየት ኅብረትን ፣ ዩጎዝላቪያን ፣
ቱርክን ፣ ኢራንን ፣ ኢራቅን ፣ ቻይናን ፣ በአፍሪቃም በርካታ አገሮች

በዙሪያችን እንኳን ሱማሊያን ሱዳንን ኬንያን ማየት ይቻላል ። ኢትዮጵያም ከእነዚሁ ውስጥ እንጂ ከእነዚህ ውጭ አይደለችም ። ለምን የሚለውን ጥያቄ በዚህ ፅሑፍ ከምንመልሳቸው ጥያቄዎች አንዱ ነው ።

በዚህ ፅሑፍ በኢትዮጵያ የብሔረተኝነት ስሜት እየተጠናከረ መምጣቱን ፡ ይህ ለምን እንደሆነ ፡ የብሔረተኝነት መጠናከር በአማራው ሕዝብ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖና የአማራው ሕዝብ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ምን ማድረግ እንደሚገባውም የሚመስለንን ጠቁመናል ።

ከዚህ በተጨማሪ ፅሑፋችን የተለያዩ ጉዳዮች የሚነካ ቢሆንም ዋንኛ ትኩረቱ በአማራው ሕዝብ የወደፊት ዕጣ ላይ ነው ። አማራው ከዚህ በፊት ስለብሔረኝነት ለምን እንዳላሰበ ፣ ባለንበት ወቅት በኢትዮጵያ የብሔረተኝነት ጥያቄ ሲነሣ አማራውን የሚገጥሙትን ሁለንተናዊ ችግሮች በመጠኑም ቢሆን ለመዳሰስ ሞክረናል ።

ዛሬ የሃገራችን ፖለቲካ ብሔር ብሄረሰቦችን መሠረት ያደረገ ፖለቲካ ነው።በዚህ የፖለቲካ መድረክ ጠንካራ የብሔረተኝነት ስሜት የሚሰማቸውና በዚህም መንገድ በከፍተኛ ደረጃ የተደራጁ የተለያዩ የብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ድርጅቶች ከብሔራዊ ጥቅማቸው በመነሳት የተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን መንደፍ የሚያስችል አቅም አላቸው ። ይህ አቅም ፡ ብሔረተኝነትን ነዳጁ አድርጎ በየጊዜው እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይሄድም ። እነዚህን የመሰሉ ጠንካራ ድርጅቶች ያሏቸው ሕዝቦችና በዚህ መንገድ ባለ መደራጀቱ እንደተበተነ ያለው የአማራ ሕዝብ በአንድነት እንጓዝ ቢሉ ፣ የጉዞው አላማ ሺህ ጊዜ ቀና ቢመስል ጉዞው ከጎታችነትና ከተጎታችነት ፣ ከፊት ቀዳሚነትና ከኋላ ተከታይነት ውጭ ነፃና ዕኩል ጉዞ መሆን አይችልም ። የዚህ ዓይነቱ ያልተመጣጠነ ግንኙነት ውጤቶች ምን እንደሚመስሉ በከተማና በገጠር ያለው አማራ ሁሉ ከወዲሁ መገመት የቻለ ይመስለናል ። ለአማራውም ሆነ ለሌሎች ሕዝቦች የሚጠቅም አይደለም ።

በመሆኑም ከእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ለመውጣት አማራው ምን ማድረግ እንደሚገባው በዚህ ፅሑፍ ለማሳየት ሞክረናል ። ምርጫው በአማራነቱ መሰባሰብ ብቻ ነው ። በአማራነት የሚደረገው መሰባሰብ ደግሞ እንደሌሎች ብሔረሰቦች መሰባሰብ ትርጉም እንዲኖረው ከተፈለገ ጠንካራ የብሔራዊ ማንነት ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ሊሆን



ይገባዋል ። የአማራ ብሔረተኝነት ያልነውም ይህንን የብሔራዊ ማንነት ግንዛቤ ነው ። የዚህን ብሔረተኝነት ያለፈ ታሪክና ወደፊትም በምን መልክ መገለፅ እንደሚገባው በፅሑፋችን አቅርበናል ።

በእኛ እምነት ታሪክ ከነባራዊ ሁኔታ ውጭ በምኞትና በዘፈቀደ አይሠራም ። የሚሠራ ቢሆን ኖሮ ነገሥታቱና አምባገነኖቹ ዛሬም በዙፋናቸው ላይ በተገኙ ነበር ። ባለንበት ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝቦች መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆመው ከዚህ ወዴት እንደሚሄዱ ግልፅ ባልሆነበት ሰዓት ፣ "ሥልጣን ላይ ያለውም" ሆነ የሌለውም የየግሉን የተሰፋ ጎዳናን ዕውነተኛው የወደፊቱ ጎዳና አድርጎ የሚያይ ከሆነ ፣ ዛሬም እንደትናንቱ ከታሪክ መማር አልቻልንም ማለት ነው ።

መጪውን የታሪክ ጉዞ ከምኞት ውጭ ለማየት ከፈለግን ዛሬ ያለንበትን ዕውነታ ከስሜትና ከጠባብ ፍላጎት ነፃ ሆነን በአግባቡ ማንበብ ይኖርብናል ። በሀገራችን ይህ ዕውነታ ብሔርና ብሔረሰብን መሠረቱ ያደረገ የሕዝቦች ፣ የድርጅቶች እንቅስቃሴዎች የሚታይበት ዕውነታ ነው ። ይህ ዕውነታ ያለፈን ታሪክ ፡ የአውሮፖ ማኅበረሰብን የአንድነት ጉዞ ፣ የዓለምን መጥበብ ፣ የመሳሰሉትን ጉዳዮች በማንሳት የማንሸፍነው ዕውነታ ነው ። በተለያዩ ምክንያቶች ይህንን ዕውነታ ለመቀበል ችግር የገጠመን ከማንም በላይ እኛን አማሮቹን ነው ። በዚህ ግን መቀጠል እንደማንችል ግልፅ እየሆነ የመጣ ይመስለናል። እንቀጥልም ከተባለ ይህ ድርጊታችን በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለይም በአማራው ሕዝብ ሕይወት ላይ የከፋ መዘዝ የሚያመጣ ይሆናል ።

የአማራው ሕዝብ ጠንካራ ብሔራዊ ማንነቱን አዳብሮ በዚህ ብሔረተኝነት ዙሪያ ተሰባስቦ ለታላላቅ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ክንዋኔዎች ራሱን በፍጥነት ማዘጋጀት ካልቻለ ፣ ይህ ሕዝብ በሚሊዮኖች በረሐብ የሚረግፍበት ፣ በሚሊዮኖች የሚሰደድበት ፣ እንደ ሕዝብ ክብሩ ነፃነቱና ሕልውናው ከማይጠበቅበት ሁኔታ ውስጥ እንደሚገባ መጠራጠር አይኖርብንም ።

በመጨረሻም የዚህ ፅሑፍ ዓላማ "አንድና አንድ" ብቻ ነው ። ዛሬ በሃገራችን ውስጥ ባለው ሁኔታ በተለይም የአማራውን ሕዝብ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በአማራውና በአማራው ውስጥ ብቻ መደረግ ላለበት ውይይት የራሳችንን መንደርደሪያ ሃሣቦች ለማቅረብ ነው ። የሚታዩንን ፣ የሚሰማንን ነፃ በሆነ መንፈስ ለማቅረብ ሞክረናል ።

ከጉዳዩ አሳሳቢነት የተነሳ በጥድፊያ የቀረበ ጽሑፍ በመሆኑ፣ ድክመቶች እንዳሉበት እናውቃለን። መነቀፍ የሚገባቸውን በመንቀፍ፣ መኰልበት የሚገባቸውን ሃሳቦች በማኰልበት፣ ከዚህም በተረፈ የየራሳችሁን ጽሑፎች በማቅረብ የተነሳንበትን ዓላማ የምታሳኩት እናንተው አማራዎች፣ አንባቢዎች ናችሁ። ከጽሑፍም ሌላ አማራውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት እንድንችል ቴሌቪዥን ሬዲዮንና ሌሎችን መድረኮች የሚቆጣጠሩ ባለሥልጣናት ድጋፍ እንዲያደርጉልን ሁላችንም በያለንበት መጠየቅ ይኖርብናል።

## ማሳሰቢያ

ይህችን ትንሽ ጽሁፍ ለምታነቡ አማሮች በሙሉ!

ይህን ጽሁፍ፣ በቆዩ ሃሳቦችና አመለካከቶች እሥር ቤት ሆነን ማንበቡ ጠቀሜታ የለውም። በተለይ በምዕራፍ አንድ የሚገኙትን መሠረታዊ ሃሳቦች ሳንመረምር አማራውን ወደ የሚመለከቱ ምዕራፎች መሸጋገር ፋይዳ አይኖረውም። ስለዚህም ይህ ምዕራፍ ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን በትዕግሥትና ነፃ በሆነ ስሜት እንድታነቡት በትህትና እንጠይቃለን።



## ምዕራፍ አንድ

# ብሔረተኝነት በኢትዮጵያ ፈጠራ ወይንስ እውነታ?

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ሃገር ወይንስ የአንድ ብሔር? ለዚህ ጥያቄ መልስ በመስጠት በየትኛውም ወገን ልዩነት ያለ አይመስለንም። ብሄረተኝነትን የሚቃወሙ፣ የሚያወግዙ ግለሰቦች ድርጅቶች ሳይቀሩ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ሃገር መሆኗን አይክዱም፤ ለሁላችንም መነሻችን እራሳቸውን የቻሉ ቋንቋ፣ ታሪክ ባህልና ወግ ወዘተ. ያሏቸው የተለያዩ ሕዝቦች የሚኖሩባት ሃገር መሆኗ ነው።

## የብዙ ብሔርና ብሔረሰብ ሃገር ከሆነች በኢትዮጵያ ምን ዓይነት ብሄረተኝነት ሊኖር ነው?

አንድ ወጥ ብሄረተኝነት አለ ብሎ ለመናገር ከብዙ ብሄር ብሔረሰቦች አገርነቷ እውነታ ጋር ይጋጫል። በመሆኑም እንደብሄር ብሄረሰቦች ብዛትና ዓይነት የተለያዩ ብሄረተኝነት ያቀፈች ሃገር ናት ማለት ነው። ኦሮሞ የሚባል ብሔር፣ ትግሬ የሚባል ብሔር፣ አፋር የሚባል ብሔር ወዘተ. በመኖሩ ከተስማማን የእነዚህ ብሄር ሕዝቦች የማንነት መግለጫ የኦሮሞ ብሄረተኝነት፣ የትግራይ ብሄረተኝነት፣ የአፋር ብሄረተኝነት ከመሆን ሊያመልጥ አይችልም። ሕዝቦች በባህል በቋንቋ በታሪክ ልዩ የሚያደርጓቸው መለዮች ጠፍተው በተለየ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ እስካልተተካ ድረስ የየብሄረሰቦቹ ብሄረተኝነት ከብሄራቸው ማንነት የሚቀዳ እንደሆነ ይቀጥላል። በመሆኑም የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች አገር መሆኗን የሚቀበል ግለሰብ፣ የተለያዩ ብሄሮችን ብሄረተኛነት መኖርን አልቀበልም ካለ ከራሱ ጋር ይጣላል። በኢትዮጵያ ውስጥ ከሰባ የሚበልጡ ብሄር ብሄረሰቦች መኖራቸውን ተቀብለው፣ ነገር ግን የብሄረተኝነትን ጥያቄ ሲመልሱ፣ በኢ

ትዮጵያ የሚገኘው ብሄረተኝነት አንድ ኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት ብቻ ነው የሚሉ አሉታጡም ። እንዲህ የሚሉ ሃይሎች ሊመልሱት የማይችሉት ጥያቄ አለ ። ብሄረተኝነቱ ኢትዮጵያዊ ከሆነ ምን ዓይነት ቋንቋ ፡ ባህል ፡ ታሪክ ፡ ወግ ወዘተ ፡ በአጭሩ ይዘቱ ምን ይሆናል የሚለውን ነው ። ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ፡ ኢትዮጵያዊ ባህል ፡ ወግ ብለው እንዳይሉ እንዲህ ዓይነት የሁሉም ሕዝቦች የሆነ አንድ ወጥ ቋንቋ ባህል ፡ ታሪክ ፡ ወግ በኢትዮጵያዊነቱ የሚታወቅ የለም ። አለ ከተባለም በቋንቋ ረገድ የሃገሪቱ ብሄራዊ ቋንቋ ሆኖ ሲሰራበት የቆየው የአማራኛ ቋንቋ ሊሆን ነው። በታሪክ ከመጣም ከአማራውና ከትግሬው የሰሜን ኢትዮጵያ የ3000 ዘመን ታሪክ ሳያልፍ ነው። በባህልም ከመጣን በአለባበስ ፡ በአመጋገብ ፡ በዘፈን እስከ አሁን በሃገር ባህልነቱ ሲቀርብ ከነበረው የሰሜን ኢትዮጵያ ባህል ሌላ ባናቀርብ ነው ። እነዚህ ደግሞ አንድ የተወሰነ የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝብ ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ ከመሆን አያልፉም ።

ይህ ደግሞ በዋነኛነት የአማራው ፡ በታሪክና በባህል መልኩ ሲባዛ ትግሬውን የሚጨምር ካልሆነ በስተቀር የጋምቤላው ፡ የኩናማው ፡ የወላይታው ፡ የአፋሩ ፡ የሱማሌው ፡ የኦሮሞው ፡ ቋንቋ ፡ ባህል ፡ ወግ ፡ ታሪክ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም ። ባለመቻሉም ነው ኢትዮጵያ አንድ ቋንቋ ፡ ባህል ታሪክ ያለው ሕዝብ የሚኖርባት የአንድ ብሔር ሃገር ሳትሆን የብዙ ብሄርና ብሄረሰቦች አገር ናት የሚለውን እውነታ ሁላችንም መካድ ያልቻልነው ። የብሄሮች መኖርና የብሄሮቹ ብሄረተኝነት ከዚህ የማይነጠል መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለዚህ ብሄረተኝነት ፡ ግለሰቦች ወይንም የፖለቲካ ቡድኖች እንደፈለጉት የሚፈጥሩት ነገር ሳይሆን በግልፅ የተለየ ቋንቋ ፡ ባህል ፡ ወግ ፡ ታሪክ ፡ ወዘተ. መለያ ያላቸው እራሳቸውን በእነዚህ መለዮዎች ልዩ አድርገው የሚያዩ ሕዝቦች ስለአሉ ብቻ የሚመጣ ነው ። ብሔረተኝነት ፈጠራ ሳይሆን በኢትዮጵያ እውነታ ነው ።

"በኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች አሉ ። በመኖራቸውም ብሄረተኝነት ሁሌ የሚኖር ነው ፡ ነገር ግን ብሄረተኝነት ጎልቶ እንዲወጣ ፣ የብሄረተኝነት ስሜት እንዲጠናከር የሚያደርጉት የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው "

ይህንንስ አባባል እንዴት እናየዋለን ?

ይህን አባባል በደንብ ለማየት ትንሽ ወደኋላ ተመልሰን ታሪክን መፈተሽ ሊያስፈልግ ነው ።



ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯ ዓለም ዓቀፍ እውቅና አግኝቶ አሁን በውስጧ የተካተቱ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰብ ሕዝቦች የያዘች ፡ በተማዕከለ መንግሥት የምትተዳደር ሃገር ከሆነች አንድ ምዕተ ዓመት አልፋል ። ሁላችንም እንደምናውቀው አሁን በሃገሪቷ የሚገኙ ሕዝቦች በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት አስተዳደር ሲገቡ ሕዝቦች ፈቃዳቸው እየተጠየቀ በቅርቡ የአውሮፖ የጋራ ማህበረሰብ ሃገር ሕዝቦች እንደሚያደርጉት ሬፍረንደም እየተካሄደ በጋራ በተስማሙባቸው ውሎች አማካይነት አልነበረም ። ሊሆንም አይችልም ነበር ። ለምን እንዲህ አልሆነም የሚሉ የሚኖሩ አይመስለንም። በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሃገርና መንግሥት ምሥረታ በቀጥታ የተፈጸመው በመሣሪያ ሃይል ፡ በቅጥቀጣ ፣ በእሳትና በብረት ነው ። ሃይለኛው ደካማውን አስገብሮ ነው ። ሃይል የነበራቸው በጊዜው ከፍተኛ ብዛት ያለው የጦር መሳሪያ በዚህ የታሪክ አጋጣሚ በእጃቸው ያስገቡት የሸዋ ነገስታትና መሳፍንት ነበሩ ። በሰሜን ጎጃምን ፡ ጎንደርን ፡ ወሎን ትግራይን በመሳሪያ ሃይላቸው ያስገበሩትና በደቡብም ተመሳሳይ በሆነ መንገድ በጣም ብዛት ያላቸውን የራሳቸው ታሪክ ፡ ባህል ፡ ቋንቋ ፡ የመሬት ስሪት አስተዳደር ወዘተ የነበራቸውን ሕዝቦች በግዛታቸውም ያጠቃለሉት "እነዚህ የሸዋ መሳፍንት ናቸው"። በዚህ የሸዋ መኳንንት የግዛት ማስፋፋትና ሕዝቦችን የማስገበር ዘመቻ ነበር ፡ የውጭ ሃይሎች የተለያዩ ብሄረሰቦች አባላት ድርሻ የየራሳቸው የታሪክ ዝርዝር የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ሳንረሳ በዋናው ቁም ነገር ላይ ስናተኩር የሃገሪቷ ምስረታ በአንድ ብሔር መሳፍንት በዋንኛነት ያውም በአንድ ክልል በሚገኝ የሸዋ አማራ መሳፍንት የሃይል እርምጃ የተከናወነ ነበር ማለት ይቻላል ። ?

ከዚህ በተጨማሪ የተካሄደው የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ በመሠረቱ በሰሜንም ይሁን በደቡብ ከነበሩ ሕዝቦች የእድገት ደረጃ ማለትም በኢኮኖሚ ፡ በቴክኖሎጂ ፡ በባህል ፡ በፖለቲካና ማህበራዊ አስተሳሰብ ምንም ዓይነት የላቀ ደረጃ ባልነበረው ሃይል የተካሄደ ነበር። በመሆኑም ነው ተመሳሳይ በሆነ የዘመቻና የማስገበር ስልት ግዛታቸውን እስፋፍተው በቁጥጥራቸው ስር ያስገቧቸውን ሕዝቦች አንድ አድርገው ሃገራቸውን የአንድ ብሄር ሃገር ለማድረግ እንደበቁት እንዳንድ የምዕራብ አውሮፖ አገሮች ዓይነት ታሪክ መስራት ያልተቻለው ። ዘመቻው ፊውዳላዊ ከሆነ የግዛት ማስፋፋት ፡ መሬት የመያዝ ፣ ሕዝቦችን የማስገበር ፍላጎት የመነጨ በመሆኑ፣ በሕብረተሰብ የእድገት ደረጃ ተመሳሳይነት የነበራቸው የሌሎች ሕዝቦች የአስተዳደር ፡

የአመራረት ፡ የአኗኗር ሁኔታን ወደ ላቀ ደረጃ ለመውሰድም ሆነ ለመቀየር አልተቻለም ። በአውሮፖ አገሮች እንደታየው በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሃገር ምስረታ የተትረፈረፈ ካፒታልና የኢንደስትሪ አብዮት የፈጠራቸው ከፍተኛ የማምረቻ መሣሪያዎች መተንፈሻ ፍለጋ ከተደረገ የመስፋፋት ፍላጎት የመጣ አይደለም ። ባለመሆኑም በምዕራብ አውሮፖ ሃገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ የተለያዩ ሕዝቦችን በካፒታሊስት አንድ ወጥ ስርዓተ ማህበር ውስጥ በመከተት በእንዱስትሪና በንግድ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ሃይል ፡ ተበታትነው የነበሩ ሕዝቦችን በዋንኛነት ወደ ኢኮኖሚያዊ ውህደት ማምጣት አልተቻለም ። ከኢኮኖሚያዊ ውሁድ ሀገርነት ጋር ተያይዞ የመጣ ተመሳሳይነት ያለው የሕዝቦች የሕይወት አመለካከት ባህል ክልላዊ ልዩነትን የሰበረ ተቀባይነት ያገኘ ቋንቋ አልተፈጠረም ።

አንዳንድ ግለሰቦች የጣሊያንንና የጀርመንን ብሔራዊ መንግሥታት አመሠራረት በምሳሌነት በማቅረብ የምኒልክ የደቡብንና የሰሜን ሕዝቦችን የማስገበር እርምጃ ፡ከጀርመኑ ቢስማርክና ከጣሊያኑ ጋሪባልዲ ጋር የሚያመሳስሉ ፡ ከዚህም በመነሳት ታሪክ ከሚያውቀው የብሔራዊ አገር አመሰራረት ውጭ የተለየ ነገር በሃገራችን አልተካሄደም ይላሉ ። በመሆኑም ለምን የሸዋ አማራ መሳፍንትን ስራ በተለየ መልክ እናነሳዋለን ፡ ይላሉ ። ለምንስ በተለየ መልክ እንደምናነሳው ከዚህ በታች እናየዋለን ።

ከላይ እንዳስቀመጥነው በኢትዮጵያ የተካሄደው የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ በባህሪው ከምዕራብ አውሮፖ ብሔራዊ መንግሥታት ምሥረታ የሚለዩትን ነገሮች አይተናል ። አውሮፖውያኑ በመሣሪያ ሃይል የተደገፈ የተማዕከለ መንግሥት ምሥረታ ቢያካሄዱም የተማዕከለውን መንግሥት ለመጠበቅና በጦር ሃይል የገበሩ ሕዝቦች ግዛቶችን ወደ ተጠቃለለ ውህድ ብሔራዊ መንግሥትነት ለመቀየር የተጠቀሙበት ዋንኛው ሃይል የኢኮኖሚ ትስስርና የኢኮኖሚ እድገት ነው ። ሕዝቦች በየክልላቸው የነበራቸውን ባህልና የሕይወት ርእዮት አንድ ወጥ ያደረገው አድማሳዊ የሆነ የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት ነው ። በቋንቋዎችም መካከል የነበረውን ልዩነት ያጠፋው የንግድ ፡ የኢንዱስትሪ የምርምር ፈጣን እድገትና ግፊት በዚህም መስክ ግንኙነቶችን አስላጭ በመሆን በሂደት የበላይነት እያገኘ የሄደ አንድ ቋንቋ ተጠናክሮ መውጣቱ ነው ።

በኢትዮጵያችን ግን የተማዕከለ ዘመናዊ ሃገር ምስረታ ፡ እንደ በርካታ በታሪክ የታዩ ሃገሮች በወታደራዊ ሃይል የተከናወነ ቢሆንም



የተማዕከለውን ሃገር እንደተማዕከለ ለማስቀጠል ፡ የተለያዩ ብሔረሰብ ሕዝቦች በኢኮኖሚያዊ ትስስርና በማይፋለስ መደጋገፍ ማለትም በንግድ ፡ በእንዱስትሪ ፡ በመገናኛ ዘዴዎች በባህልና በቋንቋ ውህደትና መቀላለፍ ወደ አንድ ብሔራዊ አገር የቀለጡበት ሁኔታ በመፍጠር አልነበረም። የነበረውም ኋላ ቀር ተስፋፊ የፊውዳል ሃይል ይህንን ለማድረግም የሚችለው አልነበረም ። በመሆኑም የግዛት መስፋፋቱ ስራ ከተከናወነ ከመቶ ዓመት በኋላም የተለያዩ የሃገሪቷ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦች የዛሬ መቶ ዓመት ከነበሩበት አኗኗራቸው ፡ አመለካከታቸው ፡ ባህላቸው ቋንቋቸው ፡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገታቸው ሳይቀየር እንደ ነበሩ እናገኛቸዋለን ። ኢትዮጵያ የብሔሮችና ብሔረሰቦች ሙዝየም ናት የሚለው አባባልም እነዚህን በነበሩበት እንደ ነበሩ የቆዩትን ሕዝቦች ታሪክ ለመግለጽ የተሰነዘረ ነው ። እዚህ ላይ የምንጠይቀው ጉዳይ ይኖረናል ። ኢትዮጵያ በውስጧ የሚገኙ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በፈጣን የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ትስስር ወደ አንድ ካል መጡ እንዴት ተደርጐ በአንድ ተሰባስበው እንዲቆዩ ማድረግ ተቻለ ? መልሱ ቀላል ነው ። የተማዕከለ መንግሥት ለማቋቋም ሕዝቦችን ለማስገበር የተወሰደው ወታደራዊ እርምጃና በጠመንጃ ላይ የተመሰረተውን አስተዳደር በመቀጠልና በማጠናከር ብቻ ነበር። ሕዝቦች የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት የማያዩበት በጠመንጃ ላይ የተመሰረተ የአፈና የፖለቲካ ሥርዓት በተንሰራፋበት ሁኔታ ደስተኛ ሆነው ኋላቀርነታቸውንና ባርነታቸውን ተቀብለው እንዲኖሩ ተፈጥሮአቸው አይፈቅድላቸውም ። በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች እንደ ብልጭ ፡ እንደ ድርግም ሲል የቆየው የተለያዩ ብሔረሰቦች ቁጣ ፡ በኋላም ሃገሪቷ በከፋ የጦርነት ማዕበል ውስጥ እንድትዘፈቅ ያደረጋት ጉዳይ ይሄው የብሄሮችና ብሄረሰቦች ምሬት ነው ።

በኢትዮጵያ ብሄርና ብሄረሰቦች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ብሄረተኛነት ጎልቶ እንዲወጣ የሚያደርገውም ይሄው እስካሁን ስናየው የቆየነው የሃገሪቷ ያለፈው መቶ ዓመት ማህበረዊ ፡ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እውነታ ነው ። ኢትዮጵያ በውስጧ የሚኖሩ የተለያዩ ሕዝቦች ወደ ተጠቃለለ ውህደት የሚሄዱበት አገር ከመሆን ይልቅ ሕዝቦች የጨቋኝና የተጨቋኝ ብሔሮች ግንኙነት የፈጠረው የባርነት ሰንሰለት ሁሉንም ተብትቦ የሚያማቅቅበት ሃገር መሆኗ ነው ። በታሪካችን ውስጥ ሁሉንም ብሄሮች በጋራ ስሜት የሚያስተሳስሩ ተናጠል ታሪካዊ ክስተቶች አልነበሩንም ማለት ባይቻልም ፡ ለምሳሌ የአድዋ ጦርነትና የአምስት ዓመት በፀረ ጣልያን ተጋድሎ ፡ በዋንኛነት የመቶ

ዓመት ታሪካችንን የሚገልጸው የተለያዩ ብሔረ ብሔረሰብ ሕዝቦች በእሳትና በብረት ተብረው ፡ በእሳትና በብረት ሲጠበሱ በመኖራቸው የሚሰማቸው ቁጭት ምሬት ፡ ሃዘንና ፀፀት ነው ። በኢትዮጵያ ብሔሮች አሉ ብሔረተኝነትም ይኖራል ። የብሔረተኝነት መፈጠር የራሱ መሠረት ስላለው ብቻ እንጂ በጉትጎታና በቅስቀሳ የመጣ አይደለም ። ብሔረተኝነትም የየብሔሩን ሕዝቦች የመብት ፡ የሰብዓዊ ክብር የነፃነት ፡ የእድገት ጥያቄዎችን በእልህ ፡ በቁጭት የሚያነሳ ከመሆኑ ውጭ ሌላ መግለጫ ሊኖረው አይችልም ። ለምን ያለፈውን እናነሳለን የሆነው ሆኗል ፡ ምኒልክንም አፄ ሃይለስላሴን ደርግን እያነሳን የሕዝቦችን ምሬት ማባባስ ምን ያደርጋል የሚሉ አሉ ። እንዲህ የሚሉት በግልጽ ሊያጤኑት የሚገባ ጉዳይ አለ ። የብሔሮች ጭቆና ያለፈ የዛሬ መቶ ዓመት የተዘጋ ታሪክ ቢሆን ኖሮማ እውነትም ጉዳዩን ማንሳት የሚቻልም ባልሆነ ነበር ። ሕዝቦችን ለማስገበር የተደረጉ ጦርነቶች በሕዝብ ላይ የተፈጸሙ ግፎች ፡ የደረሱ ስቃዮች ፡ በታሪክ መጽሐፍ ውስጥ የተዘከሩ ትውልድ ቢያነባቸው ስሜት የማይቀሰቅሱ ደረቅ የታሪክ ሀቆች ብቻ ሆነው በታዩ ነበር ። ጦርነትን በሰላም ፡ ኋላቀርነትን በእድገት ፡ የጠመንጃ አስተዳደርን በዲሞክራሲያዊ ፖለቲካዊ አስተዳደር መቀየር በቻሉ ሃገሮችማ ሕዝቦችን በአንድ ብሔራዊ መንግስት ለመክተት የተደረገው ሙከራ ተሳክቶ ፡ ሕዝቡ አንድ እንዲሆን በታሪክ ከተደረገበት ጦርነትና ከተፈጸመበት ግፍ ይልቅ አሁን በሚኖርበት ሃገር ያገኛቸውን ኢኮኖሚያዊ ፡ ማህበራዊ ፡ ፖለቲካዊ ጥቅሞቹን በማስላሰል በብሔራዊ ዜግነቱ እየኮራ ይኖራል ። የኛ እንደዚህ መሆን አለመቻል የእድገት ደረጃችን ፡ የነባራዊ ታሪክ አስገዳጅነት ያመጣው እጣችን ነው ። ይህንን እጣ ፊት ለፊት ከነመዘዙ መጋፈጥ እንጂ እንደ ሌለ በማስመሰል ፡ በመሸሽ የትም አይደረስም ። በኢትዮጵያ ብሔረተኝነት የማንም ፈጠራ አይደለም ። ግለቱ ያልበረደውን ቢሞቅ እፍራሽም ሚና ሊጫወት የሚችል ሕያው የሕዝቦች ስሜት ነው ።



## ምዕራፍ ሁለት

# ኢትዮጵያዊነት የሁሉም ብሔር ሕዝቦች የጋራ የዜግነት መግለጫ ወይንስ ብሔሮችን የተካ ራሱን የቻለ ብሔረተኛነት

ባለንበት ወቅት ብሔርህ /ብሔርሽ/ ምንድነው የሚል ጥያቄ እየተለመደ መጥቷል ። ይህ ጥያቄ ከዚህ በፊት የነበረ ቢሆንም አሁን እንዳለንበት ዘመን ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊና ሕልውናዊ ትርጉም ኖሮት ተጠይቆ አያውቅም ነበር ። በመሆኑም በተጠያቂዎች ዓይን የነበረው ትርጉም እንደዛሬው ከብዶ ታይቶ አይታወቅም ።

አንዳንዶቻችን ብሔራችሁ ተብለን ስንጠየቅ ያለምንም ማመንታት አማራ ፣ ኦሮሞ ፣ አፋር ፡ ትግሬ ወዘተ . ብለን ያለምንም ጭንቀት እንመልሳለን ።

አንዳንዶቻችን ተመሳሳይ ጥያቄ ሲቀርብልን ለምን ብሔር የሚባል ነገር ይነሳል ? ለምን ይህ ጥያቄ ያስፈልጋል ብለን የምንቆጣ አለን ። ለምን እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ተጠየቅን በማለት ተናደን የሄድንበትን ጉዳይ ሳናሳካ የምንመለስም አለን ። ብሔር ፡ ስንባል ኢትዮጵያዊ ብለን የምንመልስ ሞልተናል ። ባለፈው ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማና በተለያዩ ከተሞች የክልል ምርጫ በተደረገበት ወቅት ለመራጭነት ለመመዝገብ የሄድን ግለሰቦች ብሔራችንን ስንጠየቅ ከላይ የሰፈሩትን መልሶች መልሰናል ። በአንዳንድ መመዝገቢያ ጣቢያዎች ብሄሩን ሲጠየቅ አማራ ፣ ኦሮሞ ወዘተ . ያለውንና ኢትዮጵያዊ ያለውንም ለመራጭነት መዝግበዋል ። በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ብሔራቸውን ሲጠየቁ ኢትዮጵያዊ ያሉትን ፡ ኢትዮጵያዊ ብሔር አይደለም ፡ ብሔርህን ካልተናገርክ ለምርጫ አትመዘገብም ተብለን ተባረናል የሚሉ አሉ ። እዚህ ላይ ጉዳዩ ምርጫው አይደለም ። ጉዳዩ ስለብሄራችን ስንጠየቅ ለምን የተለያየ መልስ እንሰጣለን ነው ። ?

ብሄር ፡ ሲባል ከቀጥታ ትርጉሙም ከስሜቱም ተነስተን በምዕራፍ 1 ከቀረበው ሃተታ ጋር አገናዝበን ስናየው ኦሮሞ ፡ ትግሬ ፡ አፋር

ቢል ትክክልም ተገቢም ይመስላል ። አማራ የሚልም መገኘቱ የሚያስገርም አይሆንም ። የስሜቱ ጉዳይ ቢያጠያይቅም አማራ የሚለው ቃል በአንድ ሕዝብ መገለጫነቱ የነበረ ፡ ያለም በመሆኑ ። ግር የሚያሰኘው ብሔሩን ሲጠየቅ ኢትዮጵያዊ የሚለው ወይም ለምን ተጠየቅሁኝ ብሎ የሚቆጣው ነው ።

ብሔሬ ኢትዮጵያዊ ነው የሚለው ፡ ብሔሩን ሲጠየቅ ኦሮሞ ፡ ትግሬ ፡ አማራ ፡ ወዘተ ። ነው ብሎ የሚመልሰውን ሌላውን ኢትዮጵያዊ እንዴት ሊያየው ነው ? ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ሃገር መሆኗን መካድ የማይቻል እውነታ ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያዊነትን ለምን የብሔር መገለጫ አድርገን ለመውሰድ እንሞክራለን ? በኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦች ፡ በእነዚህም ሕልውናቸው ገሃድ በሆኑ ብሔረሰቦች ዙሪያ የነበረና ያለ ብሔረተኝነት ዋነኛው የኢትዮጵያ ሕዝቦች መገለጫ ሆኖ ሳለ ብሄርህ ወይም ብሔርሽ ምንድነው ስንባል የምንቆጣው፤ ለምን እንጠየቃለን የምንለው ለምንድነው ? ችግሩ ከጠያቂው ነው ወይንስ ለምን እጠየቃለሁ ከሚለው ። በእኛ እምነት ችግሩ ከጠያቂው አይደለም ። ጠያቂው እውነታን መሰረት አድርጎ የአብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ተጨባጭ ስሜት ተንተርሶ ነው የሚጠይቀው። ችግሩ ከተጠያቂው ላይ ይመስለናል ፡ የተጠያቂዎቹ ሁሉ ችግር ግን አንድ አይደለም ።

1. ከስነልቦና ጭንቀት የሚመነጭ ችግር ፡

እየተጠናከረ የመጣው የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔረተኝነት ፡ ሕዝቦች በተለያዩ ብሔራዊ ድርጅቶች መሰባሰብ ቋንቋንና ባህልን መሠረት ያደረገ ብሔራዊ መስተዳድሮች መመስረት ከፍተኛ ስነልቦና ጭንቀት ያስከተለባቸው በርካታ ግለሰቦች መኖራቸው ግልፅ እየሆነ መጥቷል ። ብሔር ፡ ብሔረሰብ የሚባል ነገር አታንሱብኝ ፡ እንዲህ እያላችሁ ሕዝቡን እየከፋፈላችሁ ነው ፡ ለምን "እንደሚማዳችን" ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን•እያልን አንኖርም በማለት በስሜትና በምሬት የሚናገሩ ሞልተዋል ። የዚህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ግለሰቦች ከሌሎች የሚለዩቸው ፡ ብሔራቸውን ሲጠየቁ በቀላሉ ለመመለስ የሚያስችል አንድ ወጥ ብሔራዊ ማንነት የማይሰማቸው መሆኑ ነው። በዚህ ችግር ውስጥ የሚገቡ ቢጋብቻ ከተለያዩ ብሔሮች የተወለዱ ወይንም ቢጋብቻ ከተለያዩ ብሔሮች የተሳሰሩና ቤተሰብ የመሠረቱ ናቸው ። ይህን ችግር በሚገባ ማጤንና በዚህ ችግር የተነሳ ጭንቀት



ውስጥ ለገቡት ወገኖቻችን መፍትሄ የመስጠት ወገናዊ ግዴታ አለብን። ይህን ችግር መፍታትም በሕዝቦች መሃከል ሊኖር ለሚገባው ጤነኛ ግንኙነት የራሱ አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

## የችግሩ ስፋት

የዚህ ችግር ስፋት በውል የተጠና ባይሆንም አንድ ነገር ማለት ይቻላል ። ባለፉት መቶ ዓመታት ከአንዱ ክልል ወደሌላው ክልል በወታደርነት ፣ በመንግሥት ሠራተኝነት ፣ በነጋዴነት በመንቀሳቀስ ሲሰራ የነበረው የሰው ሃይል ቁጥሩ ብዙ ነው ። ከዚህ በመነሳት ለሥራ በተለያዩ ምክንያቶች በሄደባቸው ቦታዎች ቤትና ትዳር መስርቶ ከብሄሩ ውጭ ተጋብቶ ፣ ወልዶ ይኖራል ፤ አብዛኛው የዚህ ዓይነት አኗኗር ውስጥ የገባው ሕዝብ የሚኖረው በከተሞች ነው ። አንዳንድ የተለያዩ ብሄሮች በአዋሳኝነት በሚገኙባቸው ወይንም እንደ ደቡብ ኢትዮጵያ በነፍጠኝነት የዘመተው ወታደር በሰፈረባቸው አካባቢዎች እንዲህ ዓይነቱ የብሄርና ብሄረሰብ መቀላቀል በአርሶ አደሩም መሃከል ይታያል ። ይህ መጋባትና መዋለድ አልፎ አልፎ በአርሶ አደሮች መሃከል ያለ ቢሆንም ከመጀመሪያው ጀምሮ በነገሥታቱና በመሣፍንቱ በኋላም በአንድ ማዕከል በመማርና በመሥራት በተገናኙ የተለያዩ ብሄሮች ምሁራን መሃከል ጐልቶና ሰፍቶ ይታያል ። በተለይ የተለያዩ ብሄርና ብሄረሰቦችን አስገብረው የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ናመሰረቱት የሸዋ ነገሥታትና መሳፍንት የግዛታቸውን አንድነት ለማስጠበቅ ከተጠቀሙበት ስልቶች አንዱ ልጆቻቸውን ለተለያዩ ብሄሮች መሳፍንትና ባላባት ልጆች መዳር ነበር ። ይህ አሠራር በመሃከለኛው ዘመንም በአውሮፓ ነገሥታት የተፈጸመ ፣ ከቅድመ ምኒሊክ በፊትም በሰሜን ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የተለመደ አሠራር ነበር ።

ለምሳሌ፦

አፄ ሃይለሥላሴን ብቻ እንኳን ብንወስድ ፡ ልጆቻቸውንና የልጅ ልጆቻቸውን ከአምስት ላላነሱ የተለያዩ ብሔር መሳፍንትና ባላባት ልጆች ድረዋል ። እንግዲህ ከመሳፍንቱም ከመኳንንቱም ፡ ከምሁሩም ፣ ከነጋዴውም ፡ ከአርሶ አደሩም በዚህ ዓይነት የጋብቻ ትስስር የገቡ እንዳሉ ግልፅ ነው ።

ይህም ሆኖ ግን የችግሩን ስፋት ለማየት ምን ያህሉ ሕዝብ ነው በዚህ ዓይነት ብሄር-ዘለል የጋብቻ ትስስር ውስጥ የገባው ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል ። ተዋልደናል ፡ ተጋብተናል አጥብ ፋፍሉን የሚሉት ክፍሎች እውነት እንደሚሉት በኢትዮጵያ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦች በጋብቻ ተቀላቅለው በምዕራፍ 1 ለማስቀመጥ የሞከርነው በኢትዮጵያ ራሳቸውን የቻሉ ብሔሮችና ሕዝቦችን ማግኘት መለየት እንደማይቻል አድርገዋል ወይ ? የተጋቡ የተዋለዱ ሰዎች እንዳሉ ብናስቀምጥም በኢትዮጵያ የሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ እነዚህ ተዋልደናል ፣ ተጋብተናል የሚሉት ግለሰቦች እንደሚሉት ፡ ጋብቻና መዋለድ ሙሉ ሃገሪቱን የቀላለፈ ጉዳይ አይደለም ። በአዲስ አበባና በአንዳንድ የደቡብ ከተሞች ፣ በመሃናንቱና በባላባቱ በተለያዩ ብሄሮች ምሁራን መሃከል የሚታየውን ጋብቻ ብቻ ወስደን የሃገሪቱ ሁኔታ ዋናኛ መገለጫ ማድረግ ስህተት ነው ። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እርሶ አደሩ በሚኖርባቸው ገጠሮች ይህ ዓይነት ጋብቻ የለም ማለት ይቻላል ። ማነው ከአፋሩ ፡ ከሱማሌው ፡ ከኦሮሞው ከሺናሻው ፡ ከአኝዋኩ ከአማራው ፡ ከትግሬዶ ፡ ወዘተ እርሶ አደር ጋር የተጋባና የተዋለደ ። በተለይ በሃገራችን ከአንድ ክልል ወደሌላ ክልል የሚንቀሳቀሰው የሕብረተሰብ ክፍል በአብዛኛው ሥራው በከተማ ያተኮረ እንደነበረ ስንረዳ ፡ ከከተማ ወጥቶ በገጠሮች በመዋለድና በመጋባት ብሄርና ብሄረሰቦችን ቀላቅሉ የብሄሮችን መኖር ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል ማለት ትልቅ ስህተት ይሆናል ። ዛሬም በአማራው ምድር ከየትኛውም ብሄር ያልተቀላቀሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አማሮች አንዳሉ ፡ በተመሳሳይ በትግሬይ ፡ በኦሮሚያ ፡ በአፋር ፡ በሶማሊያ ፣ በወላይታ ፡ በከምባታና ሃድያ የምናገኘው ይህንኑ ሃቅ ነው ። ይህ በመሆኑ ነው ሕዝቦች በስፋትና በቀላሉ ለብሄራዊ አደረጃጀት ፡ ለብሄራዊ ጥቅምና መብት ማስከበር የሚነሳሱት ። እንደሚባለውማ ሕዝቡ ተዋልዶና ተጋብቶ ያለቀለት ጉዳይ ቢሆን ማንም ቢቀሰቅሰው የብሄር አክራሪነት ጥያቄን እንዲያነሳ ሊያደርገው ባልቻለ ነበር ።

ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ማህበራዊ ሕይወት ገጽታ ሲታይ ተዋልዶ ተጋብቶ የሚኖረው ሕዝብ በጣም ጥቂት መሆኑ ግልጽ የሆነ ይመስለናል ። ስፋት የለውም ማለት ግን ችግሩ አሳሳቢ አይደለም ማለት መሆን የለበትም ። በተለይ ከየትኛውም በኢትዮጵያ ከሚገኙ የተለያዩ ሕዝቦች በብዛት ከተለያዩ ብሄሮች ጋር የተጋባው በአንጻሩም በሰፊው የሃገሪቱ ክልሎች ተበትኖ የሚኖረው አማራው መሆ



ኑን ስንገነዘብ ፡ በቁጥርም ቀላል ያልሆነ የአማራ ምሁር በመወለድም ይሁን በጋብቻ ከበርካታ ብሄሮች ጋር መተሳሰሩን ስንረዳ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠትን እንገብጋቢ ያደርገዋል ።

እዚህ ላይ ከ1966 ዓ.ምአብዮት በፊት በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርስቲ አስተማሪ የነበሩ አንድ እንግሊዛዊ ፕሮፌሰር የተናገሩት ነገር ትውስ ይለናል። “አንዳንድ የኢትዮጵያ ምሁራን ብሄረሰቦችን ያቋረጠ ጋብቻ በመፈጸማቸው የሀገሪቱ ሕዝብ ሁሉ እንደእነሱ ተዋልዶ ተጋብቶ ያለቀለት ይመስላቸዋል ። ከዚህም ተነስተው በሃገሪቱ የብሄሮችንና የብሄራዊ ጭቆና መኖርን የማያስታውስ ሕሊና ፈጥረዋል ። እውነቱ ግን ወደፊት በኢትዮጵያ የብሔሮች ጥያቄ ቁልፍ ጥያቄ ሆኖ መምጣቱ የማይቀር መሆኑ ነው ። የብሄሮች ጥያቄ የተቀበረ ፈንጂ ነው ። ይህን ፈንጂ የሚያፈነዳው ሃይል ሲመጣ እነዚህ ምሁራን ችግር ውስጥ መውደቃቸው አይቀርም።” ብለው ነበር ። ችግር ላይ መውደቃቸው እንደተባለው አልቀረም ። ከሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታና ይዞ ከወለደው የብሄረሰቦች ፖለቲካ ጋር ሕሊናቸውን ማስተካከል አልቻሉም ። ከእውነታው ጋር ፊት ለፊት ተያይቶ ምን ማድረግ ይሻላል ከማለት ፋንታ ብሄሮች ብን ብለው ቢጠፉላቸው ይመኛሉ ። በሃገራችን ተጨባጭ የፖለቲካ እውነታ ፋይዳ የሌላቸውን በይዘት የአንድ ወይ የሁለት ብሄር አባላትን ያሰባሰቡ ፡ በስምና በቅርጽ ግን ሕብረ-ብሄራዊ የሆኑ ድርጅቶች ፈጥረው በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የመንግሥት ተቃዋሚ ሆነው ይንቀሳቀሳሉ ። አብዛኛዎቹ ከዳር ቆመው ያያሉ ። በእኛ እይታ የዚህ ዓይነቱ ችግር ጉልቶ የሚታየው በአማራው ምሁራን አካባቢ ነው ። ከዚህም የተነሳ ከሌሎች ብሄረሰቦች ሕዝቦች መሰባሰብ ፤ ተደራጅተው በክልላቸውም ይሁን በሃገር አቀፍ ጉዳዮች ላይ ስራ ተጽእኖ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጋር ሲነጻጸር የአማራው ሕዝብ ያለአሰባሰቢ መቅረቱ የዚህ ችግር መገለጫ ነው ብለን ስለ ምንስጋ ጉዳዩን የተለየ ትኩረት ልንሰጠው ተገደናል ።

## 1.1 ከሁለት ብሄር መወለድ

ይህንን ጉዳይ ለመፈተሽ በቀጥታ አንድ ምሳሌ እንውሰድ ።

አንድ ግለሰብ ከአማራ አባት እናት በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ብሔረሰቦች ከአንዱ በእናቱ በአባቱ ይወለዳል ። ባለንበት ወቅት የብሄሮች ጥያቄ ሲነሳ ፡ በአካባቢው የሚኖሩ የተለያዩ ብሄረሰብ አባላት በየብሔራቸው ድርጅቶች ሲሰባሰቡ ይህ ግለሰብ ወደየት

እንደሚሄድ ግራ ይገባዋል ። ወደ አማራው ድርጅት እንዳይሄድ ወይንም ብሄሩን ሲጠየቅ አማራ እንዳይል ግማሽ አሮሞ ትግራይነቱ /ጉራጌነቱ/ እንዴት የሚል ጥያቄ ያቀርብበታል ። በዚህ ውሳኔ አንድ ብቻውን አይደለም ። የቤተሰብና የዘመድ ክሮች ባሉበት ሕብረተሰብ ውስጥ እንደመኖራችን በእናቱ ወይንም በአባቱ ወገን ያሉት አጐት አክስት ፣ አያት በሙሉ በዚህ ውሳኔ የሚነኩ ይሆናሉ ። ከሁለቱ አንዱን መምረጥ አንዱን መካድ ሆኖ ይታየዋል ። ምርጫው ማንነቱን ለሁለት የሚሰነጥቅ ግማሽ ሰው የሚያደርገው ይመስለዋል ። በተለይ ምርጫው ሁለት በእኩልነት በተቀመጡ ብሄረሰቦች መሃከል አለመሆኑን ሲያውቅ ጉዳዩ ይወሳሰብበታል። አንዱ የበላይ ሌላው ደግሞ የበታች ሆነው ሲታዩ ከመጡ ብሄሮች መወለዱ አማራነቱን መምረጥ ማለት በሌላ ጐኑ ባለው ብሄር ሲደርስበት ለነበረው የበታችነት ተጽእኖ መገበር ሆኖ ይታየዋል ። እንዲህ ዓይነት ጭንቀት ውስጥ የሚገባ ግለሰብ ከጭንቀቱ መውጫ አድርጐ የሚከተለው መንገድ ሁሉንም ትቶ ኢትዮጵያዊ ነኝ ወይንም አልፎ ተርፎ ምንም አይደለሁም ወደሚለው የሕልውና ክህደት መሄድ ነው ። በኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች የሚባል ነገር ፈጠራ ነው ብሎም ይከራከራል ። አንድ ሃገር አንድ ሕዝብ የሚለው ፈጠራ ምንጩ ይሄ ሳይሆን ይቀራል ?

በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ግራት ምርጫ ቢያደርግም የምርጫውን ምንነት በሚገባ ካልተረዳ በጣም አጥፊ ወደሆኑ ተግባራት ሊሰማራ ይችላል ።

ሙሉ እምነት ኖሮት ባልገባበት ብሄራዊ ድርጅት ውስጥ በእምነት አለመሥራት ፣ ለእነዚህ ብሄር ሕዝቦች ጥቅም አለመቆርቆር፣ ለመብታቸው አለመከራከርን ፣ ለእድገታቸው ለነፃነታቸው አለማሰብን ፣ ሊያመጣ ይችላል ። ከእነዚህ ብሄር ሕዝቦች ጋር በጠንካራ ብሄራዊ ማንነቱ ያልተሳሰረ በመሆኑ የራሱን ፍላጐት ከሕዝቦች ፍላጐት በላይ የሚያስቀምጥ፣ የሕዝብ መብት አፋኝ፣ የሕዝብ ሃብት ዘራፊ፣ የጎንን ግለኝነት ያወረው ይሆናል ። በራስ መተማመን የማይኖረው ግለሰብ በመሆኑ በብሄሩ አባላት መሃከል የሚታዩ ስህተቶችን ለማረም የማይችል ፣በአድርባይነት የተዋጠ ይሆናል ። ከሌሎች ብሔር ድርጅቶችና ሕዝቦች ጋር በሚኖሩ ግንኙነቶች ላይም ፍትሃዊ ያልሆኑና በመርህ ላይ ያልተመሠረቱ ፣ ከግል ክብርና ጥቅም ከሚመነጩ መደራደሮች ውስጥ ይገባል ፤ እዚስ የተላበሰው ብሄረተኝነት ከቆዳ በታች የሚዘልቅ ባለመሆኑ የብሄሩን ሕዝቦች ሕልም ማለም ፣ ሕመም መታመም ፣ ጭንቀታቸ



ውን መጨነቅ ፣ ተስፋቸውን መጋራት ራእያቸውን ማየት የሚሳነው ይሆናል ። እንደበት ሆኖ ሊናገርላቸው ዓይን ሆኖ ሊያይላቸው እድሉና አጋጣሚ ቢፈቅድለትም በሚገባ ሊመራቸው አይችልም ።

በሌላ መልኩም ወደ ሌላ ጽንፍ ሊሄድ ይችላል ። ከአማራው በላይ አማራ ፣ ከኦሮሞ በላይ ኦሮሞ ፣ ከትግሬው በላይ ትግሬ በመሆን ሕዝቦች በመሃከላቸው በተፈጥሮአቸው የሚኖራቸውን ቀና መተሳሰብ የሚያደፈርስ ፤ ከውይይት ይልቅ ግጭትን ፣ ከማላላት ይልቅ ማክረርን በመከተል ጤናማ የሕዝቦችን መቀራረብና መፈቃቀርን ያጠፋል ።

ከዚህም አልፎ ብሄሬ ነው ብሎ በተቀላቀለው ብሄር ውስጥ ከፍተኛ ጥላቻና ቂም በቀል ያዘለ አደገኛ ሚና ሊጫወት ይችላል ። ከሁለት ብሄሮች ተወልዶ በደንብ ባል ተጠናና ባልተመረመረ ፤ በቂ ምክንያት በሌለው መነሻ የአንዱን ብሄር አባልነት የተቀበለ ግለሰብ ፣ በውስጡ በሚሸምቀው የታመቀ ስሜት የተነሳ በረባ ባልረባው ያለበትን ብሄር ማውገዝ መለያ ባሕርዩ ይሆናል ።

ይህን ሁሉ ያልነው ያለምክንያት አይደለም ። ከላይ በጠቀስናቸው ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች የተነሳ ፤

አማራነቱን ጠላሁ የሚሉ ግለሰቦች ቁጥራቸው መበርከቱ ፤

የአማራውንና የራሳቸውን ችግር በደንብ ሳይረዱ በረባው ባልረባው የአማራውን ሕዝብ ከሌላው የሚያጋጩ ፣

በአማራው የሚሰጡ አስተያየቶች ፣ የሚቀርቡ ሃሳቦችን በደንብ ሳያጤኑ ሁሉንም ነገር ትምክህት ፣ ትምክህት በማለት ሲፈርጁ የሚውሉ ፣ አማሬ ነን ባዮች መኖራቸው

ራሳቸው ከዚህ ችግር የተላቀቁ ባለመሆናቸው በዚህ ፈታኝ የታሪክ ወቅት የአማራው ሕዝብ የሚያስፈልገውን የበሰለ ፣ የረጋና የሰከነ አመራር መስጠት ያልቻሉ የተለያዩ አማራን እንወክላለን የሚሉ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው መኖራቸው ፣

ይህ ችግር በሚገባ መፍትሄ አግኝቶ ከጭንቀታቸው የተላቀቁ በርካታ ምሁራንን ከተፋይዳ ቢስ ሕብረ-ብሄራዊ ድርጅቶች በማውጣት አየር ላይ ከተንሳፈፈ ኢትዮጵያዊ ብሄረኝነት ፣ ምርጫቸው ከሆነ ፣ ወደ አማራነታቸው በመመለስ ለራሳቸውና ለዚህ መከረኛ ሕዝብ ጥቅም በእውቀታቸው የየግል ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ማድረግ ስለሚገባ ፣

በአጠቃላይ በራሳችን እየተማመንን አላስፈላጊ ከሆነ ተጋፊነት ወይንም አስከፊ ከሆነ አድርባይነት በመውጣት እንደ ሕዝብ በሕዝቦች መሃከል በነፃነት ፣ በሰላምና በብልፅግና ለመኖር ወሳኝ በመሆኑ ነው ።

## 1.2 ከአንድ ብሄር ውጭ መጋባት

ከአንድ ብሄር ውጭ መጋባትና ቤተሰብ መመስረት ከላይ እንዳየነው ዓይነት አስከፊ የሆነ ችግር በግለሰቦች ላይ ባይፈጥርም ግለሰቡ እንደቤተሰብ ሲያስብ ግን ችግር የሚገጥመው ይሆናል ። እኔ አማራ ነኝ ፤ ሚስቴ ኦሮሞ(ትግሬ) ናት ልጆች አሉን ምን እንሁን የሚል ጥያቄ ያቀረቡም አሉ ። እነዚህም እንደላይኞቹ ከችግራቸው ለመላቀቅ መፍትሄ ብለው የያዙት የብሄር ጉዳይ አይነሳብን ማለት ነው ። አይነሳብን ስላሉ ግን ችግሩ ሊጠፋ እንደማይችል አይተናል ። በእንዲህ ዓይነቱ ጭንቀት ውስጥ ለገቡ ሰዎች ተገቢ መፍትሄ እስካልተሰጠ ድረስ በራሳቸው ሆነ በቤተሰባቸው አልፎ ተርፎም በሕብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ይኖራል ። በዚህ ችግር ውስጥ የገቡ ሰዎች ለችግራቸው ተገቢውን ምላሽ ሳይዙ በአንድ ወይንም በሌላምክንያት በአንድ ብሄራዊ ድርጅት ውስጥ ቢገቡ ከላይ የዘረዘርናቸውን ዓይነት የተሳሳተ ተግባራትና ባህሪያት ከማዳበር የሚመለሱ አይሆኑም ። እዚህ ላይ ችግሩን ካነሳን ይበቃል ለመፍትሄው በሌላ ቦታ እንመለስበታለን።

## 2. ከጠንካራ ብሔራዊ ማንነት አለመኖር የሚመጣ ችግር

ይህ ችግር በግልጽ በእኛ በአማሮቹ ውስጥ ያለ ችግር ነው ። ችግሩ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል ።

ሀ. አማራውና በኢትዮጵያ የብሄር ብሔረሰቦች ታሪክ

ለ. ከዘመናዊት(ሞደርን) ኢትዮጵያ ምስረታ ታሪክ አኳያ

ሀ. አማራውና በኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች ታሪክ አኳያ

በኢትዮጵያ ስለብሔራዊ ጭቆና ስናወራ ጭቆናው ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ስነልቦናዊ ነው ። ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጭቆናን ብቻ ስንወስድ ፣ የአማራው



ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ የሆነ አስተዳደር ኖሮት አያውቅም ። በሃብቱ ፣ በጉልበቱ አዘበት አያውቅም ። በተከታታይ በሚደርስበት የአስተዳደር በደል አፈናና ዘረፋ ተማሮ በተነሳ ቁጥር የነበሩት መንግሥታት ከሌሎች ሕዝቦች የተለየ አላደረጉለትም ። አጼ ኃይለሥላሴ ለጉጃም አማራ ችግር ዳቦ ከሰማይ በአውሮፕላን አልጣሉለትም ። የወረደው ቦንብ ነው። በደርግ ጊዜም ለጉጃም የብቸና ሕዝብ ተቃውሞ ምላሹ የብቸናን ሕዝብ ከምድረ ገጽ ማጥፋት ነው ። ከመርሳ ፣ ከሃውዜን የበለጠ ሕዝብ በብቸና መጨፍጨፉን እናውቃለን ። ለጉንደር ፣ ለወሎ ፣ ለሰሜን ሸዋ ሕዝብ ደርግ ከሰማይ ዝናብ አላወረደም ። በናፓልም እሳት አቃጠላቸው እንጂ ። በኢኮኖሚ መስኩም ቢሆን የአማራው ሕዝብ በድህነቱ በኋላቀርነቱ እጅግ ዘግናኝ አዘቅት ውስጥ ይገኛል ። እንዲያውም በአንዳንድ የአማራው ክልል ያለው አሰቃቂ ድህነት ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነፃፀር የከፋ የሚሆንባቸውም አሉ ። ይህ የድህነት የኋላቀርነት እጣ በረሃብና በበሽታ መጠበስ አማራውን ጨምሮ የሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕይወት ይገልፃል ። ነገር ግን አማራውን ከሌሎች ሕዝቦች የሚለየው ጉዳይ አለ ። በባህል በቋንቋ ፣ በስነልቦና ሌሎች ሕዝቦች ፣ የደረሰባቸውን አበሳና ጭቆና አልደረሰበትም ። እንደ ኢጋጣሚ የአገሪቷን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፣ የባህል ሕይወት በኦምባገነንነት ሲቆጣጠር ከኖረው የአማራ ገዢ መደብ ጋር አንድ ዓይነት ቋንቋና ባህል በመጋራታችን የሌላ ብሄር ቋንቋ እንድንቀበል ፣ የሌላ ብሄር ባህል እንድንላበስ የተገደድን አልሆንም ። የተለያዩ ብሄር አባላት ቋንቋቸው ሲንቋሸሽ ፣ ባህላቸው ሲዋረድ ፣ የግለሰቦች ስም እንኳን ሳይቀር ማፌሪያ ሆኖ ስማቸውን ሲቀይሩ እኛ እንዲህ ዓይነቱ የባህልና የስነልቦና ጭቆና ውስጥ አልወደቅንም ። በመሆኑም በቋንቋ ፣ በባህል ፣ በታሪክ መንቋሸሽ የሚመጣ ውርደትን ፣ ይህ ውርደት የሚፈጥረውን የቋንቋ ፣ የባህል ፣ የታሪክ ማስከበር ብሄራዊ ቁጭት ፣ በዚህ የጭቆና መንገድ እንደተጓዙት ብሄር ብሔረሰብ ሕዝቦች የሚሰማን አይሆንም ። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጭቆናና የኢኮኖሚ ብዝበዛ በቀጥታ ከቋንቋ ፣ ከባህልና ከስነልቦና ጭቆና ጋር የተያያዘ በመሆኑ በተጨቆኑ ብሄሮች ሕይወት ውስጥ አንዱን ከአንዱ ለይቶ ማየት አይቻልም ። በመሆኑም ነው ብሄራዊ ጭቆናን መቃ

ውም ስለብሄራዊ ማንነት መቆርቆር ፡ ብሄራዊ በሆነ መንገድ የፖለቲካ ተቃውሞን መግለፅ በተጨቆኑ ብሄሮች ቀድሞ የተነሳውና እየተጠናከረ የመጣው ። በዚህ አኳያ ከታየ ትናንትም ሆነ ዛሬ በሌሎች ብሄርና ብሄረሰብ ሕዝቦች ውስጥ የሚታየውን ዓይነት የተጠናከረ የብሄረተኝነት ስሜት በኛ በአማሮች ውስጥ አለመታየቱ የሚያስገርም አይሆንም ። ይህንን የብሄረተኝነት ስሜት በውስጣችን ፈትሸን ማጣት ግን አንድ ዓይነት ቋንቋ ፡ ባህል ፡ ታሪክ ያለን አማራ የምንባል ሕዝቦች የለንም ማለት አይደለም ። የብሄረተኝነት ስሜታችን አለመጠናከርን ሆን ብለን እንዳመጣነው ፡ ብሄረተኝነትን ስለምንጠላ የተደረሰበት መደምደሚያ አድርጐ ማቅረብ እራስን ማታለል ነው ። ከሌሎች ሕዝቦች የተለየ ለየት ያለ ተጨባጭ ታሪካችን ያመጣው መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል ። ስለሆነም አንድ አማራ ብሄሩን ሲጠየቅ አማራ ባይል ወይንም ብሄሩን ለመናገር ቢያንገራግር እልፎ ተርፎም ኢትዮጵያዊ ብሎ ቢመልስ ችግሩ ከነቃ የፖለቲካ ተቃዎሞ ውጭ ሊነሳም የሚችል መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው ። በጅምላ ግራ የተጋባውንና ሆን ብሎ የሚያጭበረብረውን በአንድ ላይ ትምክህተኛ በማለት ችግሩን መፍታት አይቻልም ። ይህ ችግር የአብዛኛው የአማራ ምሁርና የከተሜ አማራው ችግር ስለሆነ በአማራው ሕዝብ ሕይወቱ ላይ የራሱ ጫና ስለሚያሳድር በደንብ መፍትሄ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነው ።

## ለ. ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ምስረታ አኳያ

ቀደም ብለን እንዳየነው በዘመናዊት ኢትዮጵያ ሃገር ምስረታ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተው ጠንካራ የሆነ የተማዕከለ አስተዳደር የነበረው የራሱን ብሄረተኝነት በዚሁ አስተዳደር አማካይነት ያዳበረ አማራ የሚባል ብሄር አልነበረም ። ከአማራው መሃከል የሸዋ አማራ እንዴት ወሳኝ ድርሻ እንደነበረው አይተናል ። በመቶ ዓመት የሃገሪቷ እድሜ ውስጥ ፤ ሌሎች ብሄርና ብሄረሰቦችን ትተን እራሱን አማራውን ከጐጃሜ ፣ ከጐንደሬ ፡ ከወሎዬና ከሸዌ አልፎ ተርፎም ከዚህ በታች ከሆኑ መንደረተኝነት ስሜቶችና አመለካከቶች ለማውጣት የቻለ ፖለቲካዊ፡ ኢኮኖሚያዊና



ማህበራዊ እድገት የአማራው ሕዝብ ማምጣት አልቻለም ። በተዋረራው በሃገሪቱ የነበሩ ብሄር ብሄረሰቦች ባሉበት እንደደረቱ፣ አማራውም በክልል በመንደር እንደተለያየ ፤ለመፍጠር የተሞከረው፣ በርእዮተ ዓለም ደረጃ ሁሉንም ወደ አንድ የሚጨፈልቅ ኢትዮጵያዊነት ነበር ። ሌሎች ብሄሮች ከደረሰባቸው ጭቆና ተነስተው በብሄራዊ ማንነታቸውና በኢትዮጵያዊነታቸው መ/ከል ክፍተት ማየት ሲጀምሩ፣ ብሄሬ ኦሮሞ ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ፡ ብሄሬ ትግሬ ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ሲሉ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ አማራውም በኢትዮጵያዊነቱና በአማራነቱ መሃከል ልዩነት እንዳለ ማየት ተስኖት ሁሉም ሕዝቦች በጋራነት የሚጠቀሙበትን ኢትዮጵያዊነት የዜግነት መለያ የብሄሩ መግለጫ አድርጐ ያስቀምጣል። ይህ ችግር የተፈጠረው የአማራ ገዥ መደብ በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄሮችን ሕልውና ለማጥፋት በብሄሮች ላይ አማርኛ ቋንቋን የአማራውን ባህልና ታሪክ የሁሉም ብሔሮች እንደሆነ አድርጐ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ቋንቋ ፡ ባህልና ታሪክ በአንድ ብሄር ቋንቋ ባህልና ታሪክ ለመተካት ተቀባይነት ለማግኘት ባደረገው ሙከራ ነው። ለዚህ ዓይነቱ የገዥ መደቡ ተንኮል ከሌሎች ብሄርና ብሄረሰቦች ይበልጥ ያለብዙም ጭንቀት ልንጋለጥ የቻልነው አማሮች በመሆናችን ዛሬ ከኢትዮጵያዊነት ትልቁ ጃንጥላ ስር የተጠለሉ ኦሮሞች ፣ አፋሮች ወዘተ መሃከል እኛም እንደእነዚሁ ተጠላዮች አንድ ፍጥረት እንጂ ሌላ መሆን እንደማንችል ስንረዳ ፡ ለዘመናት ይዘነው ከነበረ የገገር መደብ አመለካከት ጋር መጋጨቱ ስለማይቀር መደናገራችን የማይቀር ነው ።

## 3. ከነቃ የፖለቲካ ተቃውሞ የሚመነጭ ችግር

በዚህ ክልል የሚነሳው ችግር ኢትዮጵያ የብዙ ብሄሮች ሃገር መሆኗን ካለማወቅ (ካለመረዳት) የሚመነጭ አይደለም ። ሕዝቦች በብሄር በመደራጀታቸው ፣ ብሄራዊ መብታቸውን ለማስከበር በመነሳታቸው የራሳችንን እድል በራሳችን እንወስን በማለታቸው ፣ ራሳችንን እናስተዳድር ፡ በሃብታችን ተጠቃሚዎች እንሁን ፤ ቋንቋችን ፣ ባህላችን ፤ ታሪካችን ይከበር በማለታቸው በቀጥታ ሥልጣንና ተጠቃሚነትን በበላይነት ይዘው ከኖሩ ሃይሎች ጋር የሚያፋጥጥ በመሆኑ ነው ። ብሄሮች መብታቸውን ለማስከበር የሚያደርጉት ግፊት ከዚህ ቀደም እንደልቡ በሕዝቦች መብትና ሃብት ላይ ሲያዝ የነበረውን የተወሰነ

የሕብረተሰብ ክፍል ማስቆጣቱ አልቀረም ። ይህ የሕብረተሰብ ክፍል በጥንቱ ከተለያዩ ብሄርና ብሄረሰቦች ገገር መደቦች የተውጣጣ ቢሆንም በዋንኛነት ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ምስረታ ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ፖለቲካዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ ፤ ማህበራዊና ባህላዊ የበላይነቱን አስጠብቆ የኖረው የአማራው ገዥ መደብ ነው ። ከዚህ ቀደም በመንግሥት የአስተዳደር መዋቅሮች በቢሮክራሲው ፤ በጦር ሃይሉ ፤ በፀጥታ ፤ በፍርድ ሰጭነት ፤ በመንግሥታዊ የትምህርትና የምርምር ተቋማት ፤ በውጭ ሃገሮች ዲፕሎማሲ ግንኙነት ሥራዎች ሥልጣን በመያዝ ከፍተኛ ተጠቃሚ የነበረው ይህ ሃይል ነው ።

ይህንን ኃይል ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከተው እንኳንስ የሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች መኖርን ለመቀበል ቀርቶ የፈለቀበትን አማራዊ መሠረት አጥብቆ በመያዝ በአማራው ሕዝብ መሃከል የነበሩትን ክልላዊ ልዩነቶች አሸንፎ የአማራውን ሕዝብ በአንድ ክልል አስተዳደር በማካተት ጥብቅ የሆነ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ሊፈጥር ያልቻለ ሃይል ነው ። በኢትዮጵያ የሃገር ምስረታ ዋንኛውን ሚና የተጫወቱት የአማራ ነገስታትና መኳንንት በየጊዜው በተነሱ ቁጥር አማራነታቸውን መሠረት ያደረጉ ቢሆንም ውለው ሳያድሩ ነበር ይህንን አማራነታቸውን ወደጐን የሚገፉት ለዝናና ለሃብት በየጊዜው በሚያደርጉቸው የመስፋፋት ዘመቻዎች በግዛታቸው የሚያሰባስቧቸው የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በተበራከቱ ቁጥር አማራነትን በግልፅ አጥብቆ መያዝ ሌሎች ብሄሮችም የየራሳቸውን ብሄረተኝነት አጥብቀው እንዲይዙ የሚጋብዝ በመሆኑ በሃገሪቱ ብሄሮችና ብሄረሰቦች እንደሌሉ በማስመሰል መሄድ ብቻ ነበር የሚያዋጣው ። የሥልጣኑና የጥቅም ተቀናቃኞችን የማያበዛ በመሆኑ ብቸኛው መንገድ ነበርና ። ኢትዮጵያዊነት የግለሰብ የዜግነት መግለጫ መሆኑ ቀርቶ የተለያዩ ብሄሮችን ተጨባጭ ህልውና ሰርዞ ራሱ የብሄራዊ ማንነት መግለጫ ሆኖ መቅረብ የጀመረው በዚህ ምክንያት ነበር ። ችግሩ ግን በሌላ ቦታ እንዳየነው ኢትዮጵያዊነት የብሄር መግለጫ ለመሆን እንደ ወጥ የሆነ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ፤ ባህል ፤ ታሪክ ማትረብ ባለመቻሉ በደንብ ሲመረመር አማራነት ከመሆን አላለፈም ።

የሌሎቹ ቢቀር ከእኛው ከአማሮቹ መሃከል ጥቂቶቻችን ብሄራችንን ስንጠየቅ ኢትዮጵያዊ የምንልበት አንዱ ምክንያት የብሄራዊ ማንነትና የዜግነት የትርጉም ልዩነት ጠፍቶን ሳይሆን ስልጣንና ጥቅም አስከብሮ ለመቆየት ብቸኛው መንገድ ይህ ብቻ ነው ከሚል ንዛት የመጣ ነው ።



ምዕራፍ 3

# አማራነት ምንድነው ?

የሌሎች ሕዝቦች ብሔረተኝነት ጥርትና ኩልል ብሎ ሲታይ የአማራነት ስሜት ግን ለምን እንደሌሎቹ ሕዝቦች ስሜት በተመሳሳይ ደረጃ መታየት አቃተው ? ይህንን ጥያቄ እንድናነሳ ያስገደደን በፍጥነት በመቀየያር ላይ ያለው የሃገራችን ፖለቲካዊና ማህበራዊ እውነታ ነው ። ይህ እውነታ ምን እንደሚመስል ባለፉት ምዕራፎች አይተናል ። እንደሌሎቹ ሕዝቦችም የብሄረተኝነት ስሜት የአማራነት ስሜት ጐልቶ እንዳይወጣ ምክንያት የሆኑትን ችግሮች በመጠኑም ቢሆን ለመዳሰስ ሞክረናል ።

ባለፉት ምዕራፎች አማራ የሚለውን ቃል በተደጋጋሚ ብንጠቀምም ራሳችንንም አማሮች አድርገን ብንገልጽም እንዴት ይህን ቃል ለመጠቀም እንደበቃን እራሳችንንም አማራ አድርገን ለማየት እንደቻልን በቂ መግለጫ አልሰጠንም ። ይህን ማድረግ በመሃከላችን ለሚደረገው ውይይት ጥራትንና ግልጽነት የሚያመጣ በመሆኑ ለብቻው አንስቶ ጉዳዩን መፈተሽ አስፈላጊ ሆኗል ።

## በግድፈት የተደረሰበት ማንነት

በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካው አጀንዳ በግልጽ የብሄሮች አጀንዳ ሆኗል ። የፖለቲካ ቋንቋውም የብሄርና ብሄረሰቦች ቋንቋ ነው ። የፖለቲካ አደረጃጀቱም ይሄው ነው ። ከዚህ የፖለቲካ ቅኝትም የሚከሄዱ የኢኮኖሚ ፤ የልማትና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ብሄራዊ መልክ ይዘዋል ። በዙሪያችን የምናየው ብሄራዊ የልማት ኮሚቴዎች ብሄራዊ የቋንቋ ኮሚቴዎች ብሄራዊ የኪነት ቡድኖች ፤ ብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው ። የተለያዩ ብሄር ብሄረሰብ ምሁራን የእነዚህ ድርጅቶች መሪዎች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራም አርቃቂዎች ተግባሪዎች ሆነዋል ። በዙሪያችን እንዲህ ዓይ

ኑቶቹ እንቅስቃሴዎች ሲካሄዱ እናየለን ። በተለያዩ መንገዶችም ስለእንቅስቃሴዎቹ እንሰማለን ።

በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ገብተን እንሳተፍም ። ለመሳተፍም ፍላጎቱ የለንም ። እነዚህ እንቅስቃሴዎች የኛ አይደሉም የሚል ስሜት አለን ። የእነሱ ናቸው እንላለን ። ይህ የኦሮሞ ብሄር ድርጅት ነው ያኛው የትግራይ ፡ ያኛው ደግሞ የጉራጌ ወዘተ. እያልን እንለያቸዋለን ። በእነዚህ ድርጅቶች የልማት መሃበራት ውስጥ የመግባት ፍላጐት ማጣት ብቻ አይደለም መብትም የለንም የሚል ጠንካራ ስሜት አለን ። እነሱና እኛ የሚል ልዩነት እንዳለ ወደድንም ጠላንም ተረድተናል ። ከዚህም ተነስተን ኦሮሞች ፡ ትግሬዎች ፣ ጉራጌዎች ፡ አፋሮች ፡ ሶማሌዎች ካልሆንን እኛ ማነን የሚል ጥያቄ ማንሳት ጀምረናል ። ጥያቄውን እንደፈለግን ብናገላብጠው ሌላ መልስ ማግኘት አልተቻለም ። አማሮች ነን ከማለት በስተቀር ። አማራነታችንን ትተን ኢትዮጵያዊያን ነን እንዳንል ኢትዮጵያዊነት የኛ ብቻ ሳይሆን እኛንና የሌሎችን ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦችን ጨምሮ የወል መጠሪያችን ነው የሚል ጽኑ እምነት ስላለን ለብቻችን ልንጠቀምበት የምንችል ቃል አልሆነም ። ወይንም በሌላ መልኩ ሲደረግ እንደ ነበረው ጐንደሬ ፡ ጐጃሜ ፡ ወሎዬ ፣ ምንጃሬ ፡ ቡልጌ ፣ መንዜ ወዘተ. እያልን እንዳንሄድ ከላይ የተነሳውን እኔ ማነኝ የሚል ጥያቄ የምናነሳው ሁላችንም በጋራ ሆኗል ። ጎንደሬ ጎጃሜ ወዘተ በማለት መልስ ልንሰጥ ብንሞክርም መልሳችን የሚያረካ አልሆነም ። በልማት ማህበር ስም የተቋቋሙ ረጅም ዕድሜ ያላቸው የጐንደር ፣ የጐጃም ፡ የወሎ ፡ የቡልጋ የሚሉ የልማት ማህበራት ቢኖሩንም የተበጣጠሱ ናቸው በሚል ማማረር ጀምረናል ። በልማት መልኩ እንደሚደረገው የጐንደር የወሎ ፣ የጐጃም የሚል ስም ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች አለመኖራቸው ራሱ እነዚህ ክልሎች በማናቸውም መመዘኛ ራሳቸውን የቻሉ ፖለቲካዊ ውሁድ መሆን እንደማይችሉ ፡ መሆንም እንደማይገባቸው የተስማማን ይመስላል ። በለዚህ ወቅቱ ያመጣውን እኔ ማነኝ የሚል ጥያቄ ጐንደሬ ፡ ጐጃሜ ፡ ወሎዬ ፣ መንዜ ወዘተ እያልን ልንወጣው እንደማንችል ግልፅ ሆኗል ። ዞሮ ዞሮ አማራ ነኝ ማለት አልቀረም ። ከዚህ የምንረዳው አማራነት እንደሌሎቹ ብሄር ሕዝቦች ብሄረተኝነት በቀላሉ በግልፅ የሚደረስበት ስሜት አለመሆኑን ነው ። ነገር ግን የሌለ ነገር የሌለ ስሜት አለመሆኑን በተጨባጭ እያየነው መጥተናል ። አማራ የሚባል ሕዝብ እራሱን የቻለ ፣ በተ



ወሰነ ክልል የሚኖር ፣ የራሱ ቋንቋ ባህልና ተመሳሳይ ስነልቦና ያለው ሕዝብ መኖሩን ያወቅንበት አንዱ መንገድ ሁላችንም በጋራ አማሮች ነን የሚል መልስ መስጠት መቻላችን ነው ። ከዚህ ድምዳሜ ለመድረስ የሌሎች ብሄሮች ብሄራዊ ትግል ፖለቲካዊ ይዘቱ መጨመሩ ያበረከተው አስተዋጽኦ የፈጠረው ግፊት የማይካድ ነው ። በመሆኑ ነው አማራነት ፣ ዙሪያውን ሕዝቦች በብሄራዊ መልኩ ሲደራጁ አንድ ሕዝብ መሃከል ላይ ተለይቶ በመቅረቱ በግድፈት የተደረሰበት ግኝት ነው የምንለው ። ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም ስለ ብሄራዊ ማንነታችን እንስተን ለማናውቀው ግለሰቦች የዳበረና ያበበ በከፍተኛ ደረጃ የደረሰ አማራነት ስሜት ማግኘት ባንችልም ሌላው ቢቀር አማሮች መሆናችንን እኛንም የሚመስሉ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖች እንዳሉን ግልፅ አድርጉልናል ። የሚቀረን ነገር ቢኖር እንደህዝብ እያለን እንደሌለን አድርጐ በመሃከላችን ሊኖር ይገባ የነበረውን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ትስስር እንዳይኖር ያደረገውን ችግር በሚገባ ፈትሾ መፍትሄ መስጠት ብቻ ነው ።

## ፪. አማራነት የተሸፈነ እንጂ የጠፉ ስሜት አይደለም

የአንድን ስሜት ትርጉም በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ መንገድ መግለጽ ይቻላል ። ለምሳሌ ፍቅርን ብንወስድ ሰው መውደድ ነው ብለን በቀጥታ እንገልፀዋለን ። በተዘዋዋሪ ስንገልፀው ደግሞ ፤ ሰው መጥላት አይደለም ልንል እንችላለን ፣ በተመሳሳይ ፊት ለፊት በግልፅ የማይታይን አማራነት በተዘዋዋሪ ልንደርስበት እንችላለን ። የአማራነትን ስሜት ፊት ለፊት ለማየት ፈልገው ለማግኘት ስለአልቻሉ ብቻ አማራ የሚባል ሕዝብ የለም የሚል አመለካከት ላላቸው ወገኖቻችን ይህ አቀራረብ በመጠኑም ቢሆን ሁኔታውን እንዲፈትሹ ይረዳል የሚል እምነት አለን ።

ለምሳሌ፦

አንድን አማራ የሚባል ሕዝብ የለም የሚል አመለካከት ያለውን ግለሰብ ኦሮሞ ወይንም ወላይታ ነህ እንዴ ? የሚል ጥያቄ እናቅርብለት ። ኦሮሞ ከሆነ አዎን ኦሮሞ ነኝ ይላል ። ወላይታ ከሆነም ወላይታ ነኝ ይላል ። ካልሆነስ ? ካልሆነ ፤ ሶማሌ ከሆነ ሶማሌ ነኝ ፣ ትግሬ ከሆነ ትግሬ ነኝ ይላል ። ይህንን ዓይነት መልስ ለመስጠት

ቆይ ላስብበት የሚል የለም ። ጥያቄው እንደተጠየቀ መልሳችን ከመቅጽበት ይከተላል ። አማሮች ከሆንም ኦሮሞ ነህ እንዴ ላሚ ለው ጥያቄ አይ አማራ ነኝ ብለን መመለሳችን የተለመደ ነው ። መልሳችን ተራ መልስ አይደለም ። አማራ ነኝ ስንል በስሜት ነው ። አንዳንዶቻችን አልፈን ተርፈን እንዴት ያልሆንኩትን ነህ ወይ እባላለሁ በማለት የምንቆጣም አንጠፋም ። ለእንዲህ ዓይነቱ ፤ ጥያቄ አይ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ የሚመልስ አይገኝም ። ሲበዛ ይህም በአርሶ አደሮች አካባቢ ብቻ የሚከሰት ይሆናል ፣ አይ መንዜ ጐንደሬ ፣ ጐጃሜ ነኝ ብሎ ሊመልስ ይችላል ። ስለብሄር ለምን ታነሳለህ ለማለት የፈለገ ሰው አይ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ሊመልስ ይችላል ።

ይህ መልስ ግን በደመ ነፍስ ማንነታችንን እንደምንገልጸው የአብዛኞቻችን መልስ አይሆንም ። በስሌት የተሰራ የፖለቲካ መልስ ነው ። ከዚህ የምንረዳው አንድ ነገር ብቻ ነው ። እንደሌሎች ብሄረሰብ አባላት የነቃ የብሄረተኝነት ማህበራዊ ሕሊና በሁሉም ቦታና ጊዜ የሰረፀበት ሕልውና ባይኖረንም አማራነታችንን የሚፈታተኑ ወቅቶች ሲመጡ አማራነታችንን አጥብቀን እንደምንይዝ ነው ። ኦሮሞ ነህ ወይ ስንባል አይ አማራ ነኝ ብለን ስንመልስ ምን ለማለት ፈልገን ነው ። ስሜ አማራ ይባላል ለማለት አይደለም ወይንም በግሌና ለብቻዬ አማራ የሚለውን ስያሜ እጠቀምበታለሁ ለማለት አይመስለንም ። ኦሮሞነት ፣ ትግሬነት የተለያዩ ሕዝቦች መለያ ስም እንደሆነ ሁሉ አማራ ነኝ ብለን ስንል አማራ የሚባለውን ቃል የአንድ ሕዝብ መለያ መሆኑን አውቀን እየተጠቀምንበት ነው ። ከዚህ በጋራ አማራ የሚባል ስያሜ ካለው ሕዝብ መሃከል አንዱ እኔ ነኝ ስል ከዚህ ሕዝብ ጋር የሚያስተሳስሩን ነገሮች አሉ ማለት ነው ። የሚያስተሳስሩኝ ቋንቋዬ ፣ ባሕሌ ፣ ታሪኬ ፣ ወጌ ፣ ሥነ ልቦናዬ ወዘተ. መሆናቸው ነው ። እስካሁን የተባለው ፤ አማራነት የተሸፈነ ስሜት እንጂ የጠፋ ፤ የሌለ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው ። አማራ በዓለም ዙሪያ የሰፈሩ ደገኞች ስም አለመሆኑን አማራ እንደ ሕዝብ አንድ የተለየ ሕዝብ መሆኑን የሚያሳይ ነው ።

ከአማራው ነገሥታትና ከክርስትና ሃይማኖት የጠበቀ ትስስር ተነስተው ፣ በተጨማሪም በየቦታው የዘመተው የነገሥታቱ አማራ ወታደር የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ በመሆኑ ፤ ሌሎች ሕዝቦች አማራ የሚለውን ቃል ክርስትና ከሚለው ቃል ተወራራሽ ስላደረጉት አማራ ማለት ክርስቲያን ማለት እንጂ የአንድ የተለየ



ሕዝብ መጠሪያ አይደለም የሚሉትንም ማለሰቦች ስህተተኝነት የሚያሳይ ይመስለናል ። ኦሮሞ ነህ ወይ ለሚለው ጥያቄ አይ አማራ ነኝ ብለን ስንመልስ አይ ክርስቲያን ነኝ ማለት እንዳልሆነ ለሁላችንም ግልፅ ነው ። እስላም ነህ ወይ ለሚለው ጥያቄ ግን ከተሜዎቹ እስላም ከሆንን አዎ ነን ብለን እንመልሳለን ካልሆንም አይ ክርስቲያን ነኝ እንላለን ። በገጠር ግን ክርስቲያን የሆነ አማራን እስላም ነህ ወይ ብሎ ቢጠየቅ የለም አማራ ነኝ ብሎ ሊመልስ ይችላል፣ ይህን የሚልበት ምክንያት እራሱም ሆነ ሌሎች ሕዝቦች አማራነትንና ክርስቲያንነትን ተወራራሽ ቃላት አድርገው የሚጠቀሙበት ስለሆነ እንጂ አማራ የሚባል ሕዝብ የለም ለማለት አይደለም ። እንደ ሕዝብ አማራው በሃይማኖትም ቢሆን ክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የነበሩት አሁንም ያሉት መሆኑን አስታውሰን ማለፉ ተገቢ ይመስለናል ። አማራ ማለት ክርስትያን ነው ማለት፣ የትግሬው ክርስቲያን ፣ የኦሮሞው ክርስቲያን ፣ የጀርመኑም ክርስቲያን አማራ ነው ከሚለው አስቸጋሪ መደምደሚያ ነፃ አያደርገንም ። ይሄ ደግሞ አማራ የሚለውን ቃል ደገኛ ተራራ ላይ የሰፈረ የሚል ትርጉም ሰጥተው ከሃገራችን ተራራ አልፈው በሂማልያ ፣ በቲቤት፣ በአልፕስ ተራሮች ላይ የሰፈረውን ፍጥረት ሁሉ አማራ ነው ብለው ሊያሳምኑን ከሞከሩ ጠበብት ጥበብ የተለየ አይሆንም ። ዛሬ ላለንበት አስቸጋሪ ወቅት እንዲህ ዓይነቱ አንጉል ፍልስፍና እንደግለሰብ ሆነ እንደሕዝብ አይበጀንም ። አማራነት የዘመናት የጋራ ቋንቋ ፣ የዘመናት የጋራ ታሪክ ፣ ተመሳሳይነት ያለው ባህል ያላቸው ሕዝቦች የጋራ ማህበራዊ ማንነት መግለጫ ነው ።

እውነት ነው ይህ አማራነት የምንለው ነገር ለብዙዎቻችን አዲስ ክስተት ነው ። አዲስ ነው ስንል ግን በቅርቡ ጠፍጥፈን የሰራነው ነገር ነው ማለት አይደለም ። ከላይ ልናሳየው እንደሞከርነው አማራነታችን በተለያዩ ምክንያቶች ተጠናክሮና ጉልቶ በመውጣት በየቀኑ የሚታይ ስሜት አይሁን እንጂ ከልባችን የጠፋ ፤ ያልነበረ ነገር አይደለም ። በተለይ በጣም በርካታ የሆነው የአማራ ምሁር በመላ ኢትዮጵያ ተበትኖ በትላልቅ ከተሞች ሰፍሮ የሚገኝ በመሆኑ ፤ ወይንም በከተሞች እንደሚኖሩ እንደሌሎች ብሄሮች ምሁራን በገጠር ከሚገኙ ወገኖቹ ጋር የጠበቀ ትስስር የሌለው በመሆኑ ከአማራነቱ ንቅልነት የሚሰማው ሆኗል ። ከዚህ በመነሳት የሌሎች ብሄር ምሁራን ስለሕዝባቸው ልማትና እድገት በሰፊው ሲቆረቆሩና ሲንቀሳቀሱ ከራሱ ተርፎ ለሌሎች ሕዝቦችም ጭምር አለኝታ

መሆን የሚችለው የአማራ ምሁር በደመና ላይ ሕንፃ ሠርቶ ወደ
ምድረ አማራ አልወርድ ማለቱ በአማራው ሕዝብ ሕይወት ላይ
ጉዳት ማድረሱ አይቀርም ። የአማራው ሕዝብ የትናንቱ ድህነት ፣
በሽታና ረሃብ ዛሬም አልተለየውም ። ሁላችንም በውስጣችን እየተጫረች
ያለችውን የአማራነት የስሜት ብልጭታ ወደ ውጋጋን ቀይረን ፣
በሕዝባችን መሃከል ያለውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር መፍ
ታት ግዴታችን ነው ። ታሪክ በምኞት በዘፈቀደ አይሠራም ።
ያለንበትን እውነታ በደንብ ለመረጠረ የነገ ቤታችን ፣ የሕዝባችን
ተስፋ ፣ ዛሬ በረሃ እየበላቸው ፣ ዝናብ እያጠባቸው ፣ በመራቆት ላይ
ያሉት የአማራ ተራሮች ላይ ነው ። የነገ ማረፊያችን ፣ ዛሬ እንደባይተዋር
የምናየው የዚያ የቆፈናም የደበሎ ለባሽ ፣ የዚያ የሰው አክባሪ ፣
የእንግዳ አስተናጋጅ የአማራ አርሶአደር መንደር ነው ።

ሮ-አማራነትን ደምና አጥንት አያገልሀጠም ።

በዚህ ርዕስ ያለንን አስተያየት ከማጠቃለላችን በፊት ግን ከላይ
ያስቀመጥነው የአማራነት ምንነት በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ
የተሟላ ትርጉም ሰጥቶ ማለፉ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ጠቀ
ሜታ ይኖረዋል ።

ከዚህ በፊት ባለፍናቸው ምዕራፎች እንዳሳየነው የብሄር ጥያቄ
ሲነሳ ከስነልቦና ጭንቀት የተነሳ እውነተኛ ችግር ውስጥ የሚ
ገቡ በርካታ ግለሰቦችን አንስተን የእነዚህ ግለሰቦች ችግር ሊሰማ
ንና ለችግሩም መፍትሄ መስጠት ወገናዊ ግዴታችን እንደሆነ ገል
ጸን ነበር ። ለማስታወስ ያህል እነዚህ ግለሰቦች፡-

ሀ. ከአማራና ከሌሎች ብሄሮች የተወለዱ

ለ. በጋብቻ ከአማራና ከሌሎች ብሄሮች ተጋብተው ቤተሰብ የመሰ
ረቱ ነበሩ ፣

ከሃገራችን ሁኔታ ስንነሳ ከእነዚህ ውጭ ያሉ የአማራው ብሄር
በቋንቋና በባህል በሁሉም ሕዝቦች ላይ በነበረው የበላይነት የብሄ
ራቸውን ቋንቋና ባህል የረሱ ቋንቋቸው አማርኛ ባህላቸውም የአ
ማራ ባህል የሆኑ የሌሎች ብሄር ተወላጆችን ጉዳይ አንድ ላይ ማየቱ
ጥሩ ነው ። በሃገራችን የፖለቲካና የማህበራዊ ሕይወት ውስጥ እ'
ዚህ ግለሰቦች የተረጋጋና ገንቢ ሚና መጫወት እንዲችሉ የብሄ
ጥያቄ ሲነሳ ከሚገጥማቸው ስጋትና ጭንቀት ነፃ መሆን ይገ



ቸዋል ። በኛ እምነት የአንድ ብሄር አባልነት በግለሰቡ ውስጥ ባለ
የአማራነት ደም ወይንም የአማራነት አጥንት የሚተረጎም አይደ
ለም ። አማራነት ምንድነው የሚለውም ጥያቄ ምላሽ ያገኘው በቋ
ንቋ ፣ በባህልና በታሪክ ተመሳሳይነት ያላቸው ሕዝቦች ማህበራዊ
ስሜት ነው በሚል ነው ። በደም ፣ በአጥንት በዘር ሃረግ ቆጠራ የደ
ረስንበት አይደለም ። እውነታው ይህ ከሆነ በቋንቋው ፣ በባህሉ ፣
በስነልቦናው አማራነት የሚሰማው ማንኛውም ግለሰብ እራሱን
አማራ አድርጎ የማየት መብት አለው ። የአማራው ሕዝብ እንደ
ሕዝብ በፖለቲካ ፣ በልማትና በማህበራዊ ... ስኩ ራሱን ለመቻል
በሚያደርገው ትግል የመሳተፍ መብት አለው ። ግዴታም አለበት ።
በተለይ ባሁኑ ወቅት የሃገራችን የመንግሥት አወቃቀር ብሄርን
መሠረት ያደረገ ፌዴራላዊ አወቃቀር መሆኑ አማራጭ የሌለው
ጉዳይ እየሆነ በመጣበት ወቅት እንደነዚህ ያሉ ግለሰቦች ለራሳቸ
ውም የመንፈስ እርጋታ ሆነ ለሕዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ግንባታ
በሚያመች መንገድ የራሳቸውን ውሳኔ በነፃነት ሊወስኑ ይገባቸ
ዋል ። አንድን ግለሰብ ከሚናገረው ቋንቋ ከተላበሰው ባህል ለስሜቱ
ከሚቀርበው ወገናዊነት ውጭ በደምና በዘር-ሃረግ ቆጠራ የት እንደ
ሚገባ እኛ እንወስንለት የምንል ከሆነ በዚህ ኋላ ቀር አመለካከት
ያለምንም ምርጫና ፍላጎታቸው ከሁለት ካላነሰ ብሄር በመወለ
ዳቸው ብቻ ፣ ያለምርጫቸው በአንድ አካባቢ በመወለድና በማደ
ጋቸው ብቻ ኢሰብአዊ ድርጊት እየፈፀምንባቸው መሆኑን መረዳት
ይገባናል ። አድማሳዊ የስብዕና መለኪያ ያለን ሕዝቦች እንደመሆ
ናችን ሁሉ ለአማራነትም የምንሰጠው ትርጉም እንደዚሁ ጥልቅ
ስብዕናን የተላበሰ መሆን ይኖርበታል ።

በዚሁ አኳያ የብሄር ጥያቄ ሲነሳ ከላይ ባስቀመጥናቸው ምክንያ
ቶች ጭንቀት ውስጥ እየገቡ ለምን ጥያቄው ይነሳብናል ወይንም የሌለ
ብሄር ብሄረሰብ የሚል ጣጣ አምጥታችሁ በማለት በምኞት ሊቀ
የር ከማይችል እውነታ ጋር የሚጋጩ ወገኖቻችን ፣ ጉዳዩ የደም ፣
የአጥንት አለመሆኑን ሊያውቁት ይገባል ። የየግል ወይንም የቤተ
ሰብ ውሳኔያቸውን ያለምንም መሸማቀቅ ሊወስኑ እንደሚችሉ
መረዳት አለባቸው ። በእንዲህ ዓይነቱ ነፃ ውሳኔ ለሚደረስበት የአማራ
ነት ምርጫ የአማራው ሕዝብ ታላቅ ክበሬታን እንደሚሰጠው
እንጠራጠርም ።

ምዕራፍ 4

# አማራነትና ብሔረተኝነት

ባለፉት ምዕራፎች ፣ ብሔር ፡ ብሔረሰብ ፡ ብሔረተኝነት ፣ አማራነት የሚሉትን ቃላቶች በሰፊው ተጠቅመናል ። አማራነት ያልነውንም ጉዳይ ምን እንደሆነ አማራነት ምንድነው? በሚለው ጽሑፋችን ለመግለጽ ሞክረናል ። ነገር ግን ከአማራው በተያያዘ መልኩ ብሔርና ብሔረተኝነት የሚሉትን ቃላቶች ትርጉም ሰጥተን አልተጠቀምንም ። ስለሌሎች ሕዝቦች ስናወሳ የኦሮሞ ፣ የትግራይ ፣ የጉራጌ ፣ ወዘተ. . . ብሔሮችና ብሔረተኝነት በማለት ስንጽፍ በአማራው ጉዳይ ላይ ግን የአማራው ብሔር የአማራው ብሔረተኝነት የሚሉ አገላለጾች በሰፊው አልነበሩንም ። ይህንን ያደረግነው ያለ ምክንያት አይደለም ።

ምክንያቶቻችን ግን ትናንትም ዛሬም በአንዳንድ ቦታዎች እንደሚሰማው ብሔር ብሔረሰብ የሚሉትን ቃላቶች ለመጠቀም ያልተመለሱ ጥያቄዎች አሉ ከማለት አይደለም ። እንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች አሁንም በአካዳሚ ክበብ ውስጥ ሊያወዛግቡ የሚችሉ ቢሆንም ፣ የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ከተግባራዊ ፖለቲካ አንፃር ከታየ ችግሩን ፈትቶታል የሚል እምነት አለን ። ዛሬ አንድን ሕዝብ ጎሳ ፣ ብሔር ፣ ብሔረሰብ አልነው አላልነው ፤ ይህ ሕዝብ ቋንቋን ፣ ባሕልን ፣ ታሪክን መለዮ አድርጐ የተሰባሰበበትን ፤ ተሰባስቦ እንደ ሕዝብ ለመብቱ የታገለበትን ሁኔታዎች ፈጥሯል ። እየፈጠረም ነው ። ለዚህ ዓይነቱ የሕዝቦች መሰባሰብና መደራጀት ፤ ሕዝቦች የሚሰጡት ስም በዋንኛነት ብሔር ብሔረሰብ ነው ። የሚታገሉለትም መብት የብሔር ብሔረሰብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ነው ። የሚሰማቸውን ስሜትም ፣ የብሔረተኝነት ስሜት መሆኑን በግልፅ ያስቀምጣሉ ።

ወደ አማራው ሕዝብ ስንመለስ ፤ አማራነት ምንድነው? በሚለው ጽሑፍ ቋንቋን ፡ ባሕልን ፡ ታሪክን መሠረት አድርገን ከዚህም ጋር የተያያዘ ስሜት እንደሆነ ስለገለፅን ፤ እራሳችንን የአማራ ብሔር ወይንም ብሔረሰብ ፣ ስሜታችንንም የአማራ ብሔረተኝነት ብለን ማስቀመጥ አያዳግትም ። ሆኖም ግን የዚህ ዓይነቱ አገላለፅ ከአማራው



ሕዝብ ልዩ ታሪክ ጋር ተገናዝቦ ካልታየ የራሱ የሆነ ችግር ይፈጥራል የሚል እምነት አለን ። በመሃከላችን ለመፍጠር ለምንፈልገው መግባባት ከሌሎች ሕዝቦች ጋር እንዲኖረን ለምንፈልገው መልካም ግንኙነት ፤ ከዚህም በተጨማሪ የአማራው ሕዝብ በክልሉ ሆነ በሃገር አቀፍ ደረጃ እንዲመሠረት ለሚመኘው ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት፣ ማየት ለሚሻው ነፃ የኢኮኖሚ ዕድገት የራሱን ድርሻ በሚገባ ለመወጣት እንዲችል በአጠቃላይ በብሔረተኝነት በተለይም በአማራ ብሔረተኝነት ጉዳዮች ላይ ግልፅና የጠራ አመለካከት ሊኖረን ይገባል ። በሚቀጥሉት ገጾች የምናቀርባቸው አስተያየቶች ለዚህ የአመለካከት ጥራት ፋንሽም ቢሆን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

## የአማራው ብሔረተኝነት ያለፈውና መጪው ታሪክ

ኢትዮጵያ ዛሬ በውስጧ የያዘቻቸውን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦች ያቀፈች አንድ ሃገር ለማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ ከተወሰደበት ዕለት ጀምሮ የሃገራችን ፖለቲካ ብሔራዊ ይዘት ነበረው ብንል አንሳሳትም ። አጼ ምኒልክ አማርኛ ተናጋሪ ያልሆነውን የሰሜን ሆነ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ያስገበሩት በሸዋ መሳፍንትና መኳንንት በሚመራው የሸዋ አማራ ሠራዊት ነበር ። ይህ ማለት የየራሳቸው ንጉሶች የነበራቸው አማርኛ ተናጋሪ የሆኑ ክልሎችን አጼ ምኒልክ በወታደራዊ ኃይል አላስገበሩም ማለት አይደለም ። የወሎና የጐጃም ንጉሶችን መገበርን ልዩ የሚያደርገው ነገር ግን አለ ። በእነዚህ ክልሎች የሚነሱ ንጉሶች የአማራውን ሕዝብ በበላይነት ለማስተዳደር አማራነታቸውን መሠረት የሚያደርጉ ነበሩና በመሃከላቸው ትግሉ ብሔራዊ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ፤ ክልላዊ መሆኑ ነው ። ሌሎች ሕዝቦችን የማስገበር ሂደቱ ግን በግልፅ ብሔራዊ ይዘት እንደነበረው ማየት ይቻላል ።

በሰሜን ጫፍ ትግራይን በሰሜን ምሥራቅ አፋርንና በደቡብ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ትላልቅና አናሣ ብሔረሰቦችን ከወሰድን ሁሉም እንደ ሕዝብ ከአማራው የሚለያቸው የራሳቸው ቋንቋ ፣ ባሕል ፣ ታሪክ የነበራቸው ሕዝቦች መሆናቸው ነው ። ከአጼ ምኒልክ ጋር ፍልሚያ ገጥመው የተሸነፉትም ሆነ የንጉሡን ኃይል ተረድተው የገበሩት የተለያዩ ሕዝቦች ተራ በተራ የወደቁትም እንደ ኦሮሞ ፣ ጉራጌ ፣ ወላይታ ፣ ወዘተ. . . ነበር ። ይህ ማለት እነዚህ ሕዝቦች በክልል የተከፋፈሉ

ግዛቶችና የግዛት ስሜቶች ያልነበሯቸው በአንድ ወጥ የተማዐከለ አስተዳደር ይኖሩ ነበር ማለት አይደለም። ከአንድ ሕዝብ መሃከል ግማሹ በጦርነት፣ ከፊሉም ያለጦርነት የገበሩ እንደነበር ማስታወሱ በቂ ነው። እዚህ ላይ ቁም ነገሩ ሕዝቦች የአጼ ምኒልክን የግዛት ማስፋፋት ጦርነት ለመቋቋም የሞከሩት በቋንቋ፣ ባሕልና ታሪክ ዙሪያ እንደ አንድ ሕዝብ ተሰባስበው መሆኑ ነው። ይህ እስከሆነ ድረስ የዘመናዊት ኢትዮጵያ የፖለቲካ ይዘት ገና ከጅምሩ ዛሬ ያለንበትን የብሔር ብሔረሰብ ፖለቲካ በሆዱ ያዘለ ነበር ማለት ይቻላል።

በደቡብ የአጼ ምኒልክ የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተፈጸመ አልነበረም። በርካታ ጦርነቶችንና ብዙ ዓመታትን ፈጅቷል። የተለያዩ ሕዝቦችንም ያስገበሩት በአንድ ጊዜ ሳይሆን ተራ በተራ ነበር። ከዚህ የተነሳ ቀድመው በምኒልክ ግዛት ሥር ከወደቁት ሕዝቦች መሃከል ንጉሡ የጦር አበጋዞችንና ወታደሮችን በመመልመል ለቀጣይ የግዛት ማስፋፋት ጦርነት ማሰማራታቸው ይታወቃል። እነዚህ የጦር አበጋዞችና ወታደሮች ከሰሜንና ከደቡብም የተውጣጡ ነበሩ። ለምሳሌ ያህል ሁላችንም የምናውቀው ሁሌም በኦሮሞ ሕዝብ ዓይን እንደከሃዲ የሚታየውን የኦሮሞ ብሔር ተወላጁን የምኒልክ የጦር አበጋዝ ጐበና ዳጬውን መጥቀስ ይበቃል። ይሁንና የተለያዩ ብሔር አባላት በምኒልክ ጦር ውስጥ በአዛዥነት ይሁን በተራ ወታደርነት መግባት በዚያን ጊዜ በነበረውም ሆነ ከዛም በቀጠለው የፖለቲካ ሥርዓት ላይ ያመጣው ትልቅ ለውጥ የለም። የተለያዩ ብሔር ንጉሶችና ባላባቶች ከምኒልክ ጋር ወደው ሆነ ተገደው ማበራቸው በሥርዓቱ የአማራው ንጉሥ፣ መሣፍንትና መኳንንት የነበራቸውን የበላይነት የነካ ጉዳይ አልነበረም። ይህ የበላይነት በገበሩ ሕዝቦች ሃብት፣ ንብረትና የሰው ኃይል ላይ የማዘዝ ብቻ ሳይሆን፣ ግልፅ የሆነ የቋንቋና የባሕል የበላይነት ስለነበር ሌሎች ሕዝቦች የነበረውንና የቀጠለውን የበላይነት የአንድ ብሔር፣ የአማራ ብሔር የበላይነት አድርገው ቢያዩት የሚያስገርም አይደለም። በተለያዩ ወቅቶችም በአጼ ምኒልክ ሆነ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን እነዚህ የተለያዩ ሕዝቦች ጭቆናን በመቃወም ሲያምፁ፣ ያመጹት የጋራ ቋንቋን፣ ባሕልን ታሪክን መሠረት ባደረገ መሰባሰብ ስለነበር አመጻው ብሔራዊ ቅርጽና ይዘት ነበረው። ብሔራዊ ጭቆና እስከቀጠለም ድረስ የተለያዩ ሕዝቦች ተቃውሞ ብሔራዊ ስፋቱና ጥልቀቱ እየጨመረ መሄዱ ግልፅ ነበር። በአጼ ኃይለሥላሴ ቀጥሎም በደርግ ጊዜ የታየው ይኸው ሆኗል። ዛሬ በሃገራችን የብሔርና የብሔረሰቦች ፖለቲካ የፖለቲካ መድረኩን በበ



ላይነት የተቆጣጠረበት ምክንያትም ይኸው በብሔራዊ ጭቆና ምክንያት እያደገ የመጣው የተለያዩ ሕዝቦች ብሔረተኝነት መጠናከር ነው።

ወደ አማራው ሕዝብ ስንመለስ ግን ሁኔታው የተለየ ነው። ታሪክን በወጉ ለተመለከተ የአማራው ነገሥታት ጠንካራ የአማራ ብሔርና የአማራ ብሔረተኝነት ለመፍጠር ዛሬ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ብሔርና ብሔረሰቦች የተሻሉ ዕድሎች ነበራቸው። እነዚህ ዕድሎች የዘመነ መሣፍንት ማብቃት፣ የአጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት መሆንና የአውሮፓ ካፒታሊዝም ያመጣው ሥልጣኔ የኢትዮጵያን በር መቆርቆሩ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ አጼ ቴዎድሮስ ወደ ንጉሠ ነገሥትነት ሲያመሩ ተቀናቃኞቻቸውን የጐንደር መሣፍንቶች መነንና ልጅዋን እራስ ዓሊን የተዋጉበት ዋንኛው የፖለቲካ መሣሪያ የራሳቸውን አማራነትና የእነሱን የየጁ ኦሮሞነት በማስረገጥ ስለነበር ለአማራው ብሔረተኝነት ማበብ በአመለካከት ደረጃ በአማራው ሕዝብ ውስጥ ለም መሬት ፈጥረው ነበር። ከዚህም ጋር ተያይዞ ከአጼ ቴዎድሮስ በፊት ማንም ንጉሠ ነገሥት ቢሆን ያስገበራቸውን ግዛቶች በአንድ የተማዕከለ አገዛዝ ተቆጣጥሮ ለረጅም ጊዜ ለማቆየት የሚያስችል ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር ሊኖረው አይችልም ነበር። አጼ ቴዎድሮስ ግን የተበጣጠሱ የመሣፍንት ግዛቶችን በአንድ የማዕከል መንግሥት ለማስተዳደር የሚያስችሉ የመንገድ፣ የዘመናዊ ትራንስፖርት፣ በገንዘብ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ልውውጥ፣ የግዛቱን ፀጥታ ለማስከበር የአስተዳደሩን ገቢ ለመሰብሰብ ፈጣን እንቅስቃሴ ማድረግ የሚችል ፕሮፌሽናል የጦር ኃይልና ቢሮክራሲ የመሳሰሉትን ለማደራጀት የሚችሉበትን ሁኔታ ወደ አፍሪካ የገባው የአውሮፓ ካፒታሊዝም ይዞላቸው የመጣበት ወቅት ነበር። ይሁንና ታሪክ በእዚህ መልኩ አልሄደም። አጼ ቴዎድሮስ ለአማራ ብሔረተኝነት ማበብ በአማራው ሕዝብ ውስጥ የተፈጠረውን የአመለካከት ለም መሬት ሆነ የአውሮፓ ሥልጣኔ ያመጣውን የተለያዩ የአማራ ግዛቶችን በአስተዳደር በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር የሚያስችሉ ስልቶችን በመጠቀም ጠንካራ የአማራ ክልላዊ ብሔራዊ አንድነት ለመፍጠር ሳይችሉ ቀሩ። የዘመኑ ፊውዳል ንጉሶች እንደሚያደርጉት የራሳቸውን ትልቅነትና ገናናነት በሚገዙት ክልል ስፋት መለካት የማድ ነበርና የአማራውን ሕዝብ ውሑድ ብሔራዊ መንግሥት ሳያደራጁ በየአቅጣጫው መስፋፋት ጀመሩ። ካፒታሊዝም ካመጣቸው የተለያዩ ዘመናዊ መሣሪያዎች ሁሉ ይበልጥ ትኩረታቸውን የሳበው ለነበራቸው የመስፋፋት ዓላማ ጠቀሜታ አለው ብለው ያመኑበት የጦር መሣሪያ መሆኑ ግልፅ ነው። ከሁሉም ነገር ይበልጥ ለመድፍ ግንባታ የሰጡት

ትኩረትና ከዚሁ ጋር ተያይዞም ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉት ግጭት በዚህም የተነሳ ሕይወታቸው ማለፉ ለአባባላችን በቂ ማስረጃ ነው። የአማራ ብሔረተኝነት መጠናከር የአማራ ብሔር ምሥረታም በአጭር ተቀጨ። አጼነታቸው በተለየ መንገድ ተጉዘው ቢሆን ኖሮ የአማራው ብሔረተኝነት መግለጫ አሁን ካለበት የተለየ መልክ ይዞ በቆየን ነበር።

ከአጼ ቴዎድሮስ ሞት በኋላም የትግራይ ፊውዳሎች በአጼ ዮሐንስ ሥር ተሰባስበው የመንግሥት ሥልጣን ወደ ትግራይ ያዘነበለ የመሰለበት ወቅት መጣ። ይህ ወቅት አጭር በመሆኑ በአማራ ብሔረተኝነት ላይ ፋይዳ ያለው ለውጥ አልታየም። ከአጼ ዮሐንስ ሞት በኋላም በአጼ ምኒልክ መሪነት ተጠናክሮ የወጣው የሸዋ ፊውዳል ኃይል የተረከበው ብሔራዊ አንድነት ያልነበረውን የአማራ ሕዝብ ነው። ሕዝቡ በግዛቶች የተከፋፈለ ታማኝነቱ ለየግዛቶቹ ንጉሶችና ገዢዎች እንጂ ለአንድ የአማራ ብሔራዊ መንግሥት ያልነበረ ነበር። ቀደም ብለን የጠቀስነው የሰሜንና የደቡብ የአጼ ምኒልክ የግዛት ማስፋፋት እንቅስቃሴ ገና ከጅምሩ የአማራውን ብሔር እንደ ብሔር መሠረት ያደረገ ስላልነበረ፣ በጎጃም በጎንደር፣ በወሎ የነበሩትን የአማራ ገዥዎች እንኳን ሳይቀር ከሥልጣን ያገለለ ነበር። አጼ ምኒልክ ከአጼ ቴዎድሮስም በተሻለ የታሪክ መጋጠሚያ ላይ የመጡ ንጉሥ ቢሆኑም፣ ይህንን ዕድል የአማራውን ክልላዊ ብሔራዊ አንድነት ለማምጣት አልተጠቀሙበትም። እንዲያውም የአጼ ምኒልክ ግዛት በሰሜንና በደቡብ እየሰፋ በሄደና የተለያዩ ብሔር ሕዝቦችን በጠቀለለ ቁጥር በሌላ ምዕራፍ ቀደም ብለን እንዳየነው የተጠናከረ የአማራ ብሔር ግዛት መመሥረት ጭራሽኑ ሆን ተብሎ የተገፋ ጉዳይ ሆነ። በኢትዮጵያ የሸዋ ባላባቶች የፈጠሯቸው የአስተዳደር ክልሎች በሙሉ የአንድን ብሔር ብሔራዊ ማንነት እንዲያዳክሙ የታለሙ ነበሩ። ከአጼ ምኒልክ ዘመን እስከ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ፍፃሜ ያየነው ይህንኑ ነው። እንደሌሎች የተጨቆኑ ብሔር ብሔረሰቦች አማራው በብሔራዊ ማንነቱ ዙሪያ የተመሠረተ፣ የአማራውን ሕዝቦች በአማራነታቸው ያዋሃደ የተማዕከለ አስተዳደር እንዳይኖር መደረጉ በተከታታይ የተነሱ የአማራ ገዥዎች ብቸኛ የሥልጣንና የጥቅም ፍላጎት ውጤት ነው። አንድን ሕዝብ በተበታተኑ የአስተዳደር ክልሎች መቆራረጥ ለገዢዎች የከፋፍለህ ግዛ ስልት አመቺ ነበር። ሥልጣናቸውን የሚጋፉ የሚያምጽን አንድን ባላባት በሌላ ባላባት በማስመታት የሥልጣናቸው ማጠናከሪያና መሰንበቻ አድርገውታል።



በደርግ ዘመንም በኢትዮጵያ የተዋቀረው የአስተዳደር ክልል የቀድሞ የአማራ ገዥዎችን ፈለግ የተከተለ፣ የአማራውን ሕዝብ በተበተነ መንገድ በጎንደር፣ በወሎ፣ በጎጃም፣ በሸዋ እንደ ቀድሞው የከፋፈለ ነበር። የአማራውን ሕዝብ በአንድ የአስተዳደር ክልል በማሰባሰብ ከአማራው ሕዝብ ውህደት የሚመነጭ የአማራው ሕዝብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊ ባሕላዊ ጥንካሬ የገታ ነበር። የአማራው ሕዝብ በአማራነቱ ሊያጎለብተው ይገባ የነበረውን የአማራ ብሔረተኝነት ሶንደ ተቀብሮ እንዲቀር በማድረግ ዛሬ የአማራው ሕዝብ ላለበት አስቸጋሪ ሁኔታ የዳረገው ይሄው የተከታታይ ገዥዎች ሥራ ነው።

የአማራው ሕዝብ ችግር አንድ ጠንካራ ውሁድ ብሔራዊ አስተዳደር እንዳይኖረው በማድረግ ብቻ አላበቃም። አማራነት ወደ ጐን እየተገፋ እየተቀበረ እንዲሄድ በተደረገ ቁጥር የአማራ ገዥዎች የአማራውንና ሌሎችንም በግዛታቸው ውስጥ ያስገቧቸውን የተለያዩ ብሔረሰብ ሕዝቦች ብሔረተኝነት ለማስወገድ አዲስ ብሔረተኝነት መስበካቸው አልቀረም። ይህ ብሔረተኝነት ከሁሉም ብሔርና ብሄረሰቦች ብሄረተኝነት በላይ የቆመ ኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት ነው። ይህ ብሄረተኝነት በደንብ ሲፈተሽ ምን እንደሚመስል ለምን በተሟላ መልኩ ዕውን ማድረግ እንዳልተቻለ ባለፉት ምዕራፎች አይተናል። ከአማራው ቀድመው እንዲህ ዓይነቱን ብሔረተኝነት ለምን የተጨቆኑ ብሔሮች መፈታተን እንደጀመሩም አውስተናል። እዚህ ላይ ትንሽ ሰፋ አድርገን ለማየት የምንሞክረው ይህ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት በአማራው ብሔረተኝነት ዕድገት ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ይሆናል።

የአማራው ሕዝብ የራሱን ብሔረተኝነት ረግጦ በምትኩ ገዥዎች በፈጠሩት የኢትዮጵያ ብሔረተኝነት ከሌሎች ሕዝቦች ይበልጥ እንዲያምን ያደረጉት በርካታ ምክንያቶች ናቸው። ቀደም ሲል ስለ አጼ ቴዎድሮስ ስናወሳ እንዳየነው የአማራ ገዥዎች ወደ ሥልጣን ብቅ ማለት ሲጀምሩ ለአማራነት የሰጡት ትርጉም አማራነትን በራሱ ለገገርነት በቂ ማረጋገጫ ማድረግ እንደነበር ነው። ይህ ትርጉም በቀጣይነት በተግባር በመንግሥት መዋቅር፣ በቢሮክራሲው ውስጥ መንፀባረቁ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ፍርድ ቤቶች፣ ሕግ አስፈፃሚ አካላት የአማርኛን ቋንቋ መጠቀማቸው በአብዛኛውም በአማራው በመሞላታቸው አማራው መሸንገሉ አልቀረም። በትምህርት ተቋሞች፣ በቤተክርስቲያን፣ በመንግሥት ድርጅቶች፣ በማኅበራዊ ሕይወቱ በአፈታሪክ በተረት አማካይነት በአማራው ሥነልቦና ውስጥ እንዲሰረጽ የተደረገው የማይካድው የአማራው አማራነት ሳይሆን፣ ቀደም ብለን የተጠ

ቀሰው አማራነቱን እንዲረሳ ታስቦ የተቀየሰውን ኢትዮጵያዊነት ነው ። በዚህም የተነሳ ነው እራሳችንን በአማራነት ማየት ያልቻልንበት ፣ በአማራነትና በኢትዮጵያዊነት መካከል ያለውን የማይሸፈን ልዩነት ለማየት አቅም ያጣነው ። አንድ አማራ ከአማራነቱ ጋር የተሳሰረ የማንነቱ ግንዛቤኖሮት የዚህን ግንዛቤ ጤናማነት እንዲቀበል ከተፈለገ አማራነቱን እንዳያይ ለዘመናት ገዥዎች በጉሊናው ላይ ያደሩበትን ድር መግፈፍ ይኖርበታል ።

እስካሁን ከተባለው የምንገነዘበው አንድ ቁም ነገር ነው ። በኢትዮጵያ ስለ ብሔረተኝነት ታሪክ ስናወራ የሁሉም ሕዝቦች የብሔረተኝነት ታሪክ አንድ አለመሆኑን ነው ። ከአማራው ውጭ ያሉት ሕዝቦች ብሔረተኝነት መልክ መያዝና መጠናከር የጀመረው በቀጥታ በአማራው ገዥዎች አማካይነት እነዚህ ሕዝቦች ሲደርስባቸው በነበረው ጭቆና ምክንያት ነው ። ይህ ድርጊት እነዚህ ሕዝቦች እንደ ብሔር እንዲያድጉና ብሄረተኝነታቸውም እንዲጠናከር አድርጓል ። በእነዚህ ብሔር ሕዝቦች ላይ በቋንቋ ፣ በባሕል ፣ በታሪክ የሚደርስባቸው ጭቆና ሁሉንም የብሔሩን የኅብረተሰብ ክፍል በጥቅሉ ያካተተ ነበር ። የእነዚህ ብሔሮች መሣፍንቶችና ባላባቶች ሕዝቦቻቸውን በማስተባበር በሔራዊ አመፃዎችን ያስነሱባቸው አጋጣሚዎች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቁጥሩ ቀንሽ አይደለም ። ባለንበትም ወቅት ቢሆን የእነዚህ የተለያዩ ብሔር ሕዝቦች በፖለቲካ ሥልጣንና በኢኮኖሚ ጥያቄ ላይ የተለያዩ አመለካከት ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ቢኖሩዋቸውም በብሔራዊ እኩልነት ጥያቄ ላይ ከሞላ ጐደል ከሊቅ እስከ ደቂቅ በአንድ የቆሙ ናቸው ማለት ይቻላል ።

ወደ አማራው የብሄረተኝነት ታሪክ ስንመለስ ግን የተለየ ሥዕል እናገኛለን ። የአማራው መሣፍንት ባላባትና ምሁራን እንደሌሎቹ ብሔሮች ባላባትና ምሁራን የራሳቸውን ብሔረተኝነት የሚያጠናክር ታሪክ አልነበራቸውም ። የነበራቸውም የባህልና የቋንቋ የበላይነት የብሔር ጥያቄን ማንሳት አላስፈላጊ ያደረገ ስለነበር ባለማንሳታቸው መገረም የለብንም ። እንኳን ቀደም ባሉት አደናጋሪ ዘመናት ቀርቶ አሁን እንኳን እንዲህ የብሔር ብሔረሰቦች ጉዳይ ጎልቶ በወጣበት ወቅት የአማራው ብሔረተኝነት ጥያቄ ሲነሳ የማይዋጥላቸው ወገኖቻችን በርካታ ናቸው ። ይህ ሐቅ ነና በእግሩ ለመሄድ በመንገዳገድ ላይ ያለው የአማራ ብሔረተኝነት ተጠናክሮ መውጣት እስኪችል ድረስ በራሳችን ውስጥ ሠፊ ትግል እንደሚጠብቀን የሚጠቁም ነው ። የአማራው ብሄረተኝነት እንደሌሎች ብሄሮች ብሄረተኝነት የሁሉም የአማራው ኅብረተሰብ ክፍል ጅምላ



ድጋፍ ያገኛል ብሎ ማሰብ ስኅተት ይሆናል ። የአማራው ብሄረተኝነት እንዲጠናከር የአማራው ሕዝብ ጠንካራ ብሄራዊ ድርጅት እንዲኖረው የተማዕከለ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ አስተዳደር እንዲያገኝ ሁሉንም የአማራ ክልሎች የሚያስተሣሥር የልማትና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ እንዲያብብ እነማን በፅናት እንደሚቆሙ ከወዲሁ ግልፅ ነው ። የአማራው ገዥ መደብ ከዚህ ቀደም በሃገሪቷ በነበረው የቋንቋ የበላይነት በቋንቋው ከመጠቀም በስተቀር ቤሳ ቤስቲን ያላየው ፣ ዛሬ መጩቅጩቂት እንደለበሰ ፣ ዛሬም ትኋንና ቅማል እንደበላው ፣ ዛሬም ጀርባ በሚያጐብጥ ነገር ግን ከእጅ ወዳፍ በማያልፍ መራራ ሕይወት የሚሰቃየው የአማራ ሰፊ አርሶ አደር የአማራው ብሔረተኝነት የማይነቃነቅ መሠረት ነው ። ከዚህ ቀደም በሀገራችን የዲሞክራሲ ትግል የብሔሮችን እኩልነት የመሬት ላራሹን የሕዝቦች የፍትህና የነፃነት ጥያቄ በማንሳት ተወዳዳሪ የማይገኝለት መስዋዕትነት የከፈለው ሰፊ የአማራ ምሁር ያለበትን ጊዜያዊ ችግር ተወጥቶ ከአማራው አርሶ አደር ጐን የሚቆመው ሌላው ኃያል ኃይል ነው ። ከዚህ ውጭም ዛሬ የአማራነታቸው ጉዳይ እንደሁላችንም እያሳሰባቸው የመጣው ፣ የአማራው ክልል እንደሌሎች ክልሎች ለዕድገትና ለልማት ሲነሳሳ ባለማየታቸው መቆጨት የጀመሩ ፣ ሀብት ዕውቀትና ሙያ ያላቸው አማሮች በሙሉ ከአማራው አርሶ አደርና ምሁር ጐን የሚቆሙ ናቸው ። በአማራ ብሄርተኝነት ዙሪያ የሚሠራውን መጪ ታሪክ የሚሠሩት እነዚህና እነዚህ ብቻ ናቸው ።

## ጭፍን ብሔረቀኝነትን የማይቀች
## የአማራ ብሔረተኝነት ከቶውኑ ሊኖር አይችልም

በኢትዮጵያ የተለያዩ ሕዝቦች በተለያዩ ወቅቶች እምቢ አሻፈረን በማለት የተለያዩ ሥርዓቶች የሚጭኑባቸውን ጭቆናና ብዝበዛ ተቃውመው አምፀዋል ። የአማራው ሕዝብ አርሶ አደሩ ላብ አደሩ ምሁሩ ሌላውም አገር ወዳድ በእነዚህ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የፀረ ጭቆና ትግል ውስጥ የራሱን ከፍተኛ ድርሻ አበርክቷል ። በኢትዮጵያ ውስጥ ለነፃነት ፣ ለፍትህ ፣ ለእኩልነት በተደረገው ትግል የአማራው ሕዝብ ድርሻ ምን ይመስል እንደነበር ወደፊት የሕዝብ ታሪክ ፀሐፍት የአማራ ምሁራን እንደሚዘግቡት ተስፋ እናደርጋለን ። በዚህ ጽሑፍ ለማየት የምንሞክረው ግን የአማራው ሕዝብ ትግል ከሌሎች ሕዝቦች የሚለዩትን ግልፅ ባሕሪዎች ይሆናል ። ይህን በማድረግ ወደፊት

የአማራው ብሔረተኝነት ከጋራ ቋንቋ ባሕል ታሪክ ወግና የጋራ ስሜት በላይ አልፎ ጭብጥ የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፕሮግራሞቹ ምን መሆን እንደሚገባቸው በመሃከላችን ለሚደረግ ውይይት የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ከሚል እምነት ነው ።

የአማራው ሕዝብ ትግል ልዩ የሚያደርገው ሕዝቡ ትግሉን ያደረገው በቀጥታ ቋንቋውን ከሚናገር ፡ ባህሉን ከተላበሰ የአማራ ገዥ መደብ ጋር መሆኑ ነው ። ቋንቋውን እየተናገሩ ፡ ባሕሉን ተላብሰው የሃገሪቱን ሕዝቦች ሕይወት በመዳፋቸው የያዙ ነገሥታትና መሣፍንት እነዚህንም የተከሉ አምባገነን መሪዎች በሌሎች ሕዝቦች ላይ ከዘረጉት የብዝበዛና የጭቆና መረብ ወጭ አለመሆኑን ቀድሞ የተረዳ ሕዝብ ነበር ። በአጼ ኃይለ ሥላሴም ይሁን በመንግሥቱ ዘመን የተነሳው የጐጃም ፡ የጐንደር ፡ የወሎና የሸዋ አርሶ አደር አመጽ በገዢዎቹና በአርሶ አደሩ መሃከል በጥቅም በፍትህና በዕኩልነት ጥያቄ ላይ ሆድና ጀርባ መሆናቸውን የተረዳ አመፃ ነበር ። በኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ የትግል ታሪክ ውስጥም ግንባር ቀደም ሚና የነበራቸው የአማራ ዲሞክራሲያዊ ምሁራን ታሪክ የሚያሳየው ይህንኑ በገዥዎቹና በአማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች መሃከል የነበረውን እርቅ የለሽ ትንንቅ ነው ። ይህ ዓይነቱ ታሪክ ለአማራው ሕዝበ ያስተማረው ነገር ቢኖር አንድ ግለሰብ አማራ በመሆኑ ብቻ ለሕዝብ ማሰብ ፡ ለፍትህና ለዕኩልነት መቆምን ተፈጥሮ የምትቸረው አለመሆኑን ነው ። ገዥዎች ምንም ያህል አማራ ቢሆኑ ሥልጣናቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር የአማራውን አርሶ አደር ምሁርና አገር ወዳድ ከማሰር ፡ ከመጨፍጨፍ እንደማይመለሱ ነው ። ይህን ሐቅ የሚያውቅ ሕዝብ በብሄረተኝነት ስም ቋንቋና ባሕሉ አንድ የሆነውን ሁሉ እያግበሰበሰ ወደ ዳግም ጥፋት እንዳይጎዝ ከታሪክ ማስጠንቀቂያ የወሰደነውና ዕድለኛ ነው ማለት ይቻላል ። የሩቁን ትተን የቅርቡ ማስጠንቀቂያ እንዲህ ይለናል ፦

"መላኩ ተፈራ የእግዜር ታናሽ ወንድም
የዛሬን ማርልኝ ሁለተኛ አልወልድም"

ከአማራው ሕዝብ ተወልዶ የአማራውን ሕዝብ ወጣት ሽማግሌውን ፡ ሴት ወንዱን ያለምንም የወገን ስሜት ከኢጣልያን ፋሽስቶች በከፋ ፋሽስትነት የጨፈጨፈ መላኩ ተፈራ ብቻ አልነበረም ። መላኩ ተፈራ የጐንደርን እናቶችንና የጐንደርን ሕዝብ የወላድ መሃን እንዲሆኑ ያደረገ አረመኔ ነበር ። የጐጃምን ሕዝብና ጀግናውን በላይ ዘለቀን የብቸናን ሕዝብና ጀግናውን ውባለ ተገኑን ፡ የንዋይ ልጆችን ፡ የጐንደሩ አምበሳን ወርቅነህ ገበየሁን ፡ የወሎውን የሕዝብ ልጅ ዋለልኝ መኮንን በአጠቃላይ ዘርዝረን የማንጨርሳቸው ኀልፈታቸው በአማራው ሕዝብ ሕይወት ለትውልድ የሚተላለፍ ሃዘን የተወውን የቡልጋ ፡ የምንጃር ፡ የመንዝን ወጣት ምሁራን ፍጅት ስናስታውስ ማን ለፍጅቱ በዋንኛነት እንደሚጠየቅ አንረሳም ።

ለዚህም ነው የአማራ ብሄረተኝነት እንደሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብሔረተኝነት ከቋንቋና ከባሕል ጭቆና የተሳሰረ ባለመሆኑ ቋንቋና ባሕልን ከለላ አድርጎ ለሥልጣን መወጣጫ ሊጠቀምበት ማንም አይችልም የምንለው ። የአማራው ብሄረተኝነት የሚቀፋቸው ኃይሎች በአማራነታቸው የፀና እምነት ያላቸውን የሕዝቡን ልዕልና የሚያከብሩ ለአማራው ሕዝብ የጋራ ዕድገትና ብልፅግና የሚሠሩ ፡ በአማራው ሕዝብ የትግል ታሪክ ውስጥ አድማሳዊነታቸውን ማንም የማይክዳቸውን የዲሞክራሲና የስብዕና መመዘኛዎች ይበልጥ ለማጠናከር የሚጥሩትን ብቻ ነው ። ከዚህ ውጭ በቋንቋና በባህል ተመሳሳይነት ብቻ የታጠረ ዲሞክራሲያዊነትን ፡ ፍትሃዊነትን ፡ ቅንነትን ፡ ታማኝነትን ፡ ሕዝባዊነትን ፡ ነፃነት ወዳድነትን ፡ ሰብዓዊነትን ያልፈተሸ ጭፍን ብሔረተኝነት የአማራው ብሔረተኝነት መግለጫ ከቶውኑ ሊሆን አይችልም ።

ምዕራፍ 5

## ለአድማሳዊ ጭቆና የአማራው ምሁር ብቸኛ ምላሽ አድማሳዊ ፀረ-ጭቆና ትግል ነበር

በኢትዮጵያ የነገሥታቱንና በኋላም የደርግን አምባገነናዊ አገዛዝ በመቃወም የአማራው ዲሞክራሲያዊ ምሁር ከፍተኛ የትግል መስዋዕትነት ከፍሏል ። በዚህ ትግል ውስጥ ግን ይህ ምሁር እንደ አማራ የተደራጀ ወይንም የአማራውን ሕዝብ መብትና ነፃነት ብቻ ለማስከበር የተነሳ አልነበረም ። ያነሳቸው ጥያቄዎች የሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝቦች የመከራና የድኅነት ሕይወት የሚነኩ ነበሩ ። ይህ ትግል ምን እንደሚመስል በዚህ አጭር ጽሑፍ ሁሉንም መነካካት ባንችልም ፣ ጥቂቶችን ለማንሳት እንሞክራለን ። እግረ መንገዳችንንም ዛሬ አስተዋሽ አጥቶ ተቀብሮ የቀረውን ሕልቆ መሳፍርት የሌላቸውን ውድ የአማራ ልጆች የበላውን ለዲሞክራሲ ፣ ለፍትህ ፣ ለሕዝቦች ዕኩልነት የተከፈለውን ታሪካችንን ያስታውሰናል ።

ታኅሣሥ 1953 ዓ.ም.

ታኅሣሥ 4 ቀን 1953 ዓ.ም. የነዋይ ልጆች መንግሥቱና ገርማሜ የመሩት መፈንቅለ መንግሥት "አለቀ ደቀቀ" በሚል ርዕስ ባስተላለፉት የሬዲዮ መግለጫ ፣ ስጋ የተላበሰ ሰው የማይደፍረው ይመስል የነበረውን መለኮታዊ የአጼ ኃ/ሥላሴ መንግሥት ማብቃት አበሰረ ። እርምጃው የራሱ ታሪካዊ ውስንነት ቢኖረውም ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ዓይን ገላጭ ነበር ። የሰለሞን ስርወ መንግሥት ሊገፋ ፣ ሊጣል እንደሚችል ያበሰረ ነበርና ።

መፈንቅለ መንግሥቱ ከሸፈ ። ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ነዋይ እራሱን ለመግደል ያደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀርቶ ተያዘ ። ያም ሆኖ ከንጉሡ ፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኞች ሳላለቀበት የሙት



ይብቃ ብያኔ ይግባኝ ይል እንደሆን ተጠይቆ ያሰማው ሕዝባዊነትና ጀግንነት የተሞላው ንግግር እንዲህ መሰለ ።

"እናንተ ዳኞች የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለይግባኝ ተቀብያለሁ ። ይግባኝ ብዬ ጉዳዩን የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ ይግባኝ ማለት በፈለግሁ ነበር ። ነገር ግን ይህ እንደማይሆን አውቃለሁና በይግባኝ የአጼ ኃ/ሥላሴን ፊት ለማየት አልፈቅድም ። በእግዚአብሔር ስም ተሰይማችሁ በተቀመጣችሁበት የፍርድ ወንበር ላይ ከመቀመጣችሁ በፊት በእኔ ላይ የሞት ሰጡትን የዛሬውን ፍርድ ታውቁት እንደነበር ሳስብና ፍርድ እስከዚህ መርከሱን ስታዘብ ሃዘኔ ይበዛል ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ነፃነትና እርምጃ የተነሳሁ ወዳጅ ነኝ እንጂ ላፋጀው የተነሳሁ ወንበዴ አይደለሁም ። ይህንን ፈልጌ ቢሆን ኖሮ ማንም የማይወዳደረው ሠራዊትና መሣሪያ ሳላጣ ዛሬ ከእናንተ ፊት ለመቆም ባልበቃሁ ነበር ። እኔ ከአጼ ኃ/ሥላሴ ድንክ ውሾች ያነሰ ደመወዝ የሚያገኙ ሁለት የተራቡ ወታደሮች አጣልቼ ለማደባደብና አገር ለማፍረስ አለመምጣቴን የሚያረጋግጥልኝ እናንተ በትዕዛዝ ያገኛችሁትን ፍርድ ለመቀበል እዚህ መቆሜ ነው ።

ከእኔ በፊት በግፍ የፈሰሰው ንፁህ የኢትዮጵያውያን ደም ብዙ ነው ። በአጼ ኃ/ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ግፍ ሸልማት በመሆኑ እኔ ለሞት የመጀመሪያው ሰው አልሆንም ። ሥልጣን አላፊ ነው ። እናንተ ዛሬ ከጨበጣችሁት የበለጠ ሥልጣን ነበረኝ ። ሀብትም አላጣሁ ። ነገር ግን ሕዝብ የሚበደልበት ሥልጣንና ደሃ የማይካፈለው ሐብት ስላልፈለግሁ ሁሉንም ንቄ ተነሳሁ ። አሁንም እሞታለሁ ። ሰው ሞትን ይሸሻል እኔ ግን በደስታ ወደ ሞት እሄዳለሁ ።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነት ቀድመውኝ መስዋዕት የሆኑትን አብረውኝ ተነስተው የነበሩትን ጀግኖች ወንድሞቼን ለመገናኘት ናፍቄአለሁ ። የጀመርኩት ሥራ ቀላል አይደለም ። አልተሸነፍኩም ። ወገኔ የሆነውን ደሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀመርኩለትን ሥራ በቅርቡ ጊዜ ውስጥ ፈፅሞ ራሱን በራሱ እንደሚጠቅም አልጠራጠርም ። ከሁሉ በበለጠ የሚያስደስተኝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ልሠራለት ካሰብኳቸው ሥራዎች አንዱ የኢትዮጵያ ወታደር ዋጋና ክብር ከፍ ማድረግ ሲሆን ይህ ሃሣቤ ሕይወቴ ከማለፉ በፊት ሲፈፀም ማየቴ ነው ።

ዛሬ መኖራችሁን በማየት ነገ መሞታችሁን ረስታችሁ አሜን ብላችሁ ቀናችሁን ለማስተላለፍ በመገደዳችሁ በእኔ ላይ ስትፈርዱ በእራሳችሁ ላይ የፈረዳችሁ መሆናችሁን አላስተዋላችሁም ።

እኔ የተነሳሁት ከትክክለኛ ሕግና ከኅሊናችሁ ውጭ ለመፍረድ እንዳትገደዱ ለማድረግ ነበር ። በአጭሩ በእኔ ላይ ለመፍረድ የቸኮላችሁትን ያህል አሥርና አሥራ አምስት ዓመት በቀጠሮ የምታጉላሉትን የደሃውን ሕዝብ ጉዳይ እንደዚህ አፍጥናችሁ ብትመለከቱለትና ብትሸኙት ኖሮ የእኔ መነሳት ባላስፈለገም ነበር ። ከእናንተ ከዳኞቹና የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ እኔ ፍርድ ተቀባይ የዛሬ ወንጀለኛ የነገ ባለታሪክ ነኝ ። የእኔ ከዳኞቼ መካከል ለጊዜው በሕይወት መቆየትና ለእናንተ ፍርድ መብቃት የዘመኑን ፍርድ ለመጭው ትውልድ የሚሳይ ሆኗል ። ዋ.ዋ.ዋ. ለእናንተ ለገዥአችሁ ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃሣቤ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሳበት ጊዜ የሚወርድባችሁ መዓት የሚያሳቅቅ ይሆናል ። በተለይ የአጼ ኃ/ሥላሴ የግፍ መንግሥት ባለአደራዎች ሆነው ደሃውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲገሸልጡት ከነበሩት መኮንን ሐብተውልድና ገብረ ወልድ እንግዳ ወርቅን ከመሳሰሉት በመንፈስ የታወሩ ፣ በሥራ የኮሰሱ መኸገሮች መካከል ጥቂቶቹን ገለል ማድረጌን ሳስታውስና የተረፉትም ፍፃሜአቸውን በሚበድሉት በኢትዮጵያ ሕዝብ እጅ ላይ መውደቅ ሲሰማኝ ደስ ይለኛል ።”

መንግሥቱ ነዋይ በዚህ ንግግሩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያሉበትን ፍትህ አልባ የሆነውን የድኅነትና የውርደት ሕይወት ገልጿል ። ከዚህም አልፎ ዳኞች ከኅሊናቸውና ከትክክለኛ ሕግ ውጭ ተገደው እንዳይፈርዱ ጭምር ማመፁን ተናግሮ ለነፃ ፍርድ ቤት እምነት ቤዛ ሆኗል ። ዋ.ዋ. ለገዥዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ የተነሳሁበት ዓላማ ገብቶት የተነሳ ዕለት ይብላኝላችሁ በማለት እንደ ነብይ የሕዝቦች ዓመፃን አይቀሬነት ተናግሯል ። ያለውም አልቀረ ። የካቲት 1966 ዓ.ም. መጣ ። ይህ ከነፃ ኅሊና ፣ ከሕዝብ ፍቅር የመነጨ የአቅጣጫ ግልጽነት የእምነት ጽናትና ወደር የሌለው የጀግንነት ተግባር ዘላለም በኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለይም በአማራው ሕዝብ የትግል ታሪክ ሲታወስ የሚኖር ነው ።

ይህ ንግግር የሃገራችንን ውስብስብ የፖለቲካ ዕውነታ የሚተነትን ባለመሆኑ ፣ በተለይ ዛሬ የፖለቲካ አጀንዳ የሆነውን የብሄሮችን ብሄረሰቦች ጉዳይ ባለማንሳቱ በታሪክ ፊት ለሕዝቦች ነፃነት የተከፈለ



ታላቅ መስዋዕትነት መሆኑን አይሽረውም ። ታሪክ የራሱ ገደብ ያደረገበት አመጽ ነውና ሰውየው ! በአመፀበት ዘመን በነበረው ነባራዊ ሁኔታ ክልል መታየት ይኖርበታል ። ይህንን ስንል ግን የታኅሣሡ 1953 ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ ስለነበረው ብሔራዊ ጭቆና ባይተዋር ነበሩ ለማለት አይደለም ። ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው በቅርቡ የምዕራብ ሶማሌ የነፃነት ግንባር ተወካይ የመፈንቅለ መንግሥቱን ዋንኛ መሪ የሆነውን ገርማሜ ነዋይን አስመልክተው የፃፉትን ደብዳቤ ማየት ይቻላል ።

ከምዕራብ ሶማሊያ የነፃነት ግንባር ተወካይ የተፃፈው ፣ የድርጅቱን ማኅተም የያዘው ደብዳቤ “አጋዴንና ታላቁ ሰው ገርማሜ” በሚል ርዕስ ገርማሜ ነዋይ በአጋዴን አስተዳዳሪ በነበረበት ወቅት የሠራቸውን ሥራዎች በዝርዝር የሚያስቀምጥ ነው ። እነዚህ ሥራዎች አስተዳደርን የመሠረተ ልማት ግንባታን የፍትህ ሥርዓትን ሌሎችም የገርማሜ ነዋይ ሥራዎች ናቸው ። ከእነዚህ ውስጥ የአስተዳደር ሰዎችን በተመለከተ የነፃነት ግንባሩ ተወካይ ያሉትን እንይ ።

> “ገርማሜ ሕዝቡ በራሱ ሰዎች እንዲተዳደር እነዚህም ሰዎች የአካባቢው ተወላጅ ምሁራን መሆን አለባቸው የሚል አቋም ነበረው ። በዚህ አቋሙ መሠረት ንጉሠ ነገሥቱ በባላባትነት መጠሪያ ብቻ በሕዝቡ ላይ ያስቀመጧቸውን ወረዳና ምክትል ወረዳ ገዥዎች በእራሱ ውሣኔ በመሻር ከአውራጃ ጽ/ቤት ጀምሮ እስከታች ያለውን የአስተዳደር ሰንሰለት በአካባቢው ምሁራን በመተካት እስከ ንጉሠ ነገሥቱ ድረስ በአደገኛነቱ የተሰማውን እርምጃ ወስዷል ።”

የግንባሩ ተወካይ ፅሑፋቸውን ሲያጠቃልሉ ስለ ገርማሜ የሰጡት ታሪካዊ የምሥክርነት ቃል የአማራው ምሁር ለሕዝቦች ዕኩልነት የከፈለውን መስዋዕትነት ማንም ከታሪክ ማኅደር ሊፍቀው የማይችል መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ እንጠቅሰዋለን ።

“ከዚያ የአገርና የሕዝብ አሳቢነት መንፈሱ ጋር በዚህ ክልል ብዙም እንዲይቆይ ሁኔታዎች ያልፈቀዱለት ገርማሜ የለጦተ ዓላማውን ከግቡ ሳያደርስ ማለፉ በተለይ በእኛ የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝቦች መንፈስ ውስጥ ከፍተኛ ሃዘንን ፈጥሯል ። ምክንያቱም እኛ ከገርማሜ በፊትም ሆነ በኋላ የዚህን ሰው አምሳያ አላየንም።

እኛ የኢትዮጵያን ሶማሌዎችን እንደ ሙሉ የኢትዮጵያ ዜጋ እይቶ
አክብሮና ለሥራ ለልማት ያንሳሳን ገርማሜ ብቻ ነበር ።”

ዛሬ የመንግሥት መገናኛ ብዙሀን ስለ አማራው ገዥ መደብ
ታሪክ ብቻ በሚያወሩበት ወቅት ፣ ዛሬ የአማራው ሕዝብና ምሁር
ለፍትህ ፡ ለዲሞክራሲና ለሕዝቦች ዕኩልነት የከፈሉት ረጅም ዘመን
ያስቆጠረ መራራ የመስዋዕትነት ታሪክ አስታዋሽ አጥቶ የትም
በቀረበት ወቅት ፣ ዛሬ ከተለያዩ አቅጣጫዎች በሚሰነዘሩ ሚዛና
ቸውን ያልጠበቁ የታሪክ ሐተታዎች የተነሳ የአማራው ሕዝብና
ምሁር የራሱን የሆነውን ከገዢ መደቡ የተለየ ታሪክ እስከመጠ
ራጠር በደረሰበት ወቅት ፡ የማንባሩን ተወካይ ደብዳቤ የአማራው
ምሁራንና ሕዝብ በከፍተኛ አክብሮትና አድናቆት እንደሚያዩት
አንጠራጠርም ።

በመፈንቅለ መንግሥቱ የተሳተፉት ሲቢሎችና ወታደሮች
እየታደኑ አለቁ ። ግማሾቹም የጥይት እርሳስ በራሳቸው ተጐንጭ
ተው እንደ ጀግና አለፉ ። ከፊሎቹም ከወደቁበት አስከሬናቸው እየ
ተጐተተ መጥቶ በአደባባይ ተሰቀሉ ። መንግሥቱና ገርማሜ ሁለት
ወንድማማቾች እነ ወርቅነህ ገበየሁ ሌሎችም ዋናዎቹ የአመፁ
መሪዎች አማሮች ነበሩ ። አመፃቸው ግን የተካሄደው በኢትዮጵያ
ግፉአን ሕዝቦች ስም ነበር ። ይህ ለምን እንደሆነ ሌሎችንም የአ
ማራው ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች የትግል ታሪክ ከዳሰስን በኋላ
እንመለስበታለን ።

<u>የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ፣</u>

በዓለም ላይ እስከዛሬ ድረስ በተማሪዎች ፣ ለነፃነት ፣ ለዕኩል
ነት ፣ ለፍትህ ፡ በተደረጉ ትግሎች ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ቢኖር
የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ነበር ። ይህ የተማሪዎች እንቅስ
ቃሴ መጀመሪያ በዩንቨርስቲ ቀጥሎም በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ
ት/ቤቶች እንደ ሰደድ እሳት መቀጣጠል የጀመረው ከታኅሣሥ
1953 የመንፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ነበር ። መፈንቅለ
መንግሥቱ ዓይን ገላጭ ነበር ያልነውም ለዚህ ነው ።

የተማሪው እንቅስቃሴ ውሎ ባደረ ቁጥር የዘውድ ሥርዓቱን
ከሥር መሠረቱ የሚያናጉ ጥያቄዎች ማንሳት ጀመረ ። ሁላችንም
እንደምናስታውሰው በከፍተኛ ደረጃ ሲስተጋቡ የነበሩ ጥያቄ



ዎች “የመሬት ለአራሹ ፡ የብሔሮች ዕኩልነት ፡ የመናገር ፡ የመፃፍ
የመሰብሰብ ነፃነት ፡ የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች” በሙሉ
መከበር ነበሩ ።

ይህ የተማሪ እንቅስቃሴ በጣም የተጠናከረው በአዲስ አበባ
ከተማ በቀኃሥ ዩኒቨርስቲና በሁለተኛ ደረጃ ት ቤቶች ነበር ። ከዚህ
ውጭ የወሎው ወ/ሮ ስሂን ፣ የጐንደሩ አጼ ፋሲል ፡ የናዝሬቱ ገላ
ውዲዮስ ፣ የደብረዘይቱ ልብነ ድንግል የሐረሩ ልዑል መኮንን የመ
ሳሰሉ ት/ቤቶች በተማሪው እንቅስቃሴ ገናና ታሪክ ነበራቸው ።
በጊዜው በዩንቨርስቲው ሆነ በእነዚህ ት ቤቶች የሚማሩ ተማሪ
ዎች ከተለያዩ ብሄር ብሄረሰብ የተውጣጡ ቢሆንም ፡ አብዛኛው
ተማሪ ከአማራ ቤተሰብ የመጣ እንደነበር ጥርጥር የለንም ። በደ
ቡብ ኢትዮጵያ በነበሩት ትምህርት ቤቶች ሳይቀር በዳኝነት በአ
ስተዳደርነት በወታደርነትና በሌሎችም የመንግሥት ሥራዎች
ከመሃል አገር የተላኩትን ሠራተኞችንና ቀደም ብለው በነፍጠ
ኝነት በመሄድ በደቡብ የሠፈሩ ባለ መሬት ልጆች ጨምሮ የአማ
ራው ተማሪ ቁጥር በጣም በርካታ ነበር ። ይህ ከፍተኛ የአማራ
ተማሪዎች ተዋጽኦ የነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ያነሳቸው
መፈክሮች በዋንኛነት የአማራውን ነገሥታትና መሣፍንት ሥር
ዓት የሚጠራርጉ በቦታውም የሕዝቦችን እኩልነት ፡ ነፃነት ፡ የጋራ
ብልፅግና ጉዳና የሚያሳዩ ነበሩ ። የመሬት ለአራሹ ጥያቄን ብቻ
ብንወስድ ሰሜን ከሚኖረው አማራ አርሶ አደር ይበልጥ ትልቅ
ትርጉም የነበረው ለደቡብ ኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ነበር ። የአማ
ራው መሣፍንትና መኳንንት ሠፋፊ መሬቶችን ከተለያዩ ብሄር
ሕዝቦች ቀምተው አገሬውን አገር አልባ በማድረግ በሚሊዮን
የሚቆጠሩ ሕዝቦችን ከባርነት ባልተሻለ የገባርነት ሕይወት ውስጥ
የሚያማቅቁት በዋንኛነት በደቡብ ኢትዮጵያ በመሆኑ የመሬት
ለአራሹ መፈክር በቀጥታ ያነጣጠረው በእነዚህ መንግሥቱ ነዋይ
በመጨረሻ እስትንፋሱ በመንፈስ የታወሩ ፣ በሥራ የኮሰሱ ብሎ
በኮነናቸው ቀሪ መኸገሮች ላይ ነበር ። የመሬት ላራሹ ጥያቄን
አንስተው መራራ ትግል ካደረጉትና በትግሉም ከወደቁት መሃል
ቁጥራቸው የበዛ የባለመሬት ልጆች እንደነበሩበት ስናስታውስ
የአማራው ምሁር ለሁሉም ሕዝቦች ብልፅግናና እኩልነት ሲል
የቤተሰቡንና የራሱን ጠባብ ጥቅም ተፃር መቆም የሚችል አድማ
ሳዊ የሰብዕና መሠረት የነበረው ምሁር መሆኑን ያሳየናል ።

በብሄሮች እኩልነትና በብሄሮች የራስን ዕድል በራስ የመወ

ሰን ጥያቄም ላይ እንደተራራ የገዘፈ ታሪክ ያላቸው የአማራ ምሁራን ወድቀዋል ። እንዲህ እንደዛሬው የተጨቆኑ ብሄር ሕዝቦች ተደራጅተው በአደባባይ ስለመብታቸው የመከራከር ባሕል ባል ነበረበት በዚያ እስከፊ የጨለማ ዘመን የጭቁን ብሄሮችን ቀንበር እንደተሸከሙ መስዋዕትነት ከተቀበሉ የአማራ ምሁራን መሃከል አንዱን ዋለልኝ መኮንን ብቻ መጥቀስ ይበቃል ።

ከዛሬ ሃያ አራት ዓመት በፊት በብሔሮች የዕኩልነት ጥያቄ ላይ የጠራ አመለካከት ላልነበረው የዩኒቨርስቲ ተማሪ ፣ ዋለልኝ ስለ ጉዳዩ በሠፊው ካተተበት "በብሔር ጥያቄ ላይ" በሚል ርዕስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከፃፈው ጽሑፍ ጥቂቱን እናስታውስ ። በተማሪው መሃከል ለተለያዩ የሕዝቦች ዓመፅ ይሰጥ የነበረውን አድሎአዊ ድጋፍ በሙንቀፍ እንዲህ ብሎ ነበር ።

"ጭቆናን በሙቃወም ለሚነሱ ዓመጻዎች አንድ ዓይነት አመለካከት ሊኖረን ይገባል ። የጉጃም ሕዝብ ሲያምፅ ማጨብጨብ ፡ የባሌና የኤርትራ ሕዝቦች ሲያምፁ ዝም ማለት ፣ የመንግሥቱ ነዋይን ሙፈንቅለ ሙንግሥት ሙከራ ማወደስ ነገር ግን የታደሰ ብሩን ሙከራ መንቀፍ ምን ማለት ነው ? አማሮች ሲያምፁ ብቻ መደገፍ አማራው የሚሙራው አመፅ ከሆነ ማወደስ ፣ ኦሮሞውና ኤርትራዊ ከሆነ ግን የማይዋጥልን ለምንድንነው ? ለሌሎች ሕዝቦች ያለንን ብሔራዊ ንቀት ከማሳየት ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም ። ለፀረ ጭቆና እስከቆምን ድረስ ጭቆናን ተቃውሞ ማንም የትም ይነሳ ሁሉም ልንደግፈው ይገባል ። እያንዳንዱ ፀረ ጭቆና አመፅ የኢትዮጵያን ሕዝቦች የነፃነት ቀን የሚያቀርብ እርምጃ ነውና ።"

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በኤርትራ ይካሄድ የነበረውን ጦርነት ተቃውሞ ስለ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት መናገር ልክ በደርግ ጊዜ እንደነበረው አሁንም እንዳልጠፋው በአረብ ዶላር የተገዛ ፡ የኢትዮጵያ ጠላቶች ቅጥረኛ የሚል ስያሜ ያሰጥ ነበር ። በዚህ ጉዳይ ላይ ንጉሡ ልክ እንደደርግ በጣም ስሱ ነበሩና የሴኩሪቲ ኃይላቸው ይበልጡኑ የሚያተኩረው እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን በሚያነሱ ግለሰቦች ላይ ነበር ። ዋለልኝ ይህንን ጠንቅቆ እያወቀ ነበር ይህን የፃፈው ።

"የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ከየትም ሊጀምር ይችላል ። ከደቡብ ከሰሜን ፡ ከምሥራቅ ፡ ከምዕራብ ፣ ሲፈልግም ተገንጣይ ሆኖ ሊነሳ ይችላል ። ከየትም ይጀምር የፈለገውን ዓላማ ይዞ ይነሳ



ፀረ ጭቆና ትግል እስከሆነ ድረስ ከሌሎች ሕዝቦች ፀረ ጭቆና ትግል ጋር መቀናጀቱ አይቀርም ። የሁሉም ብሄር ሕዝቦች የዘመናት የድኅነት ሕይወት ተመሳሳይነት ከልዩነታቸው የበለጠ ስለሆነ ፣ ሁሉም ሕዝቦች በተባበሩት ጠላቶቻቸው ፊት በኅብረት መቆማቸው አይቀርም ።"

ስለ ብሔርና የኃይማኖት ጭቆና ሲያስረዳ ተማሪውን እንዲህ ብሎት ነበር ።

"አሁንም የሚነገረን ሃገሪቱ የክርሲቲያን ደሴት እንደሆነች ነው ። በዓይናችን የምናያቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ እስልምናና የሌሎች ኃይማኖት ተከታዮች የኢትዮጵያ ሕዝቦችስ ? በሃገሪቱ ያለ ቋንቋ አማርኛ ብቻ እንደሆነ ይነገራል ። በዓለም አቀፍና በሃገር ውስጥ ትርኢቶች የሀገር ባህል ልብስ ተብሎ የሚቀርበው የአማራውና የትግሬው ልብስ ነው ። የሃገር ባህል ምግብ ተብሎ የሚቀርበው እንጀራና ዶሮ የአማራው ምግብ ነው ። የሃገሪቷ ታሪክ ሆኖ የሚቀርበው የሰሜን ኢትዮጵያ የአቢሲኒያ ታሪክ ብቻ ነው ። ሌሎች ሕዝቦችስ በኢትዮጵያ የሉም ?ቋንቋ ባሕልና ታሪክ የላቸውም ? "

ይህ ነበር የዋለልኝ አንደበት ። ኢትዮጵያ የብሔሮች እሥር ቤት መሆኗን ለተማሪው ያሳየበት ። ዋለልኝና ጓደኞቹ በእንዲህ ዓይነቱ ትግል ነበር ተማሪው በኢትዮጵያ የብሔሮችን ጭቆና እንዲረዳና ለብሔራዊ ዕኩልነት እንዲነሳ ያደረጉት ። ምንም እንኳን እንደ ዋለልኝ ዓይነቶቹ ግንባር ቀደም ታጋዮች የሌሎች ብሔሮች መጨቆን ማለት የአማራው ሕዝብ መጨቆን እንደሆነ ጠንቅቀው የሚያውቁ ቢሆኑም ፣ በዘመኑ ለነበሩ በርካታ አማራ ተማሪዎች ከመሬት ለአራሹ ጥያቄ ይበልጥ የብሔሮች የዕኩልነት ጥያቄ የሚመለከተው አማራ ያልሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነ አድርጎ መገመቱ አልቀረም ። ያም ሆኖ በነዋለልኝ ጥረት በሺዎች የሚቆጠሩ የአማራው ምሁራን ጥያቄውን ጥያቄያቸው አድርገው በሕዝቦች የዕኩልነት ትግል ከሁሉም ቀድመው ተሰለፉ ። ዋለልኝም ይህን እምነቱን እንደያዘ በንጉሡ ሴኩሪቲዎች ተገደለ ።

## ከ1966 የካቲትና ከየካቲት በኋላ ፣

መንግሥቱ ንዋይ በ1953 ዓ.ም. ለገዥዎች የሰጠው ማስጠንቀቂያ ጊዜውን ጠብቆ በ1966 የካቲት ደረሰ ። የኢትዮጵያ ተማሪዎች የመሬት ለአራሹ ፡ የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ፣ የዲሞክራሲ መብቶች መከበር ጥያቄ ከተማሪዎቹ አልፎ የሁሉም ሕዝቦች ጥያቄ ሆነ ። የረጅም የትግል ዕድሜ የነበራቸው የሠራተኞችና የመምህራን ማኅበራት ከተማሪው ጐን ተሰለፉ ። ሕዝቡ በገዥዎች ላይ አመፀ ። በኢትዮጵያ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የኖረው የዘውድ ሥርዓት ተመንገለ ። በዚህ በየካቲት 1966 ዓ.ም. አመፅ ውስጥ በተደራጀ መልኩ ከፍተኛ ተፅዕኖ ባደረጉ የሙያ ማኅበራት ውስጥ ከነበሩ አባላትና የአመራር አካላት መሃከል በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አማሮች እንደነበሩ ማስታወስ ተገቢ ይመስለናል ።

ከ1966 በኋላም ደርግ በጠመንጃ አፈሙዝ የሕዝቦችን ሥልጣን ከቀማ በኋላ የደርግን አምባገነን መንግሥት በመቃወም በዋንኛነት በሚታወቀው በኢሀአፓ (የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ) ውስጥ እጅግ በጣም በርካታ አማሮች የተሳተፉበት እንደነበር እናውቃለን ። ኢሀአፓ የተማሪው እንቅስቃሴ ቀጥተኛ ውጤት ስለነበር በነሐሴ ወር 1967 ዓ.ም. ባወጣው ፕሮግራሙ ላይ ተማሪውና ምሁሩ ለዘመናት የታገለላቸውን የመሬት ለአራሹ ፣ የብሔሮችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል ያልተገደበ የሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ መብት መከበርን በማያሻማ ቋንቋ በፕሮግራሙ የቀረፀ ድርጅት ነበር ። በኢሀአፓ ውስጥ በሺዎች ተሰልፈው በሺዎቻ ያለቁት ውድና መተኪያ የሌላቸው የአማራ ልጆች ኢሀአፓን የተቀበሉት በጭፍን ሳይሆን ፡ በፕሮግራሙ ላሰፈራቸው ብዙ ለደሙባቸው ለታሠሩባቸው ፡ ለሞቱባቸው የሕዝብ ጥያቄዎች ነበር ። ዛሬ ይህ ድርጅት በአመራሩ ጥፋት ብትንትኑ ወጥቶ ቀሪውም በስደት ፕሮግራሙን ቀይሮ ቢገኝ ይህንን ሳያውቁ በረፋዳው የሕዝቦች የትግል ወቅት ተወዳዳሪ በሌለው የሕዝቦች አቸናፊነት እምነት ተሞልተው እሥራትን ግርፋትን ሞትን በፅናት ተቀብለው ያለፉትን ሰማዕታት ክብር የሚቀንሰው አይሆንም ። ባለንበት ወቅት በሥልጣን ላይ ያሉ ድርጅቶች ይህንን በማንኛውም መመዘኛ ራስን መቆጠብ ያልታዩበትን የአማራ ዲሞክራቲክ ምሁራን ሕዝባዊ የተጋድሎ ታሪክ ማድበስበሳቸው የሚያ



ስተዛዘብ ሆኗል ። በዘመናችን ያለው የአማራ ምሁርና ወጣት የኔ ነው የሚለው የራሱ ታሪክ እንዲያጣና ባዶነት እንዲሰማው በማድረግ እየተፈጠረ ያለው ባይታወርነት፥ በአማራው ሕዝብ የወደፊት ዕጣ ላይ ለሚያስከትለው ጉዳት በታሪክ ፊት ተጠያቂነትን ማምጣቱ አይቀርም ።

## ከኢሀአፓ ውድቀት በኋላ ፡

በአስከፊው የቀይ ሽብር ጭፍጨፋ በሺዎች የሚቆጠሩ ታጋይ አማራ ምሁራን አለቁ ። ከአንድ ዓመት በፊት በተደረሰበት ቆጠራ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ በቀይ ሽብር ያለቀው የሕዝብ ቁጥር 54.000 ደርሷል ። ከዚህ ውስጥ የከተማውን የአማራ ሕዝብ ብዛትና የአማራውን ምሁር ሠፊ የፖለቲካ ተሳትፎ ግምት ውስጥ በማስገባት ጭፍጨፋው ከፉኛ የአማራውን ሕዝብ እንደጐዳ ማየት ይቻላል ። በጐጃም ፣ በወሎ ፡ በጐንደር በተለያዩ ከተሞችም ቁጥሩ በጣም ብዛት ያለው ወጣትና ምሁር በቀይ ሽብር ረግፏል ።

ከግድያ የተረፈው ፣ ከአሰቃቂ ግርፋት በኋላ በየእሥር ቤቱ ታጐረ ። ከሞትና እሥራት ያመለጠውም እንደ አሸዋ በዓለም ዙሪያ በስደት ተበተነ ። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለዕኩልነትና ለዲሞክራሲ ባደረጉት የዘመናት ትግል ጉልህና ሠፊ ሚና የነበረው የአማራ ዲሞክራሲያዊ ምሁር ከኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ጠፋ ። አጼ ኃይለ ሥላሴና መኳንንቶቻቸው ሞክረውት ያቃታቸውን ምኞት ደርጉ ተዋጣለት ።

ይሁንና ከዚህ አስከፊ የልጆቹ እልቂት በኋላም የአማራው ሕዝብ እጁን አጣጥፎ አልተኛም ። ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በማበር የደርግን ጭቆናና ብዝበዛ መቃወሙን ቀጠለ ። የደርግን መንግሥት ለማንበርከክ በተደረገው መራራ ጦርነት በሕይወት በጥሪቱ ድርሻውን ከፍሏል ። በደርግ መቃብር ላይም የአማራው ውድ ልጆች በሺዎች የወደቁለትን የዲሞክራሲና የሕዝቦች ዕኩልነት መብቶች መከበር ሌላው ቢቀር በመንግሥት ደረጃ ሕግ እንዲሆን አስችሏል ።

የአማራው ታሪክ የገዥ መደቡ ታሪክ ብቻ አይደለም ። በእርግጥ እስከ ዛሬ የታሪክ ፀሐፊዎች የሚዘግቡት ታሪክ የነገሥታቱና የመሣፍንቱን ገድል ብቻ ነው ። በመሆኑም የአማራው ታሪክ ሲወሳ በብዙዎቹ ኅሊና የሚታወሰው ይሄው የመኳንንቱ ታሪክ ብቻ ነው ። ዕውነታው ግን ይህ እንዳልሆነ በመጠኑም ቢሆን ለማሳየት ሞክረናል ። የታሪክ ፀሐፊዎች አይደለንምና የአማራውን ሕዝብ የነፃነት ፣

የፍትህ ፡ የዲሞክራሲ ፡ የተጋድሎ ታሪክ በስፋት አስውበንና አድም
ቀን ለማቅረብ አልቻልንም ። ይህ ታሪክ ቢጠልቁት የማያልቅ የገድ
ልና የጀግንነት ጥልቅ የታሪክ ኩሬ ነው ። ከእዚህ ኩሬ እየጠለቁ
ሁላችንንም ማጠጣት የአማራው ታሪክ ተመራማሪዎች ሥራ ይሆ
ናል ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የዚህ ፅሁፍ ዓላማ የአማራውን የትግል ታሪክ ለመዘርዘር አይ
ደለም ። ታሪክን መዘርዘር ያስፈለገው አማራው በትግል ታሪኩ ያነ
ሳቸው ጥያቄዎች ምን እንደነበሩና በምንስ መልክ እንደታገለ ለማሳ
የት ነው ። አማራው በትግሉ ያነሳቸው ጥያቄዎች ከአማራው ቀጥተኛ
ጥቅም በላይ የተሻገሩ የሌሎችም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥያቄዎች
ጭምር ነው ። ለእነዚህ ጥያቄዎች የታገለውም እራሱን በአማራነት
በማደራጀት እንዳልነበረ አይተናል ። ለምን የሚለውን ጥያቄ ቃል
በገባነው መሠረት እዚህ ላይ በአጭሩ ለመመለስ እንሞክራለን ።

የአማራው ዲሞክራሲያዊ ኃይል በአማራው አካባቢ ብቻ የታ
ጠረ ጭቆና አይታየውም ነበር ። እንደሌሎች ብሔር ሕዝቦች የአካ
ባቢውን ጭቆና ልዩ አድርጐ በማጉላት የሚያሳይ የቋንቋና የባህል
ጭቆና በአማራው አካባቢ አልነበረም ። የሚታየው ጭቆና ሁሉንም
የኢትዮጵያ ሕዝቦች በጋራ የሚያማቅቅ ጭቆና ነበር ። በሌሎች ሕዝቦች
ላይ ከሚደርሰው ጭቆና የተለየ ነገር በአማራነቱ የመጣበት ባለ
መሆኑ ፡ የአማራ ድርጅት እንዲያቆም የሚገፋፋው ሁኔታ አልመ
ጣም ። አጼ ኃይለ ሥላሴ ሆኑ አምባገነኑ ደርግ ከናቅፋ እስከ ሐርጌሳ
የሚገኘውን ሕዝብ የሚገዙት በአንድ አይነት መንገድ ነበር ። ይህ
ሕዝብ በሰላሙ ቀን ረሃብና በሽታ ይፈጀዋል ። ከፎቶት ሲያምፅ
ቦንብ ይጥርድበታል ። ይህ ዕጣ ለአማራውም ፣ ለኦሮሞውም ፣ ለትግ
ሬውም ፡ ለአፋሩም ፡ ወዘተ . . . ለሁሉም ሕዝቦች አንድ ዓይነት ነበር።
ሌሎች ሕዝቦች በቋንቋቸው መታፈን ፣ በባህላቸው መርከስ ለሚደር
ስባቸው አፈና ቀደም ብለን እንዳየነው የአማራው ዲሞክራሲያዊ
ኃይል ከጐናቸው ቆሞ በአንድ ላይ መታገል የማይቻልበት ምክን
ያት አልታየውም ። የአማራው ዲሞክራሲያዊ ኃይል በሃገሪቱ ገዥ
ዎች ለሚያደርሱት አድማሳዊ ብዝበዛና አፈና ተፈጥሮአዊ ምላሹ
አድማሳዊ የሆነ ፀረ ብዝበዛና ፀረ አፈና ትግል ነው ። ለአማራው ዲሞ
ክራሲያዊ ምሁር ለሁሉም ሕዝቦች ነፃነት መታገልና መስዋዕትነት
መክፈልን የመሰለ ክቡር ነገር አልነበረም ። በመሆኑም ስለ አፋር ፣



ስለ ጋምቤላ ፡ ስለ ኤርትራ ፣ ስለ ኦሮም ወዘተ . . . . ሕዝቦች መታገልና
መስዋት በማያገባው ገብቶ በከንቱ መባከን አድርጐ አላየውም ።
በአማራው ሕዝብና በራሱ ላይ ለሚደርሰው ግፍ ተጠያቂዎች የአማ
ራውን ቋንቋ የሚናገሩ ባሕሉን የተላበሱ ገዥዎች መሆናቸውን ጠንቅቆ
ስለሚያውቅ የሕዝቦች የዲሞክራሲ የፍትህ ፡ የብልፅግናና የሰላም ጥያቄ
ቋንቋና ባሕል ስለተከበረ ብቻ እንደማይገኝ ከተመክሮው ቀልጥፎ የተ
ረዳ ኃይል ነበር ። በዚህ ግንዛቤ ላይ ቆሞ ሁሉም የኢትዮጵያ ግፉአን
ሕዝቦች በቋንቋ ፣ በባሕል ፡ በኃይማኖት ያላቸውን ልዩነት እንደያዙ
በጋራ በሁሉም ጨቋኞች ላይ እንዲነሱ ጥሪ ማድረጉ የፈለቀበት ኅብረተ
ሰብ ነባራዊ ዕውነታ ያስተማረው ነበር ። ይህ አካሄዱ ትናንትም ሆነ ዛሬ
ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የዘለቄታ ጥቅም ወሣኝ በመሆኑ ፡ በትክክለኛነቱ
ላይ ለአንድ ሰኮንድም መጠራጠር የለበትም። ባለንበት ወቅት መመለስ
ያለበት ጉዳይ ቢኖር እንዴት ተግባራዊ ይሆናል የሚለው ብቻ ነው። ከዚ
ህ ውጭ አማራው ባለፉት የትግል ዘመናት የአማራ ድርጅት ለብ
ቻው አለማቆሙ ትግሉን ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በአንድነት ለማራ
መድ መሞከሩ ፣ አንድ አንድ ኃይሎች ሊያሳምኑን እንዲሚሞክሩት
በኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔረሰቦች መኖራቸውን በመካድ ኢትዮጵያ
የአንድ ሕዝብ አገር ብቻ አድርጐ ከሚያይ የገዥ መደብ
ትምክህተኛ አመለካከት የመነጨ አልነበረም ። ይህ ላለመሆኑ የብሔ
ሮችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ጥያቄ በከፍተኛ ደረጃ
እንስተው የወደቁ የአማራው ሕዝብ ልጆች በሺዎች የሚቆጠሩ እን
ደሆኑ ስለምናውቅ ነው ።

ዛሬ ታሪክ የራሱን ጉዞ ተጉዞ አዲስ ነባራዊ ዕውነታ ይዞ መጥ
ቷል ። ዛሬ ናቅፋ የለም ። የአጋዴን ጭቆናችም ገርማሚ ነዋይን በታሪ
ካቸው ያስታውሱት እንጂ ሌላ ገርማሚ ላኩልን አላሉንም ።
ላራሳቸው እራሳቸው እያወቁበት ነው ። ከዘመናት በፊት የአማራው
ዲሞክራሲያዊ ኃይል በትግል አብረውት እንዲነሱ ጥሪ ያደረገላቸው
ሕዝቦች የየራሳቸውን ብሔራዊ ድርጅቶች አቁሙዋል ። ቀደም ብለን
እንዳየነውም በብሔር መደራጀት በኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ጠንካራ
የብሔረተኝነት ስሜት ላይ የተመሠረተ እንጂ እንደ አንድ ቦድኖች
እንደሚሉት እፍ ቢሉት የሚጠፋ የዘመኑ ፋሽን ባለመሆኑ ከዚህ
በኋላ የአማራው ዲሞክራሲያዊ ኃይል የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለፍትህ
ለዕኩልነት ፡ ከኋላቀርነት ለማላቀቅ ፣ ለአንድነት በሚያደርጉት ትግል
ድርሻውን የሚወጣው እንደ አማራ በመደራጀት ብቻ ነው ። ይሁንና
አማራው ፡ ይህንን በማድረጉ ከዚህ በፊት ከነበረው የትግል ልምድና

አደረጃጀት ጋር የሚቀረን እንዲያውም አልፎ ተርፎ ከፍተኛ አደጋ ሳዊ፡መርሆችን ለቆ ትምክተኛ ወይንም ጠባብ ብሔረተኝነት እንዲ ጠናወተው ልታደርጉት ነው የሚሉን አልታጡም ። ለእነዚህ መል ሳችን ሁለት ነው ። የመጀመሪያው ደግመን ደጋግመን ያስቀመጥነ ውን የሣገሪቷን የፖለቲካ አጀንዳና አደረጃጀት በቅጡ እንዲመረምሩ መጠየቅ ነው ። ሌላው ከዚህ ቀደም በሺዎች የሚቆጠሩ የአማራ ዲሞክራቶች የወደቁበትን የሰብዕና የዕኩልነት ለሁሉም የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የጋራ ዕድገትና አንድነት መርሆችን አጥብቀን እስከ ያዝን በአማራነታችንም ስንሰባሰብ እነዚህን መርሆች መሠረት እስካደረግን የሚያሳስበን አንዳችም ነገር አይኖርም ። ባለንበት ሁኔታ የአማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጊዜ የማይሽረውን አኩሪ ሕዝባዊ ታሪካቸውን አቅበው የአማራውን ሕዝብ የመብትና የነፃነት ባለቤት ፣ የሰላምና የብልፅግና ጌታ ለማድረግ በዋንኛነት በመሥራት ብቻ ነው ፣ ከአማራውም ሕዝብ ሆነ ከተቀሩት የኢትዮጵየ ሕዝቦች የሚጠበቅባቸውን ግዴታ መወጣት የሚችሉት ። ይህንን አዲስ ዕው ነታ አለማጤን ፡ እምነትን በተግባር ለመተርጐም በማያስችል ከወሬ ከማያልፍ የተበተነ ተራ የፍትህ ፣ የዴሞክራሲ ፣ የዕኩልነትና የአን ንድነት ቱልቱላ ሆኖ ዓየር ላይ መቅረትን ያስከትላል ። ከዚህ በላይ በአንድ ዘመን በሺዎች የሚቆጠሩ ተራራ የሚያነቃንቅ ጽኑ ሕዝባዊ እምነት የነበራቸው ዴሞክራቶች ያፈራው የአማራ ሕዝብ ዛሬ የሁላ ችንንም ዕውቀት ጉልበትና መስዋዕትነት በሚጠይቅበት ወቅት የተለያዩ ምክንያቶች እያቀረብን ፣ በምኞት ፈረስ እየጋለብን ከዳር ቆመን ብናየው ድርጊታችን በታሪክ ፊት የሚያስወቅሰን ይሆ ናል ። የአማራውንም ሆነ ሌሎችንም የኢትዮጵያ ሕዝቦች የቀን ጅቦች ሲሳይ ማድረጋችን አይቀርም ።



ምዕራፍ 6

## አዲሱ ዕውነታና የአማራው ሕዝብ የመከልና ጥያቄ

### አዲሱ ዕውነታ ምንድን ነው?

አዲሱ ዕውነታ ቀደም ብለን እንዳየነው በኢትዮጵያ የፖለቲካ አጀንዳው የብሔሮች አጀንዳ መሆኑ ነው ። የፖለቲካ አደረጃጀቱም በብሔር ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው ። ሕዝቦች በኢኮኖሚና በማኅ በራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፉት በየብሔራዊ ድርጅቶቻቸው አማካይነት ነው ። በዙሪያችን እነዚህን እንቅስቃሴዎች በማየት ከዚህ ቀደም በግል ጠይቀነው የማናውቀውን የራሳችንን ብሔር ማን ነት እንድንጠይቅ ያደረገ ዕውነታ ነው ። አማራነታችንን እንድንቀ በል ፡ አማራነት እንደ ሌሎች ብሔሮች ብሔረተኝነት በግልፅ ባይታ ይም የጠፋና ያልነበረ እንዳልሆነ ለማየት ያበቃን ነው ። በአማራነታ ችን አለመሰባሰብ በግለሰብ ደረጃ ይሁን እንደ ሕዝብ ሊያመጣብን የሚችለውን ጉዳት ገና ከወዲሁ መገንዘብ የጀመርንበት ነው ። የአማ ራውን መሰባሰብና የአማራው ብሔረተኝነት ከሌሎች ሕዝቦች ብሔረ ተኝነት የሚለየው ምን እንደሆነ የዚህ የአማራ ብሔረተኝነት ችግ ሮች ምን እንደሚመስሉ ያየንበት ዕውነታ ነው ። የአማራ ሕዝብ እንደ ሌሎች ሕዝቦች ጠንካራ የፖለቲካ ፣ የልማትና ማኅበራዊ ድርጅቶች ለማቆም እንዳይችል እንቅፋት የሆኑበትን የአመለካከት ችግሮች እን ድንፈትሽ ያስገደደ ነው ። ይህ ዕውነታ ቢመኙት የማይጠፋ ፣ እፍ ቢሉት ብን የማይል ዕውነታ ነው ።

### የአማራውን ሕዝብ እንወክላለን ማለት ምን ማለት ነው?

እስካለንበት ወቅት በይፋ የአማራውን ሕዝብ እንወክላለን ያሉ ሁለት ድርጅቶች አሉ ። አንዱ ኢ.ህ.ዴን (የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ) ሌላው መአህድ (የመላው አማራ ሕዝብ ድር ጅት) ናቸው ። እነዚህ ድርጅቶች የአማራውን ሕዝብ ለምን? እንዴት እንደሚወክሉ ያቀረቧቸው ጥናቶች ፣ ፕሮግራሞች የሚያደርጓቸው ተግ

ባራዊ እንቅስቃሴዎች ፣ እንደ ሌሎች የብሔር ድርጅቶች ፣ የሚታይ ባለመሆኑ በድርጅቶቹ ላይ ለጊዜው አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበናል ። በተለይ በአሁኑ ጊዜ የአማራው ሕዝብ በተለይ ምሁሩ በአማራነትና በብሔረተኝነት ጥያቄዎች ላይ ያሉትን ችግሮች በስፋት ተወያይቶ ወደ አንድ የጠራ አመለካከት ባልመጣበት ወቅት በእነዚህ ድርጅቶች ላይ አስቀድመን አስተያየት ማሳረፍ አፍራሽ ሚና መጫወት ይሆናል የሚል እምነት አለን ። ይሁንና አንድ ድርጅት የአማራውን ሕዝብ በፖለቲካ ድርጅትነት እወክላለሁ ለማለት ማሟላት የሚገባውን ጉዳዮች በአጭሩ በማቅረብ ፣ የአማራው ሕዝብ እነዚህን ድርጅቶች፣ ድርጅቶቹም እራሳቸውን እንዲፈትሹ ለማድረግ እንሞክራለን ።

ከሁሉም በፊት የዚህ ዓይነቱ ውክልና አማራነትን በሙሉ እምነትና ስሜት መቀበልን ይጠይቃል ። የአማራ ሕዝብ ማለት የአንድ ብሔር ሕዝብ ማለት መሆኑን ፣ የአማራ ብሔረተኝነትን ሕያውነት ፣ ብሔረተኝነቱ የሚገለፅባቸው ሁለንተናዊ መልኮችን ጠንቅቆ ማወቅን ይጠይቃል ። ይህ ደግሞ የአማራው ሕዝብ እንደ ሕዝብ መታወቅ ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ ሕዝቡ ያለፈባቸውን የታሪክ ሂደቶችና እነዚህም ከዛሬ ሕይወቱ ጋር ያላቸውን ተዛማጅነት መመርመርን ይጨምራል ። ሕዝቡ በታሪኩ ለነፃነቱና ለክብሩ የሚሰጠውን ክብደት መገንዘብ ይጠይቃል ።

የአማራው ሕዝብ ባለፈ ታሪኩ ብቻ የሚገለፅ ባለመሆኑ ዛሬ የሚገኝበትን ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወቱ በዝርዝር ሊታወቅ ይገባል ። የሕዝቡ ቁጥር በዕድሜ ፣ በጾታ ፣ በተለያዩ የእምነት ተከታይነቱ የጋብቻ የቤተሰብ ማኅበራዊ ባህሉ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በምን ሥራ ላይ እንደተሰማሩ እንዴት እንደሚኖሩ ፣ በትምህርት ፣ በጤና በሌሎችም ማኅበራዊ አገልግሎቶችና በንግድ ፣ በኢንዱስትሪ የደረሰበት ደረጃ ፣ የመገናኛ አገልግሎቶች መጠን የክልሉ ስፋት የመሬት አቀማመጥ የተፈጥሮ ሐብት የዓየር ጠባይ ፣ የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል የሕዝቡና የባለሐብቶች የካፒታል አቅም ፣ ወዘተ. . . መታወቅ አለበት ። የሕዝቡን ባህልና ወግ ከእነዚህ መሃከል በጎና ጐጂ ጐኖች ያላቸውን ማጤን ይገባል ።

በፖለቲካ መስኩም የአማራው ሕዝብ በታሪኩ ያነሳቸው የፖለቲካ ጥያቄዎች ምን ነበሩ? በምን ዓይነት የአስተዳደርና የፍትህ ሥርዓቶች አልፏል ። የሕዝቡ የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እያያዝ



በእነዚህ ሥርዓቶች ምን ይመስል ነበር? ዛሬስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የሚሉትን ጥያቄዎች አንስቶ መመለስ አስፈላጊ ነው ።

ከዚህ በተጨማሪ የአማራው ሕዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የተለያዩ ሕዝቦች ጋር በአንድነት የሚኖር በመሆኑ ፣ ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር ያለው ትስስር ምን እንደሚመስል ማወቅ ይጠይቃል ። የአማራው ሕዝብ ለሌሎች ሕዝቦች ያለውን አመለካከት ሌሎችም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለአማራው ሕዝብ ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ያሻል ። የአማራው ሕዝብ ከሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ይበልጥ ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ በርካታ የብሔሩ አባላት ያሉት ስለሆነ ፣ በእነዚህ የተለያዩ ክልሎች ስለሚኖሩ አማሮች ብዛት አኗኗር ሥራ ፣ ወዘተ. . . ከክልሉ ሕዝቦች ጋር ስለአላቸው ግንኙነት ማወቅ ይኖርበታል ።

የአማራው ሕዝብ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በሚጋራው የማዕከላዊ መንግሥት ውስጥ ሊኖረው ስለሚገባው ውክልና ፣ የማዕከላዊ መንግሥት ሊከተላቸው ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን የአማራውን ሕዝብ ፍላጐት የሚያንፀባርቁ የፖለቲካ የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎችን አንጥሮ ማስቀመጥ ይጠይቃል ።

በኢትዮጵያ ከሚገኙ የተለያዩ ሕዝቦች ፣ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችሉ ከአማራው ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጐቶችና እምነቶች የመነጩ መርሆችን በግልፅ ማወቅ ይገባል ።

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ነጥቦች የአማራውን ሕዝብ ለመወከል ድርጅቶች በግልፅነት ሊያስቀምጧቸው የሚገቡ ናቸው ። ይህንን መሥራት ግን በእራሱ ውክልናን አያስገኝም ። በእዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ላይ ተመሥርቶ በግልፅና በማያሻማ ቋንቋ የአማራውን ሕዝብ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፕሮግራም መንደፍ ይጠይቃል ። ይህ ፕሮግራም የአማራው ሕዝብ የሚገኝበትን ነባራዊ ዕውነታ መሠረት በማድረግ በእዚህ ዕውነታ ውስጥ ያሉ መሠረታዊ ችግሮችን በማንጠር በአጭርና በረጅም ጊዜ ሊወሰዱ የሚገባቸውን መፍትሄዎችን የአጭርና የረጅም ጊዜ ግቦችን ማስቀመጥ አለበት ። የአማራው ሕዝብ ዘጠና በመቶ በገጠር የሚኖር አርሶ አደር በመሆኑ ፣ የአማራውን ሕዝብ እወክላለሁ ለማለት የማንኛውም ድርጅት ፕሮግራም በግልፅ የእዚህን አርሶ አደር ፍላጐቶች መሠረት ማድረግ የግድ ይለዋል ። አርሶ አደር ያልሆኑትንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ፣ የተማረውን የባለሙያውን

የባለሀብቱን ፍላጐት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ፍላጐታቸው ከአርሶ አደሩ ፍላጎት ጋር ተዋህዶ ሁሉንም ሊጋራ ብልፅግናና ግንባታ የሚያንሳሳ ፕሮግራም መሆን አለበት። በዚህ ብቻ አያበቃም። ይህንን የመሰለውን ፕሮግራም ግለሰቦች አርቅቀውት በኪሳቸው ስለ ያዙት ብቻ የአማራውን ሕዝብ እንወክላለን ሊሉ አይችሉም። ይህን ፕሮግራም የአማራው ሕዝብ ፕሮግራም ለማድረግ በፕሮግራሙ ዙሪያ የተሰባሰቡ ፣ ፕሮግራሙ የሚመለከታቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ያቀፈ የአንድ ድርጅት መመሪያ ሆኖ መፅደቅ አለበት።

በእዚህ ጉዳና ያለፈ አንድ ድርጅት በስሜትና በተነሳሽነት ደረጃ እራሱን የአማራው ሕዝብ ድርጅት ብሎ ቢጠራ የሚያስነውር አይሆንም። በግልፅ፣ በንግድ ድርጅትነት፣ በሰምበቴነት ወይም በጓደኛሞች ክበብነት ከሚቋቋሙ የዘመኑ የፖለቲካ ድርጅቶች የተለየ ነውና። ያም ሆነ ይህ በዚህ መንገድ የተመሠረተ ድርጅት እንኳን ሳይቀር በውል የአማራው ሕዝብ ተወካይነቱ የሚረጋገጠው የድርጅቱ ፕሮግራም በአብዛኛው የአማራው ሕዝብ ነፃ ውሣኔ ተቀባይነት አግኝቶ መዛባት ሳይደርስበት በተግባር የሚተረጐምበት ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው።



ምዕራፍ 7

## ቅርብና ሩቅ ባላችሁ አማሮች በሙሉ

ድንገት ለማያውቁን ፤ በብዙ ሚሊዮን እንቆጠራለን። የሕዝብ ቆጠራ ጠበብት አሥራ አራት ሚሊዮን ትሆናላችሁ ይሉናል። በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የተለያዩ ሕዝቦች አሰፋፈር ጋር ሲነፃፀር እንደ እኛ በሰፋት በኢትዮጵያ ውስጥ የተበታተነ የለም። በሃገሪቷ ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ በሆኑት ቁጥራችን ቢበዛም ቢያንስም ኗሪዎች ነን። በተለያዩ የሃገሪቱ ከተሞች የምንኖረው ከአጠቃላይ ሕዝባችን 5.6 ከመቶ ብቻ ነው። የተቀረው ወገናችን 94.4 ከመቶ የሚሆነው በገጠር የሚኖር አርሶ አደር ነው።

ከአሥራ አራት ሚሊዮን መሃከል ወደ አሥራ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የሚሆነው የሚኖረው በአንድ ክልል ነው። ቋንቋችን ፣ ባህላችን ፣ ታሪካችንና ሥነ ልቦናችን አንድ ሆኖ ግን ወሎዬ፣ ሸዌ ፣ ጐጃሜና ጐንደሬ እየተባልን የተጠናከረ የአማራ ብሔራዊ አንድነት እንዳይኖረን ተደርገናል። በዚህም የተነሳ ክልላችን የአማራውን ሕዝብ ያዋሃደ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት ሳይኖረው ቀርቷል።

በመሆኑም አሥራ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ህዝብ በምንኖርበት ክልል ስድስት ፋብሪካዎች አሉን። ከእነዚህ ሁለት ለስላሳ መጠጥ የሚሞላባቸው ናቸው። የኢንዱስትሪ አቅማችን የሚያሳዝን — የሚያስቅም ነው። ይህ ሕዝብ የሚኖርባቸው ክልሎች ያሉት ሐኪም ቤቶች በአንድ ሲደመሩ 820 በሽተኛ ብቻ ማስተናገድ የሚችሉ አልጋዎች አሏቸው። በወረርሽኝ የተጠቃን የአንድ ትንሽ መንደር ሕዝብ እንኳን ማስተናገድ የማይችሉ። የሐኪሞችም ብዛት 62 ነው። ለሁለት መቶ ሺህ ሕዝብ አንድ ሐኪም ይደርሰዋል። ይህም የሚሆነው እነዚህ ሐኪሞች በሁሉም ቦታዎች በዕኩልነት ተከፋፍለው እንደሚሠሩ አድርገን ካሬዝን ነው። ዕውነታው ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ለግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ አንድ ሐኪም አይደርሰውም።

ክረምትና በጋ የሚሠሩ መንገዶች ዘጠኝ ከመቶ ወረዳዎችን ብቻ ያገናኛሉ ። የተቀረው ዘጠና አንድ ከመቶ የክልላችን ኗሪ ዝናብ ባካፋ ቁጥር ከወገኖቹ ተቆራርጦ ምድሩ እስኪመጥ በየቀየው እስረኛ ሆኖ የሚኖር ነው ። በምድረ አማራ በየዓመቱ በመኪና አደጋ ከሚሞተው ወገናችን ይልቅ በጠመዝማዛው ጠባቡ የተራራ የእግር መንገዶች ሲጓዝ ገደል እየገባ የሚያልቀው ይበልጣል ። ባቡር የሚባል ነገር ለእኛ ገና አልተፈጠረም ። የዓየር ትራንስፖርትን ስሙን ካነሳነው ይበቃል ።

ወደ ትምህርት ስንመለስ በአማራው ክልል አንድም ዩኒቨርስቲ የለም ፣ ሁለት የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና አራት የተለያዩ ማሠልጠኛ ማዕከሎች አሉ ። ዕድሜው ለትምህርት ደርሶ ትምህርት ቤት የሚገባው ወጣት አሥራ አራት ከመቶ ብቻ ነው ። ሰማንያ ስድስት ከመቶ የሆነው ወጣት የመማር ዕድል አጥቶ እጣው የከብት ጭራ ተከትሎ ሲማስን መዋል ነው ።

የውኃና የመብራት አገልግሎት በአማራው ክልል ካሉት በመቶ ከሚቆጠሩ ወረዳዎች መሐከል ለሃያ አንዱ እንደነገሩ ይደርሳቸዋል ። የፖስታና የስልክ አገልግሎት አሥራ ሁለት ወረዳዎች ብቻ ያገኛሉ ። የባንክና ሌሎች ገንዘብ ነክ አገልግሎቶች ፈጽሞ የሉም ማለቱ ያስደፍራል ። በአሥር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች የሚኖሩበት ጐንደርን ፣ ጐጃምን ፣ ወሎንና ከፊል ሸዋን የሚያክል ክልል አሥራ አንድ ነዳጅ ማደያዎች ብቻ አሉት ።

ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ፣ ለትዝብት የሚዳርጉን ስድስት የቀርኢት ማሳያ አዳራሾች ፣ አምስት የስፖርትና የባሕል ማዕከሎች አሉን ። ቴሌቪዥን በዓይኑ አይቶ የሚያውቀው ሕዝባችን አንድ ከመቶ በታች ብቻ ነው ።

እንዲያው እንዘርዝረው እንጂ ይህ ዘገባማ የአማራውን ሕዝብ አሰቃቂ የድኅነት ሕይወት አሟልቶ አይገልፀውም ። መረጃው ከሚሰጣቸው ቁጥሮች ጀርባ ያለውን የስብዕና መራከስ ፣ የውርደትና የሰቆቃ ሕይወት አያሳይም ።

ይህ ሕይወት ግን እንዲህ ይመስላል ።

በየወቅቱ ቀጠሮ ያለበት ይመስል ችነፈር ጊዜን ቆጥሮ ይመጣል። ሮጠው ያልጠገቡ ከሰምበሌጥ የሰለሉ እግሮች ፣ የሞት ትል የሚተራመስባቸው ፣ የተነረቱ ፣ በልተው የማያውቁ ሆድቃዎች ፣ እንደጋን የተ



ጋነኑ ፣ የዕውቀት ብርሃን ያልዳሰሳቸው ጭንቅላቶች ፣ በጭንቅላቶቹም መሃል የተሰፉ ብርሃናቸው የቀዘቀዘ እንደ ሲኦል የጉድጓዱ ዓይኖች ያሉዋቸውን በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሕፃናትና ወጣቶችን በጣረሞት ሰልፍ ወደ ከርሰ ምድር ያጉዛል ። ችነፈር ።

ከዚህ የሚያመልጡትም አፈር ላይ እንደተወለዱ ፣ አፈር ላይ አድገው ፣ አፈር ገፍተው ፣ አፈር በልተው ፣ አፈር ውስጥ ኖረው ፣ አፈር እንደመሰሉ ወደ አፈር ይመለሳሉ ።

እናቶችና እህቶች ለወፍጮ የሰገዱበት ጉልበታቸው መጅ ሆኖ ፣ መጅ የያዙበት እጃቸው ፣ መጅ አብቅሎ ፣ ለእንሥራና ሞት በወረንጦ ለሚለቅማቸው ሕፃናት ልጆቻቸው ሸክም የተፈጠረ ጀርባቸው ጭነት እንደበዛበት አጋሰስ ተግብጦ ፣ በአወይ መፈጠር የነጋ ጠባ ዋይታ ዓይናቸው እምባ ልባቸው ደም ያለቅሳል ።

የነፃነት ፣ የገድልና የጀግንነት መድረኮች ፣ እነያ የምድረ አማራ ተራራዎችና ሸንተረሮች ፣ ከልጆቻቸው የሲቃና የጣር ጩኸት አስተጋቢነት ወደ ሳቅና የዕልልታ ገደል ማሚቶነት እራሳቸውን የመቀየር ምኞታቸው ዛሬም እንደ ጥንቱ ተስፋ ብቻ ነው ።

ወባና ተስቦ በትኩሳትና በቅዝዋት እያሰቃዩ እንደአሻቸው እንደ ክረምት ጉመን የሚቀረድዱት ሕይወት ዛሬም አዛውንቱን ያለ ጧሪ ፣ ሕፃናትን ያለአባት ፣ ሚስትን ያለባል ፣ ባልን ያለ ሚስት እያስቀረ የአማራውን ሕዝብ ቅስም እንደሰበረ ነው ።

## ይህ ነው

እኛ እስከምናውቀው የአማራው ሕዝብ ሕይወት ይህ ነው ። ይህንን ታሪክ ይህንን ዕውነታ ማንም በገዥነትና በአቅኚነት ስም ሊሸፍነው አይችልም ። ጀግናና ኩሩ የሚል የቀባት ፋፋቴ በየመድረኩ ቢፈሰልን ሆዳችን አይሞላም ። እከካችን አይራገፍም ። በሽታችን ፣ አይድንም ። እርቃናችን አይሸፈንም ። ስቃያችንም አያበቃም ። ዛሬ ይህን ሐቅ ከመቼውም በላይ አፍጦ እንዲወጣ ያደረገ ዘመን ስለመጣ አማራው ተዋረደ የሚሉን ሞልተዋል ። አዎን ተዋርደናል ። ውርደቱ ግን የአቅኚነትና የገዥነት ታሪክ የሸፈነው ገበናችን ሲገለጥ ያየነው አስከፊ ድኅነታችንና ኋላቀርነታችንን ነው ። እንዲህ ዓይነቱን የውርደት ክስ ለመከላከል አማራው ምን ተበደለ? እንደ ሌሎቹ ሕዝቦች እሱም በቋ

ንቋው በባሕሉ እንዲኮራ ተደረገ እንጂ የሚሉንም አልታጡም ። አማራው በቋንቋና በባህሉ ተዋርዶ አያውቅም ። የቋንቋና የባሕል ኩራት ሰበኪም በተነፃፃሪነት በንቀት የሚታዩ ቋንቋዎችና ባሕሎች ሳያስቀምጥ በራሱ ስለማይቆም የሚያኮሩ ድርጊቶች ድኅነት የተጠና ወታቸው ብቻ የሚያላገኑት ነው ።

እኛ ግን ስናየው የመጣነው የድኅነት ውርደት እንዲሸፈን ፥ እንዲደበቅ መፈለግ የለብንም ። ይህ ውርደት እንደ ውሻ ጭራችንን በእግራችን መሐከል ሸጉጠን እንድንልከሰከስ አያደርገንም ። ቁጣችንን ወደ እራሳችን እንድንመልስ የሚገፋን እንጂ ። አንበሳው ለመስፈን ጠር መንበርከክ አለበት ። የኛ መንበርከክም ከአንበሳው የተለየ አይደለም ።

ከዘመናት የረሐብ የድንቁርና የመብትና የፍትህ እልባ ታሪካችን መሃል እንደፈርጥ የሚያበሩ አኩሪ ታሪኮች ቢኖሩንም ዋንኛው ታሪካችን ግን ገና አልተሣፈም ። በድርቅ ቦታ ልምላሜን ፥ በመብት ረገጣ ፈንታ ነፃነትን ፥ በጦርነት ቦታ ሰላምን ፥ በኋላቀርነት ምትክ ዕድገትን በማምጣት ብቻ ነው ይህንን አኩሪ ታሪክ የምንፅፈው ። እንዲህ ዓይነቱ ታሪክ ሠፊ ሰብዓዊ መሠረት የሚኖረው ከንዋኔ ነውና አኩሪነቱ ከእኛም አልፎ ሰበዕና ለተላበሱ ሕዝቦች ሁሉ ይሆናል ። ለእንዲህ ዓይነቱ ክንዋኔ ደግሞ እስከአሁን በአጠቃላይ ስንገልጸው የመጣነውን የሃገራችንን አዲስ ዕውነታ መቀበል የግድ ይሆናል ። አማራነትንና የአማራ ብሔረተኝነትን ከጭፍን ስሜት ውጭ በመቀበል ብቻ ነው ፤ ይህ ታሪክ የሚሠራው ።

በአማራ ብሔረተኝነት ጥያቄ ላይ ግልፅነት እስከአለን ፥ እንደ ሕዝብ የሚጠበቅብንን እጅግ አስቸጋሪ ትግል ለመወጣት ከአሁኑ የሚያስፈልገውን እንደብረት የተጠናከረ አንድነትና የእምነት ፅናት ከተረዳን ፥ ለዚህም ግንዛቤ መስፋፋት ሩቅም ቅርብም ያለን አማሮች እስከሠራን ፥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማሮች የሚኮሩበትን ሕዝባዊ የአማራ ብሔረተኝነት እንቅስቃሴ ማየት አያስቸግርም ።

በዚህ ጽሑፍ ላይ ለሚኖር አስተያየት የፖ.ሣ. ቁ. 101943 ይጠቀሙ